# ታጠቅ

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ህብረት

የቲዎሪ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

## ረሃብና ድህነት በባህል፣ ረሃብና ድህነት በኢትዮጵያ


የመጽሄት አዘጋጅ ቦርድ፡

P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHLM 3
SWEDEN


ግንቦት 1977

# ይ ዘ ት

1.0 መግቢያ

2.0 የሕዝብ ብዛትና ድርቅ ለረሐብ ዋና ምክንያት ?

2.1 የሕዝብ ብዛት ለረሐብ ዋና ምክንያት ?

2.2 ድርቅ ለረሐብ ዋና ምክንያት ?

3.0 ኮሎኒያሊዝም ለዛሬው የባህል ሀገሮች ረሀብ ተጠያቂ ነው ::

3.1 ኮሎኒያሊዝም በባህል ሀገሮች ላይ ያደረሰው ጠንቅ ::

3.2 ከኮሎኒያሊዝም በኋላ ::

4.0 የኢትዮጵያ ረሀብ ምክንያትና መነሻ ::

4.1 የደርግ ሁኔታ በመሬት ርዳገት / ጋይሶች / ላይ ያለው አሉታዊ ውጤትና አጠቃላይ ሁኔታ ::

4.2 የበጫኸ ሁኔታ

4.3 የኃይል /Energy /ችግር የፖለቲካ ውጤት ነው ::

4.4 የኃይለስላሴ መንግሥት የእርሻ ፖሊሲ ::

4.5 የቡና ሚና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ

5.0 በአብዮቱ ጊዜና ወዲህ ::

5.1 የመሬት ለአራሹ መታወጅና አገዛዙ ::

5.2 ለምን መንግሥቱ መንቀፍ ለመሬት አለማደግ፣ ለረሀቡ ተጠያቂ ይሆናል ::

5.2.1 የደርግ የእርሻ ፖሊሲ ከ1975 ዓ.ም ጀምሮ ::

5.2.2 የገበሬት አርሻና በገበሬው ላይ የሚደረገው ተጽዕኖ ::

5.3 ጦርነትና ረሀብ

5.4 የደርግ ሠፈራ ፕሮግራምና የሚያመጣው ውጤት

6.0 መ ደ ም . ደ ሚ ያ

መጽሐፍትና ስታትስቲክስ ከገጽ 71 እስከ 72

## 1.0 መግቢያ

ከጥቂት ዓመታት ጀምሮ በተለይም ከአንድ ዓመት ወዲህ ረሐብ በባህል አከባቢ ያሉ ሀገሮችንና ኢትዮጵያችንን እያጠቃ ነው ፡፡ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሕዝቦች እንደቅጠል እየረገፉ፣ እየተሰደዱና የተረፉት ደግሞ በበሽታ እየማቀቁ የሚያሳብትን ቀን እየተጠባበቁ ነው ፡፡ ከተወለዱበትና ከአደገበት አከባቢ ከረሐብ ለማለቀ በረሐ እያቋረጠ የሚጓዘውና በየቦታው እየተደፋ የሚቀረው ስፍር ቁጥር የለውም ፡፡

በባህል አከባቢና በኢትዮጵያችን ለገጠው ረሐብ የተለያዩ የምዕራብ ኤክስፐርቶች የተለያዩ ምክንያቶችና የተለያዩ መፍትሔዎች ይሰጣሉ ፡፡ አንዳንዶቹ ለረሐቡና ለድሀነት ዋናው ምክንያት የሕዝብ ብዛት ነው ይላሉ ፡፡ በሌላ አነጋገር በዓመት ውስጥ በቁጥር እየጨመረ የሚመጣው የሕዝብ ብዛት ከሚመረተው ምርት የበለጠ ስለሆነ፣ ስለዚህም የሕዝብ ብዛት ዕድገትና የምግብ መጠን መጨመር ለምጣጠኑ አልቻሉም ይላሉ ፡፡ ሌሎች ደግሞ፣ ለረሐቡ ዋናው ምክንያት የሆነው የአፈሩ ለምለምነት / fertility / በጣም ዝቅተኛ ስለሆነና የአየር ሀይል መሬት ጠርጎት የአፈር ጠባዩ ካለው የአውሮፓ መሬት ጋር ሲወዳደር ሊታረስ የሚችለው የላይኛው መሬት ክፍል / Topsoil / ተሸርሽሮ በጣም ያነሰ በመሆኑ የሚሰጠው ምርት በሄክታር ዝቅተኛ ነው ይላሉ ፡፡ ጥቂቶች ደግሞ፣ ለረሐቡ ዋናው ምክንያት በየጊዜው እየተመላለሰ የሚመጣው ድርቅ ነው በማለት ነገሩን ይዘጉታል ፡፡ ሌሎች ደግሞ፣ በከተማ በሚኖረው ተመጋቢ መሀከልና በተለይም በተማረውና ጥሩ ቦታ ባለውና / Elits / በአራሹ መሀከል ያለው ቅራኔ ለረሃቡ ዋናው ምክንያት ነው ይላሉ ፡፡ በሌላ አነጋገር በከተማ የሚኖረው በየጊዜው ከሚያድገው ገበሬ እየተከፈለ የሚወስደው የምግብ /እህል/ መጠን በረሰ ቢተመን እያደገ በመምጣቱ የገጠሩ የምግብ ሁኔታ ዝቅ እያለና ለአርሻ ከሐዝ በጣም ለረሐቡ ዋና ምክንያት ሆነ ይላሉ ፡፡ ሌሎች ተራማጅ አስተሳሰብ ያላቸውና የረሐቡን ምክንያት ከሌሎች በተሻለ መልክና ሁኔታ የሚያቀርቡት ደግሞ፣ በባህል አከባቢ ለገጠው ረሀብ መነሾ ድርቅ ባይሆን በአንዳንድ የባህል አከባቢዎች የነበረው የቅኝ ገዢ አስተዳደር ያመጣው ወንቀና ዛሬም ቢሆን እነዚህ አገሮች በሌላ መልክ ስለሚበዘበዙና የአፍ አዙር ቅኝ አገዛዝ ውጥመድ ውስጥ ስለገቡና ይህ ካለው የፑሻል ሲስተም ጋር በመተባበሩ ነው ይላሉ ፡፡



እንግዲህ ይህንን ስንመለከት ረሐብና ድህነት ራሱን የቻለ የርዕዮተ ዓለም መሠረት መድረክ ሆኖአል ፡፡ ምክንያቱና የአተናተኑም ዘዴ በተለያዩ ኤክስፐርቶች ዘንድ የተለያየውን ያህል መፍትሔውም እንደዚሁ የተለያየ ነው ፡፡ በእነዚህ የከበርቴውን ቲዮሪ አንደ ችግር መተንተኛና አንደ መፍትሔ አድርገው በሚያቀርቡና ይህንን በሚቃወሙ መሀከል ልዩነት እንዳለ ሁሉ በእኛ በኢትዮጵያዊያንም ዘንድ እንደዚሁ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የችግሩን ምንጭ በመረዳትና በመተንተን ረገድ ከፍተኛ ልዩነት አለ ፡፡ ለምሳሌ አንዳንዶቹ ዝም በሳቹ ነው እንዴት ለዛሬው ረሐብ ዋናው ምክንያት ፖለቲካ ሊሆን ይችላል፣ የተፈጥሮ አደጋ ነው እንጂ ይላሉ ፡፡ ሌሎች ፖለቲካ ነው የሚሉት ከእኛ ጋር አጠቃላይ ስምምነት ያላቸው ደግሞ የነገሩን ምንነት ጥልቀትና ዋና ምክንያት በሚገባ አያባዩም ፡፡ እንዲያው በአጠቃላይ መልኩ ቢቻ በመወሰን ፖለቲካ ነው ይላሉ ፡፡ ነገር ግን በአተናተን ደረጃ ከከበርቴው ኤክስፐርቶች አምበዛም አይለያዩም ፡፡ የእነዚህ ሁሉ ችግር ከምን የመነጨ ነው ?

በከበርቴው ቲዮሪና በግራ ቲዮሪ መሀከል የተለየ አስተሳሰብ ቢኖር ይህ ዓይነቱ የተለየ አተናተንና ችግርን መረዳት በእኛ ላይ ቢንፀባረቅም ሊገርመን አይገባም ፡፡ ችግሩ ግን በአንድ በኩል በግራ ስም እየታገሉ ባያውቁት ደግሞ የከበርቴውን ቲዮሪ ማንፀባረቃና የአተናተን ዘዴ መጠቀም የነገሮችን ልዩነት በሚገባ ለመረዳት ያለመቻል ነው ፡፡ እነዚህ የርዕዮተ ዓለም ትግል የሚካሄድባቸው፣ የከበርቴው ቲዮሬቲሺያንና ኤክስፐርቶች የበላይነታቸውን ለማስፈንና እንዳሰፈኑ ለመቀየት የሚፈወጡባቸው መድረኮች እንደሆኑ ለብዙዎቻችን ገልጽ አይደለም ፡፡ አንድ ነገር ለመረዳት፣ ለማወቅና በሙሉ በሌ የሆነ ትንተና ለመስጠት ስያች የዚያን ነገር ምንነት ቶሎ በለው ለመረዳት አይችሉም ፡፡ የገባውም ቢሆን እነዚያን ስያች በቀላሉ ለማስረዳትና ቀጥተኛ የሆነ መልስ ለመስጠት አይችልም ፡፡ የአንድን ነገር፣ ወይንም የነገሮችን ምንነት ለመረዳት ይቻል ዘንድ፣ ስያች በቁንቀላታቸው ውስጥ ማውጣትና ማውረድ አለባቸው የነገሩን በሉት ለማገኘት የዚያን ነገር ሁለንተና / in its totality / እየበነጠጠቁና በሙሉ እየገጠሙ፣ መጀመሪያ በአበስትራክት መልኩና በቲዮሪ ደረጃ፣ ከዚያም በተጨባጭ ማሳየት መቻል አለባቸው ፡፡

በነገሮች መሀከል ያለውን ግኑኙነትና አንዱ በአንዱ ላይ የሚያደርገውን ተጽ ዕኖ ለመመልከትና ለመተንተን መሞከር አለባቸው ። የዚያን ነገር ምንነት ለመረዳት የተሟላ የዙሪያ መንገድ ይጓዛሉ ማለት ነው ። ይህንን ካላደረጉ ግን ነገሮችን የነጣጠለው በማቅረብ ብቻ ይገታሉ ። ይህ ዓይነት ሁኔታ በአ ስተሳሰብ ውስጥ በተቀረጸበት ቦታ፣ የተለያዩ የትምህርት ዘርፎች በሚሰጡበትና እነዚህ የርዕዮተዓለም መሬቶች መድረኮች በሆኑበት ዓለም ውስጥ እነዚህ ቦታዎች በቀላሉ በይሆናል / Assumption / ወይንም ከኅብረተሰብ ዕጤና በላይ ተመርኩዞ በሚቀርበው የከበርቴው ቲዎሪ በመቃረክ ወደ ተራ አነጋገርና ባይገቡ ፤ ይዘት ወደ ሌላቸው ነገሮች በማምራት ነገሩን አታለው ያቀርባሉ ። ከዚህ - የተለየ አስተሳሰብ የሚያቀርቡት ቦታዎች ደግሞ በከበርቴው ቲዎሬቲሺያንና ይህንን በሚያስተጋቡት ዘንዱ እንደ አረፃ ቲዎሪ ይቆጠራል ። ወይንም ደግሞ የበሰለ አይ ደለም ። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ደግሞ ነገሮች መልካቸውን ያጡና፣ መስ መሬቸውን ስተው በተራና በቀላል አነጋገር የሚደረገው ውይይት የሚካሄደው ነገር " ምራቅ በአል ምጦና ምራቅ በ ምጡ መሀከል " የሚሆን ይመስላል ። ነገሩ እንደ ዚሁ እያለ የመሬቸያ ሆና ይቀራል ። ቦታች እውነትን ለመፈለግ ባይችሉና ተረት ባያደርጉ ከቀን ቀን፣ ከበሻምነት በምነት፣ ከወሬት ወሬ፣ ... በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ እንደታሰሩ ተር ተው፣ እነዚያ " ትክክል ነው ያሏቸው "" ምራቅ የጥ አን ጋገርና ትንተና " የተባለለት አስተሳሰብ ለችግሩ ምንም መልስ ባይሆን ይታያል ።

የከበርቴው ቲዎሪ በተለየም ደግሞ በሶሻል ሳይንስ ላይ እንደዚሁ ነው ። የከበርቴው ቲዎሬቲሺያንና ኤክስፐርቶች በዙ "ቲዎሪያቸን" ቢዙ የቴክኒካል "ዘዴ ዎችን" እየፈለጉ የኅብረተሰብ ችግርን "ለመፍታት" ይሯሯጣሉ ። ይህ ዓለም አቀፍ ፤ ተቀባይነት እንዲኖረው በየትምህርት ቤቱ እንዲሁም ከፍተኛ ቦታ ያደር ጋሉ ። ይህንን ቢያደርጉ ግን እውነተኛ የችግሩን ምንነት ለመረዳትና ፍቱን መፍትሔ ለመስጠት ሳይሆን የነገሮችን ውጪት ላይ ላዩን በማመልከትና ከጥንቱ ችግር እየሸሹ ነው ። ከዚያም የኅብረተሰብ ችግርና የዓለም ችግር ባይፈታ፣ ድህነት እየነገሰ፣ ረሀብ እየተስፋፋ፣ ጦርነት በዓለም ሕዝብ ጭንቀት ላይ እያስገመገመ፣ አካባቢ



እየቀሸሸና እየተመረዘ፣ ኅብረተሰብ ከአንዱ ፊዝ ወደ ሌላ ፊዝ እየተሸጋ ገረ ነገሮች ውስብስብ እየሆኑና በዚያው መጠን ደግሞ አዳዲስ ምዕራፎችና ቴክ ኒካል " መፍትሔዎች" እየተፈጠረላቸው የዙሪያ ጥምጥም ውስጥ ቢገባ ይታያል፡፡ ይህንን ግን ማንኛውም ተራ ሰው አይረዳውም ። ወይንም በቀላል የአካዳሚክ ዕውቀት መገንዘብ አይቻልም ። የተሟላ ከፍተኛ የሆነ የጥንቃት ትግል ማደ ረግ ያስፈልጋል ። ይህንን ለማድረግ የሚፈልግ በመጀመሪያ ስለሰው ልጅ አፈጣ ጠርና ስለተፈጥሮ እንዲሁም ስለሰው ልጅ ታሪካዊ ልምዱና ዕድገት ያለውን አስ ተሳሰብ በጠቅላላው መቀየር አለበት ። ይህንን ባያደርግ ግን፣ ወይንም ዓለም እንደዚህ የተፈጠረች አድርጎ የሚወስድ ከሆነ ትክክለኛ መልስና መፍትሔ ለማግ ኘት በፍጹም አይቻልም ።

ስለ ኢትዮጵያ ረሀብና ሀገሪቱ ስለወደቀችበት የኅብረተሰብ ቀውስ፣ የች ግሩን ምንነት ለመረዳት እንደዚሁ የተሟላ የዙሪያ ጥዝና ትንተና ያስፈልጋል ። የዛሬው መንግሥት ለዛሬው ረሀብ ተጠያቂ ነው ቢባል ወይንም ቶና ችግሩ የፖለ ቲካ ነው ቢባል እነዚህን በረዱፍ በረዱፍአቸው መመልከትና ማስቀመጥ ያስፈልጋል ። ይህ ብቻ አይበቃም ። የዛሬው አገዛዝ ምንነት፣ የተቀመጠበት የሥልጣን አውታር፣ የኅብረተሰብአችን አወቃቀር፣ ምንም እንኳ ለውጥ ቢኖር፣ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብና የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ተቋሞና የአሠራር እንዲሁም የአመራረት ዘዴዎች ከፊዩዳሉ የአሠራርና የአመራረት ዘዴዎች በፍጹም ያልተለዩ መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል ። የፊዩዳሉ ባህል፣ የፊዩዳሉ ርዕዮተ ዓለምና ፖለቲካ፣ ኋላና፤ አስተሳሰብ፣ የፖለ ቲካ ኃላቀርነትና የመደብ ትግል መሳከ አለመያዝና መዘበራረቅ በኅብረተሰብአችን ውስጥ አሁንም ቢሆን ማንተማቸውን የረገጡ ናቸው ። እነዚህም የረጅም ጊዜ ትግል የሚጠይቁና የሚፈልጉ ናቸው ።

ይህች አጭር የረሀብ ጥናት እነዚህን ሁሉ ለመንካት አትቻልም ። ምክንያ ቱም ነገሮች ከመጠን በላይ ይበረሉ ። ስለዚህም ረሀብ የኅብረተሰብአችን ተደጋጋሚ / cyclical / ችግር እንደመሆኑ መጠን የዚህች ጽሑፍ ተግባር የዚህን ረሀብ ምንጭና በኅብረተሰብአችን ውስጥ ያለውን አሉታዊ ውጤቶች ማሳየት ብቻ ይሆናል ። በሌላ በኩልም ይህች ጽሑፍ ማንኛውንም በትምህርት ያለ ሆነ በየሙያ በውጪ ሀገር

ተበጣርቶ የሚሠራውን ኢትዮጵያዊ ስለ ሀገራችን ተደጋጋሚ ረሐብ በበሬው አን ጊያጠና የምትጋርዝ ትሆናለች ። ረሐብ የኅብረተሰባችን ችግር ነው ። ይህም ችግር መሠረታዊ ባይነባሮ መፍትሔ የሚያስፈልገው ነው ።

በመጀመሪያ ደረጃ ግን የረሐቡን ዋና ችግርና ምንጭ በባህል አካባቢ በአጠቃላይ መመልከት ተገቢ ነው ። በዚህ ውስጥ ሰዎች ከበርቴው ቲዎሬቲክያን እንደሚሉት ድርቅና የሕዝብ ብዛት ለረሐቡ ዋና ምክንያት እንዳልሆኑ፣ ለምን በየጊዜው የባህል አካባቢ ሀገሮች በየጊዜው ለረሐብ መጋለጥ እንደተገለጹ እናመለክታለን ። በሌላ በኩል ግን ድርቅ በምጣም ረሐብን መከላከል እንደሚቻል፣ የሰዎችን ሕይወት መጠበቅ እንደሚቻልና ይህ ከፖለቲካ ሲስተም ጋርና ከዓለም አቀፍ ካፒታሊዝም የአገዛዝ መካኒዝም ጋር እንዴት እንደተያያዘና እንዴት በዓለም አቀፍ ደረጃ ረሐብ እንደሚፈጠር /reproduce / በመጠኑም ቢሆን እናሳያለን ። የጽሑፉ ዋና ይዘትና የመጨረሻው ክፍል የኢትዮጵያን ረሐብ በተለየ መልኩ የሚያመለክት ነው ።



## 2.0 "የህዝብ ብዛትና ድርቅ ለረሐብ ዋና ምክንያት"

### 2.1 የህዝብ ብዛት ለረሐብ ዋና ምክንያት?

በቴሌቪዥን፣ በመጽሔቶች፣ በዓለም አቀፍ ድርጅቶች አማካይነት በየጊዜው በባህል አካባቢና በሌሎች አገሮች ስለሚደርሰው ረሐብ የሚሰጠው ዋና ምክንያት በሦስተኛው ዓለም ሀገሮች የሕዝብ ብዛት ዕድገት እየጨመረ ስለሚሄድና ይህ በየጊዜው ረሐብን እንደሚያመጣና እንዲያውም መቆጣጠር እንደሚያስፈልግ ነው ።

በእርግጥ፣ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ አንድ ልጅ፣ ሁለት ልጅ ... እየተጋለደ በሄደ ቁጥር የቤተሰብ ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ በዚያው መጠን ደግሞ የቤተሰቡ ጋሬሃ ገቢ ወይም ዓመታዊ ገቢ ካሳደገ ወይም በሌላ መልኩ፣ ከመንግሥት በዱጉማ፣ የልጅ ገንዘብ እየተባለ ገቢው ካሳደገ ቀደም ባለው ገቢ ብቻ እየተገዛ የሚመጣው ምግብ በራስ ቢከፈል ዝቅ እያለ ይሄዳል ። ወረሐዊ ገቢ ካሳደገ ወይም ከጨመረ የቤተቡ ጋሳፊዎች ወይም ግሳጆች የሚገዙትን የምግብ ዓይነትና የለመዱትን ትተው ወደ ዝቅተኛ የምግብ ዓይነት ገዥ ይጋርዳሉ ። ለምሳሌ ሥጋና ቅቤ ከዚህ ቀደም በየሁለት ቀኑ ይመገቡ ከነበረ ይህ በአብና በዜይት ወይም በማርጋሪን /በአትክልት ቅቤ/ ለመተካት ይገደዳሉ ። ወይም በሳምንት አንድ ጊዜ ብቻ ሥጋና ቅቤ ይመገባሉ ።

ይህንን ወደ አራሽ ሁኔታ ላይ ብንተረጉመው፣ የአንድ ገበሬ ቤተሰብ ከአንድ እስከ ሁለት ሄክታር መሬት የሚያርስ በየጊዜው የቤተሰቡ ቁጥር እየጨመረ ከሄደ የመሬቱ ስፋት ብቻ ባይሆን ምርትን ለማሳደግና ቤተሰቡንም ለመመገብ ይችል ዘንድ የሚያርስበትን ዘዴ ካላሻሻለ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ያው መሬት በየጊዜው እየተሰላሰ ከታረሰ የሚሰጠው የእርሻ ውጤት ከዓመት ዓመት ዝቅ እያለ ይሄዳል ማለት ነው ። በዚህም ዝቅተኛ ምርት በቁጥር እየጨመረ ለሄደው ቤተሰብ ቢከፋፈል መጠኑ እንደ እንደ ድርሻው ባይሆን አነስተኛ ይሆናል ማለት ነው ። በጋቾ፣ ከዚህ በፊት በቀን ሦስቴ ይመገቡ ከነበር፣ ሁለቴ ከዚያ ደግሞ አንዴ ብቻ እንዲመገቡ ይገደዳሉ ።

ይህ ተራ ሶሿሊ ነው ። ነገር ግን አንድ ገበሬ ወይንም ገበሬዎች መሬታቸውን እንዳያበሩ፣ የመረረት ዘዴአቸውን በየጊዜው እንዳያሻሽሉና በየጊዜው ከሚታዩና ከሚመጣ አደጋ እንዳይከላከሉ የሚያግዷቸው ምክንያቶች አሉ ። መሬት በጥቂቶች በተያዘበት፣ ሰፊው ገበሬ ሕዝብ በየጊዜው በትንሽ አካባቢ ብቻ ተወስና እንዲያርስ በሚገደድበት፣ ፊውዳሊያዊ ስርዓት በሌለበት ሀገር የተጋበነ ርዕዮተ ዓለምና የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንደ መፍትሔ በሚቀርብበት ሀገር፣ እነዚያ በየጊዜው በዚያው መሬት ብቻ ላይ እንዲያርሱ የሚገደዱት ገበሬዎች ለረሃብና ለአደጋ ይጋለጣሉ ።ይህንን ችግር ለመቋቋም የሚደረገው ሙከራ ደግሞ ባይገባ ፣ ባይሆን ተራ የቴክኒካል መፍትሔ ይሆናል ።

በሌላ በኩል ደግሞ በአንድ ሀገር ውስጥ የህዝቡ ቁጥርም እየጨመረ በአየዓመት የሚታረሰው ምርት ከፍ እያለ ቢሄድ ሕዝቦቹ በሙሉ የዚህ የምርት ዕድገት ተጠቃሚ ይሆናሉ ማለት አይደለም ። ወይንም ደግሞ 90 በመቶ የሚሆነው የአንድ ሀገር ሕዝብ አንድ ሀገር ከሚመችበት የኢኮኖሚ ሥርዓት የተነሳ የሚያመርተው ምርት ከእጁ ወደ አፍ ከሆነና ለሌ የምገብ ለምዱ ያለው ከሆነው ይህ በገበያ ላይ እንደሌሎች ምርቶች በበዛት በማይቀርብበት ሀገርና የገንዘብ ኢኮኖሚ ያልተስፋፋና ይህ ውጤት በገንዘብ መተመን / quantify / አስቸጋሪ የሚሆን ከሆነ የዚህ ሀገር የኢኮኖሚ ዕድገት በዚህ ያህል ፐርሰንት ቢያድግ፣ የሕዝቡ ቁጥር በዚህ ፐርሰንት በመጨመሩ ረሃብ ለመጣ ችሏል በሉ ሁለቱን ማገናኘትና ማወዳደር በፍጹም አይቻልም ። ይህም ማለት የኢኮኖሚው ዕድገት እንዴት ይከፋፈላል / Distribute /፣ የትኛው የኅብረተሰብ ክፍል የዚህ ዕድገት ተጠቃሚ ነው የሚለውን የግዴታ ማጠታለል አለበት ማለት ነው ። በተጨማሪ በአንድ ሀገር ውስጥ የሕዝብ ብዛት በቁጥር ከፍተኛ ሆኖና ለእያንዳንዱ አራሽ የሚደርሰው መሬት በራስ ሲለካ በጣም ዝቅተኛ ሆኖ ምርቱ ከፍ ሊል ይችላል ። ሕዝቡም ከረሃብ ሊድን ይችላል ። በሌላ ወገን ግን የሕዝቡ ቁጥር ከሚታረሰው መሬት ጋር ሲወዳደር ለእያንዳንዱ አራሽ የሚደርሰው መሬት በሄክታር ሲለካ / Hypothetical / ከፍተኛ ሆኖ የሚደርሰው የእርሻ ውጤት ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል ። ወይንም ቢተበቡን በሚገባ ለመገበ አይችልም ። አንዱ ሚሊያርድ ሕዝብ የሚኖርባት ቻይናን በነወሰዱ እያንዳ



ንዱ ሰው በራስ የሚደርሰው መሬት ከሌሎች ሀገሮች ጋር ሲወዳደር በጣም ዝቅተኛ ሆና ግን ሕዝቧን በበቂው መመገብ ትችላለች ።

እንግዲህ የሕዝብ ብዛት የረሃብና የድንነት ምክንያት ያልሆነውን ያህል የምርት ማደግም ብቻውን ለችግሩ መፍትሔ ሊሆን አይችልም ። የሚታረሰው ለማን? እንዴት ይከፋፈላል? ሰፊው ሕዝብስ የዚህ የምርት ዕድገት ተጠቃሚ ነው ወይ? የሚለውን መመለስ መቻል አለበት ። ይልቁንስ የኢኮኖሚ ኃላ ቀርነትና የፖለቲካ ጥያቄያች አለመፈታት በአንድ አካባቢ "የኢኮኖሚ ዕድገቶች ማበብ" ለሕዝብ ብዛት ተጠያቂ ነው ። ለምሳሌ በአንድ አካባቢ ወይንም ከተማ አንድ የኢንዱስትሪ ዞን ወይንም ኢንዱስትሪዎች ቢቋቋሙ በእነዚህ አዲስ በተቋቋሙት ኢንዱስትሪዎች ውስጥ እየተቀጠረ ለመሥራት ከገጠር እየፈለሰ የመጣው ሠራተኛ ሕዝብና የሥራ ዕድል ለማግኘት ያልቻለው ቁጥር እየበዛ ሲሄድ በአንዱ አካባቢ አንዲካች ተገደደ ።በሌላ በኩል በገጠር ውስጥ በእያንዳንዱ አካባቢዎች በዘመና ፣ የአስተራረስ ዘዴ የሚታረሱት እርሻዎች በጣም ዘመና ፣ ከመሆናቸው የተነሳ የገጠሬውንአራሽ ከቦታ እያስለቀቁ ወደ ከተማ እንዲፈልስ አስገደዱት ። ይህ በጥቂት ከተሞች ውስጥ የሕዝብን ብዛት / relative overpopulation / አስከተለ ። የሕዝብ ብዛት ውጤት / Effect / እንጂ ምክንያት / Cause / አይደለም ማለት ነው ። እነዚህን ነገሮች በበቂው ለመመለስ የማይችል ቲዎሪ፣ ምክንያትና ውጤትን እያገለባበጠ ሙ ያስቀምጥ ገፀሀ የርዕዮተ ዓለም መሣሪያ ብቻ ነው ።

## 2.2 ድርቅ ለረሃብ ዳ ምክንያት ነው?

የድርቅንም ሁኔታ እንመልከት ። ሰዎች በዚህች ዓለም ላይ በቀ ካሉበት ጊዜ ጀምሮ ከተፍጠል አልፈው በተሰበነ መስርተው ከዚያም እየተባዙና እያደጉ በሄዱ ቁጥር በርዱን ለመከላከል፣ አበስለው ለመብላት፣ ከአደጋ ለመከላከል፣ እንደ ልብስ፣ አባት፣ የነጣፈ ፣ ቤት...ወዘተ የመባበሉትንለመሥራት፣ ለመፍጠር ተገደዱ ። በሌላ ወገንም የተፈጥሮ ሁኔታ ሲለወጥ፣ ዝናብ ሲቀር፣ ሲደርቅ እንደዚሁ እነዚህን ሁኔታዎች ለመቋቋም ጉዳያቸውን የፍሬው ተፈና ተባል የመስኖ ዘዴን ይጠቀማሉ ።

ወይንም ካለፈው ምርታቸው ቀንሰው ዝናብ ይቀራል፣ ድርቅ ይመጣል በሚል ለዚህ ጊዜ የሚሆናቸውን ጎተራ ሠርተው ወይንም ጉድጓድ ቆፍረው በአበት መርገው እዚህ ለማከማቸት የድርቅን ጊዜ እንደ ምንም የወጣሉ :: ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶችና፣ በተለይም በአንድ ሀገር ውስጥ ያለው የመደብ ትግል በሚገባ ባላደገበትና ባልተስፋፋበት ሀገር አንድ ስርዓት ተፈጥሮ የምርት ኃይሎችን ከማሳደግ ይልቅ አቆርቋሪ በሚሆንበት ሀገር ውስጥ፣ በጋች ተፈጥሮ በተለያየ ጊዜ የሚያመጣባቸውን ሁኔታ ለመከላከል፣ ለመቋቋምና እዚህ ቴክኖሎጂ ፈጥረው ሁኔታውን ለማለፍ ይቸገራሉ :: በዚህም በቀላሉ ለአደጋ፣ ለድርቅ ብሎም ለረሀብ ይጋለጣሉ :: ድርቅ የተፈጥሮ አደጋ ነው፣ ምንም ለማድረግ አይቻልም የሚለው ተራ አነጋገር ሳይንስን ያዘለ አይደለም :: ድርቅ ለመኖሩ፣ ዝናብ በአንድ የተወሰነ ወቅት አለመምጣቱ ቢታወቅ በጋች ይህንን ሁኔታ ለመቋቋምና የዚህ ድርቅ ውጤት ተጠቂ እንዳይሆኑ፣ እንዳይረገፉ፣ ቤተሰባቸው እንዳይበታተን ምን ዓይነት እርምጃ መውሰድ ይችላሉ? በዚያ ሀገር ያለው አስተዳደርና መንግሥት ምን ያህል ዲሞክራትና ለሕዝቡ አሳቢ ነው? እርምጃዎችስ እንዴት በተፋጠነ መውሰድ ይችላል የሚሉት ጥያቄዎች መመለስ አለባቸው :: ለምሳሌ አንድ ሀገር በየጊዜው በዝናብ እጦት በድርቅ የምትጠቃ ከሆነ ይህንን ረሀብ ለመከላከል እንደ ተራ መስኖዎችን ጉድጓዶችን በመቆፈርና የእርሻ መሬትን በማጠጣት ምርትን ለማምረትና ሕዝብን ከረሀብ ለማዳን ይቻላል :: ይህንን በምሳሌ መመልከት ይቻላል :: በ1972 – 73 ዓ.ም አስራ አምስት ሀገሮች በድርቅ ሲመቱና ከእነዚህም ውስጥ ከአስያ ሀገሩ፣ በአፍሪካ ውስጥ የባህል አካባቢ ሀገሮችና ኢትዮጵያ በረሀብ ሲጎዱ፣ ከቦት ቢያልቀና በበዙ መቶ ሺህ ሰው ሲሞት ቻይናም እንደዚህ ዓይነት ድርቅ ነበረባት :: ተጽፎ እንዳየነው ከሆነ አንዱ አስረኛውም የቻይና መሬት ለድርቅ የተጋለጠ ነው :: ሆኖም ግን በቻይና ውስጥ ከሩቅ ድርቅ የደረሰበት አካባቢ በተከታታይ ለሶስት ዓመታት ያህል ከፍተኛ ምርት ሊያስገኝ ችሏል :: ሕዝቡም ከረሀብ ዳነ ::

እንግዲህ በጋች የዝናብን መምጣትና መቅረት ሊቆጣጠሩ ባይችሉም የማቴሪያል ሁኔታው ከፈቀደላቸው የዝናብ አለመምጣት ውጤት የሆነውን ድርቅን ሊከላከሉ ይችላሉ :: ይህንን ለማድረግ ካልቻሉ በየጊዜው ለረሀብ እየተጋለጡ፣ እየሞቱ፣ እየተሰደዱና ቤተሰቦቻቸው እየተበታተኑ ከትውልድ ትውልድ የኖረበት አምባ ምድር በየ



ሆና ይቀራል ::

ታዲያ ለድርቅ ፍልስፍና እንደዚሁ የተለየ ግምትና አስተሳሰብ ያለውን ያህል፣ ከከበርቴው ድርጅቶችና አስተዳደሮች የሚሰጡት "መፍትሔ" ለችግሩ በቂ መልስ ሊሆን አይችልም :: በሌላ አነጋገር፣ የዛሬውን በአፍሪካ የገባውን ረሀብ ለመከላከልና በሶስተኛው ዓለም የተንሰራፋውን ድህነት ለመቋቋም በእነ ዓለም ባንክና በሌሎች የሚለፈፈው፣ እነዚህ አገሮች ኢኮኖሚያቸውን ማሳደግ እንዳለባቸው ነው :: የሚያብራሩትም፣ በእነሱ ግምት የሶስተኛው ዓለም ሀገሮች በዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍል ውስጥ በሚገባ ቢገቡና የሚያመርቱትን ምርት ለዓለም አቀፍ ገበያ ቢያቀርቡ ነው ይላሉ :: በዚህም ሁኔታ የሚያድገው የተወሰነ ሴክተር ብቻ ነው :: ይህም ወደ ዕድገት ይመራችኋል ይላሉ :: በጥንቃቄ የቀመ ቲዎሪ/ፍልስፍናው ግን እንደዚህ መሆን የለበትም :: ምርት ለማን? ለምን? እንዴት ይመረታል? የሚለው መሆን አለበት :: የበዝባዦች ለመመገብ፣ ከአደጋ ለመከላከል፣ ጤንነቱ የተጓለ እንዲሆን ማድረግ፣ ለዚህም የሕዝቡን የምግብ ጥያቄ ለመፍታት የመሬትን ጥያቄና ሌላ የሀብት ጥያቄ እንደዚሁ ከዚህ ጋር የተያያዙትን የአገዛዝ መካከም መፍታትና የምርት መሣሪያዎችን በዚያው ማሻሻል፣ የተከማቸውን የሰው ጉልበት ከሀገር ጠቃሚ ባህልና ልምድ ጋር እያዛመዱ ሬሽናል በሆነ መንገድ መጠቀም ነው :: እንደዚህ ዓይነቱን ጥያቄና መፍትሔ እነ ዓለም ባንክ በፍጹም አያቀርቡም :: ፍላጎታቸው የተለየ እንደመሆኑ መጠን ሁሉ "መፍትሔያቸውም" በበጎ ቅስል ሳይ እንዉት ስደዱብት " ነው :: ዘር ዘር ረሀብና ድርቅ የፖለቲካ ጥያቄ እንደ መሆናቸው መጠን፣ በበዝባዦችና በተበዝባዦች መሀከል የሚደረግ ትግል እንደ መሆኑ መጠን፣ ልክ እንደ ኢኮኖሚ ዕድገት ቲዎሪና ፖሊሲ ከፍተኛ የርዕዮተ ዓለምና የመደብ ትግል የሚካሄድበት መድረክ ነው ::

## 3.0 ኮሎኒያሊዝም ለረሀብ ተጠያቂ ነው ::

### 3.1 ኮሎኒያሊዝም በባህል ሀገሮች ላይ ያደረሰው ጠንቅ

ኮሎኒያሊዝም በአፍሪካ ያመጣው ጠንቅ ቢታወቅ፣ ኮሎኒያሊዝም ከአፍሪካ ተባሮ ቀኝ ሀገሮች "ነጻነታቸውን ቢቀዳጁ" ከኮሎኒያሊዝም ጠንቅ ተላቀው ሕዝባቸውን በሚገባ መገበው ሀገራቸውን አበልጽገው ወደ ሥልጣኔ ሊያመሯቸው የሚችሉ

መንግሥታት በፍጹም አልተፈጠሩም ። እነዚህ አገሮች ወደ ድኅነት አመሩ ። ጥቂት የየሀገሮች መሪዎች የዓለም አቀፍ ካፒታሊዝም ጥሬ በመሆን ሕዝቦቻቸውን የሚያራቁቱ፣ ለረሐብ የሚያጋልጡ፣ ሰው የሚባለው ፍጡር የወጣን ያህል እንኳ እንዳይከበር አድርገው ጣሉት ። የተገለበጠች ዓለም!!

ኮሎኒያሊዝም በአፍሪካ ሲገባ በሀገሩ ሊያመርት የማይችለውንና አዚያው እየተመረተ ወደ እነዚህ አገሮች / Motherlands / የሚጋዘው የእርሻ ምርት ላይ እንዲያተኩሩ አስገደዳቸው ። ከኮሎኒያሊዝም በፊት ግን ይህን ያህልም ተጋና ባይታይም በጊዜው በነበራቸ ቴክኒክና ዕውቀት በመጠቀም የተፈጥሮን ሁኔታ በመገምገም ለምግብ የሚሆናቸውን እንደ ጤፍ፣ ስንዴ፣ ማሽላ፣ በቆሎ፣ ዘንጋዳ፣ ሥራ ሥሮች / underground roots / የመሳሰሉ ነገሮችን እያመረቱ እራሳቸውን ይመገቡ እንደ ነበር በታሪክ መጽሐፍት ውስጥ ተመዝግቦ ይገኛል ። ለምሳሌ ጋምቢያ ሩዝ በማብቀል የታወቀች ነበረች። ነገር ግን ኮሎኒያሊዝም ከገባ በኋላ በኦቾሎኒ ምርት ላይ እንድታተኩር ተገደደች ። እንደዚሁም ዳሆሜ፣ የዛሬይቱ ቤኒን የፓልም ዘይት፣ ታንዛንያ ታሏ በኋላ ደግሞ ትምባሆ፣ ዩጋንዳ በቡና፣ ጋና በካካዎ ምርት ላይ እንዲያተኩሩ ተገደዱ ።

ወደ ሳህል አካባቢ ሀገሮች ጋ ስንሄድ / ማሊ፣ የላይኛው ቮልታ፣ ቻድ... ወዘተ/ እንደዚሁ እነዚህም ሀገሮች ወደ ኦቾሎኒ ምርት ላይ አተኮሩ ። ትላልቅ የኦቾሎኒ ማምረቻ መስኮች ሲቋቋሙ፣ ትናንሽ ገበሬዎች በምግብ ምርት ላይ አትኩሮ እንዳያደርጉና የእነሱ ደመወዝተኛና ጥገኛ እንዲሆኑ ማንኛውም ዓይነት ተጽዕኖና ግፊት ያደርጉባቸው ነበር ። በዚህም ሁኔታ በእነዚህ ሀገሮች የነበሩት አረሽ ገበሬዎች ነጻነታቸውን ሸጠው የአንገላቷቸውን ገዢዎች ጥገኛና ኀሰበታቸውን ለእነዚህ ሸጠው የሚያደሩ ሆኑ ። ይህ ሁኔታ እያደገ በሄደ ቁጥር በአንዳንዱ አረሽ ገበሬዎች ላይ ይጫን የነበረው ቀረጥ በገንዘብ በተለይም በእንግሊዝ ፓውንድ፣ በፈረንሳይ ፍራንክ መከፈል ስለነበረበት፣ ገበሬዎቹ ለውጭ ገበያ በሚቀርቡ ምርቶች ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ተገደዱ ። ወይንም ኮሎኒያሊስቶች ያቋቋሟቸው ትላልቅ የእርሻ መስኮች ላይ ተቀጥረው እንዲሠሩ ተገደዱ ። ይህ ሁኔታ ለሰው ልጅ ቀን ተቀን በሚያስፈልጉት የምግብ ዓይነቶችና በውጭ ገበያ ቀርበው በኢንዱስትሪ ውስጥ በሚከናወኑት/processed/ ጥሬ ዕቃዎች መሀከል መዛባትን አስከተለ ። የኃለኛው የመጀመሪያውን ከቦታው እያስለቀ



ቀው በሄደ ቁጥር የገበሬዎች ጥገኛነት እያደገ፣ የአኗኗር ዘዴያቸው እየተሰጋጠ / በተበላሸ ሁኔታ / ባሕላዊ የአመጋገብ ዘዴአቸው እየተለወጠ በሰውነታቸው ላይ ጉዳትን፣ በሀገራቸው ላይ ያልተመጣጠነ ዕድገትና የውጭ ጥገኛ የሆነና በውጭ የሚበዘበዝ ሀገርን አተረፉ ። ለምሳሌ ድርቅን ለመቋቋም የሚችሉ በመሬት ውስጥ የሚበቅሉ ሥራማ ምግቦችና ሌሎች እንደ ማሽላና ዘንጋዳ ያሉ እህሎች ፊት ከነበራቸው ብዛት እየቀነሰ መጣ ። ከዚህም በላይ፣ የአውሮፓ ካፒታሊስቶች የዘመኑ ሳይንስ በሰጣቸው ዘዴ እየተጠቀሙ የሦስተኛውን ዓለም ምግቦች እየዘረፉ የምግቡን ዋና ይዘትና ከፍተኛ ጥቅም ያለውን / Gen / እየመጠጡ በመውሰድ የዓለምን የምግብ ሁኔታ መቆጣጠር ቻሉ ። ዛሬ በዓለም ምግብን የሚቆጣጠሩ ወይንም የእህል ሞኖፖል ያላቸው አምስት መልቲ ናሽናል / Multi Nationals / ኩባንያዎች ናቸው ። ይህ በእነዚህ የካፒታሊስት ኩባንያዎች የዓለም የእህልን የጂን ባንክ በቁጥጥራቸው ስር ማድረግ በሦስተኛው ዓለም ሀገሮች የነበሩትን የተለያዩ የጂን ዓይነቶችና ከፍተኛ ሬዚስታንስ ያላቸውን ቶሬቻው ከዱሮው ዝቅ እንዲል አደረጉ ። በሌላ ጎን ደግሞ ይህ ጂን በዓለም አቀፍ ደረጃ አንድ ዓይነት /uniformity / እየጋበዘ በመምጣቱ ለተለያዩ አደጋዎች ወይንም በሽታዎች በቀላሉ ለመጋለጥ ቻለ ። በሌላ አነጋገር፣ ከዚህ በፊት የተለያዩ ጂን ያላቸው የእህል ዓይነቶችና የተለያየ የተፈጥሮ መከላከያ / resistence / የነበራቸው ጂኖችና በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ ይበቅሉና ያድጉ የነበሩት አሁን በካፒታል ቁጥር ስለ ወደቁና አንድ ዓይነት መልክ እንዲይዙ በመደረጋቸው የተለያዩትን በሽታዎች የመከላከል ኃይላቸው እየቀነሰ መጣ ። ለዚህም በቀላሉ ለአደጋ ሲጋለጡ፣ በሌላ በኩል ደግሞ " የተሻለ ዘር " እየተባለ የሦስተኛው ዓለም ሀገሮች የካፒታሊስት ሀገሮች ጥገኞች እንዲሆኑ ተደረጉ ። ያም ሆነ ይህ ብዙዎቹ የሦስተኛው ዓለም ሀገሮች የብዙዎቹ እህሎች የመጀመሪያዎች አባቶቹ ሀገሮች ወይንም በእነዚህ ሀገሮች የተገኙ እንደሆኑ አንዳንዱ መጽሐፍት ያሳያሉ ። ለምሳሌ ገብስ፣ ስንዴ፣ ሽንኩርት፣ ሙዝ፣ በሊጥ፣ ቡና ቢትሩቶያና ሌሎች የሦስተኛው ዓለም ሀገሮች ለመጀመሪያ ጊዜ የበቀሉና የተራቡ ለመሆናቸው ይናገራሉ ። ይህም ማለት እነዚህ ሀገሮች በተፈጥሮ ደሀ አልነበሩም ማለት ነው ።

ሆኖም ገን ኮሎኒያሊዝም ወደ አፍሪካ ሲገባ እነኚሁ በቆኘ አገዛዝ ስር የወደቁት ሀገሮች የተፈጥሮን ሁኔታ እየገመቱና የእህል ማብቀል ዘዴያቸውን እያሻሻሉና እያዳቀሉ ያልኖሩትን ያህል፤ ይህን በብዙ ጊዜ ሰምዱና ሥራ የበበበቡትን ዕውቀት በኮሎኒያሊስቶች ሊገፈፉና ወደ ረሐብና ወደ ድንነት ሊገፈተፉ ችለዋል ::

በተጨማሪ ኮሎኒያሊዝም ያመጣው ጠንቅ እነዚህ ሀገሮች በውጭ ገበያ ላይ እንዲያተኩሩ ወይንም ለውጪ ገበያ የሚቀርቡ እህሎችን ብመረታ ቀጥር በሀገራቸው ውስጥ ሊያድግ ይችል የነበረው የንግድ ልውውጥ እየተቀጨ፤ የምርት ኃይሎች ዕድገት እየተገታ፤ በየሀገሩ ያሉት ሸማኔዎች፤ ቀጥቃጮች፤ ፋቂዎች፤ ሸክላ ሠሪዎች ...ወዘተ ዕድገታቸው እየተመታ ወደፊት መራመድ እንዳይችሉ ሆነ ::ከዚህም በላይ የአውሮፓ ሸቀጦች የእነዚህን ሀገሮች ገበያ በመውረር በሀገሩ የሚሠሩ የእጅ ጥበብ ሥራዎችን ከገበያ እየተሰናበቱ እንዲጋሙ በማድረግ፤ ከላይ የተጠቀሱትን ባለሙያዎች ወደ ተራ ኩሊነት፤ ዕድል የገጠማቸው ደግሞ በአውሮፓ አማካይነት በተቋቋሙት የማዕድን ማውጫና ሌሎች ፋብሪካዎች ውስጥ ተቀጥረው ወደ ተራ ወዝደርነት ተቀየሩ :: ይሁንና ገን እነዚህ አዲሲ የተቋቋሙት ኢንዱስትሪዎች ይህንን ያሕል ለእነዚህ ሀገሮች የሥራ መስክ ሊከፍቱ አልቻሉም :: ዕድገትን አላመጡም ::በመሆኑም ቀስ በቀስ ማንቀሙን በረገጠው የኮሎኒያል ገኑኝነትና በሀገሬው ከበርቴዎች ከመሬቱ እየተፈናቀለ የተባረረው ገበሬ ወደ ከተማዎች ሥራ ለመፈለግ መጣ :: የከተማዎች ሕዝብ በዛት በቁጥር እየጨመረ መጣ :: ሥራ ፈላጊና የሥራ ቦታ መፍጠር ሽመሩ :: ነገር ገን የሥራ መስኩ በጣም ጠባብ ስለነበር እነዚህ ሥራ ፈላጊዎች ካለ ሥራ ቀሩ ::ብዙዎቹ አረባቸውን ለማሸነፍ ወንጀኞች ወደ ኩሊነት፤ ቤቶች ወደ ቤተኛ አዳሪነት፤ እንዲሁም ሌላው ወደ ሌላ ሙያ ተበማሩ :: በዚህም አዲስ የኅብረተሰብ ገኑኝነት ተፈጠረ :: እነዚህ ቡድኖች / የኅብረተሰብ ክፍሎች / ገበያቸው በጣም ዝቅተኛ ስለነበረና ስለሆነ አረባቸውን ሊመገቡ አልቻሉም :: ሀገሬቸውም ወደ አዲስ የሥራ ክፍፍል ውስጥ በመሸጋገሯ የእህልና የማንኛውም ነገር ቀገኛ ሆነች ::ድንነትና ረሐብ በከተሞች ባይቀር ነገሡ ::



3.2 ከኮሎኒያሊዝም በኋላ

የአውሮፓ ኮሎኒያሊስቶች ከአፍሪካ ይባረሩ እንጂ አዲስ ነጻ የወጡ ሀገሮች በአገሬቸው የሙው ሕዝባቸውን መልኪና ሥርዓት ባለው መንገድ ሊያስተዳድሩ፤ ሊመገቡ ፤ የሥራ መስክ ሊከፍቱ...ወዘተ አልቻሉም ::

ኮሎኒያሊዝም ከአፍሪካ ሲባረር በተዘዋዋሪ እነዚህን ሀገሮች የሚበዘብዙትን መሣሪያዎች አዘጋጅቶና አደራጅቶ እንጂ እንዲያው ዝም ብሎ አልወጣም :: በመጀመሪያ በኮሎኒያሊዝም ዘመን የተመሠረተው አስተዳደር ውስጥ ቡድኖችን በአሮ አምባል መኮትኮትና ማበልጠን ቻለ :: አዲስ የገዥ መደብና የኅብረተሰብ ክፍል ከሀገሬው ተራ ሕዝብ፤ በኢኮኖሚ በፖለቲካና በማኅበራዊ ስታተሱ በሳይኮሎጂካል ሜክ አፕ/ psycological make up / የተለየ፤ እንገዳ የሆነን ፍጡር አዘጋጅቶ ነው የወጣው :: በተጨማሪም ካፒታል በ19ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ዓለም አቀፋዊ መልክ እየያዘ ሲመጣ፤ አዲስ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በእሱ አምባል ማምረት / reproduce / ቻለ :: ይህ ሁኔታ ለካፒታል የበለጠ ምቹ ሁኔታን ፈጠረለት :: በርዕዮተ ዓለም፤ በፖለቲካ፤ በኢኮኖሚና በባህል እየበረገ በገባ ቀጥር እነዚህን ሀገሮች በሬሱ ሥር ጥገኛ ማድረጉን የበለጠ ተረዳው :: የኮሎኒያል ስታተሱን አጥቶ ሲባረር ይህንን ያህልም ጥቅሙን አልተገፈፈም ማለት ነው :: በተያያዘው ገን ባሙቸው ሁኔታ ሁሉ በመገባት በትምህርት፤ በባይንስ፤ በቴክኖሎጂ ...ወዘተ እነዚህን ሀገሮች ጠመዳቸው ትምህርት ዓለም አቀፍ ለካፒታል _ Capital is a social relationship ብሎም ቸ መንገድ ይበልጥ ተያያዥና ተጠናቀር ወጣ :: የአሜሪካን የትምህርት ሥርዓት፤ የእንግሊዝን፤ የፈረንሳይን የትምህርት ሥርዓት ዓለም አቀፍአዊ ጠባይ ያዙ ::በአሜሪካንና በሶስተኛው ዓለም ዩኒቨርሲቲዎች የሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች ከዩኒቨርሲቲዎቻቸው በስተቀር አበዛም የሚለዩበት ነገር የለም :: ነገር ገን የትምህርት ዓይነት አንዱ መሆኑ አይደለም :: የሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች ርዕዮተ ዓለማዊ ጠባይ ስላላቸውና ከፍተኛ የርዕዮተ ዓለም ትገል የሚካሄድባቸው መድረኮች እንደመሆናቸው መጠን አውነትን ለመረዳት ለመተንተንና ከዚያም ለችግሩችን ባይገባ መፍትሔ ለመስጠት የማይችሉ ሆኑ ::

በሌላ አነጋገር ከየሀገሮቹ ባህል፣ታሪክ ከበጀቶች አፈጻጸምና የጎሌና አስተባ በበ ጋር ተጠንተውና ተቀናጅተው የተዘጋጁ ባለመሆናቸው ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው አመዘነ ። በአውሮፓ የትምህርት ሥርዓት አማካይነት የሠለጠኑት ምሁሮች የሚያጋጩት የኢኮኖሚ ፖሊሲ የሕዝቦችን ችግር የሚፈታ፣ የምርት ኃይሎችን ዕድገት የሚያገዝ ባይሆን ቀረ ። ኢኮኖሚ ለምንና ለማን የሚለው እስ ተባበር ቀርቶ የኢኮኖሚ "ዕድገት " /Economic growth / በዚህን ያህል ፐርሰንት ማደግ አለበት የሚለው ፍልስፍና ነገሰ ።

የአውሮፓና የአሜሪካን ካፒታል በእነዚህ ሀገሮች የበላይነትን ቢቀዳጅ በእነዚህ "ምሁሮች" / ቢሮክራቶችና ቴክኖክራቶች / ብቻ አይደለም ። በእየሀገሩ ያለው ሥርዓተ ማኅበር አመቺ ሁኔታን ስለፈጠረለት ነው ። በምርት ኃይሎችና በምርት ግንኙነቶች መሀከል ያለው ልዩነት የበለጠ ገልጾ ሆና ባለመውጣቱ ነው ። በሌላ አነጋገር የበስተኛው ዓለም መንግሥታት ከምርት ኃይሎች / መሬት፣ የኢንዱስትሪ መኪና፣...ወዘተ / ጋር የበለጠ የተያያዙ / intact / በመሆናቸው ነው ። ለምሳሌ በኢትዮጵያችን ኃይለ ሥላሴ ቤተሰቦች እንኳም ሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣኖች እንደየደረጃቸው የመሬት ከበርቴዎችና የአንዳንዱ ፋብሪካ ባለቤቶች ነበሩ ። በመሆኑም ለምርት ኃይሎች ዕንቅፋት ሆኑ ። የምርት ኃይሎችን ለማበ ደግ የሚጋበቅት ከረጅም አልነበረም ። በአንጻሩግን ፎቅ ቤቶችን ማሠራት፣ ዘመናዊ መኪናዎችንና ሌሎች ሸቀጣሸቀጦችን ማስመጣት፣ ውጪ ሀገር ገንዘብ ማስቀመጥ፣ በፈረ ድግሶችን መደገስ ሙያቸው ሆነ ። በሌላ በኩል ግን ሊያድግ ይችል የነበረው የብሔ ራዊ " ከበርቴ " በአውሮፓ ካፒታልና በየሀገሩ መንግሥታት አማካይነት ተጽዕኖ ደረሰበት ። ሊያድግ ባይችል ቀርቶ ተኮላሸ ። ከብሔራዊ መደብነቱ ይልቅ ሸቀጥ አስ መጪና ሻጪ ፣ በየሀገሩ የሚመረትን እንደ ቡና፣ ከክስ፣ ስኳር ...ወዘተ ለዓ ለም ገበያ አቅራቢ የሆነ መደብ / Compradour Bourgeosie /ሆነ ። በዚህም ታሪካዊ ሚናውን ሊሸከም የማይችል መደብ ሆነ ። ጥገኛ እንጂ በራሱ የሚ ጓዝ መደብ ባይሆን ቀረ ።

ይህ ሁኔታ ማጠቃለል ባይቻልምና እያንዳንዱ ሀገር የራሱ ልዩ ጠባይ ቢኖረ ውም እነዚህ ሀገሮች ለዕድገት በሚበጁቸው ነገሮች ላይ እንዳያተኩሩ አግዷቸው ።



አፈባቸውን መመገብ የማይችሉ ሆኑ ።በተቃራኒው ግን ለምግብ የሚሆኑ ወስኮች እየተወገዱ ቡና፣ ካካዎ፣ ትምባሆ፣ አቮካዶ፣...ወዘተ ማምረቻ ሆኑ ። እነዚህ የእርሻ ምርቶች ለውጪ ገበያና ለጥሬ ገንዘብ /Hard currency / ማገኛ ተብለው ስለሚመረቱ ለሌላ ምግብ ማፍሪያ ሊውል የሚችል የሰው ኃይል / የሰለጠነ /፣ የቴክኒካልና የገንዘብ ኃይል በአንዱ አቅጣጫ ላይ ተሰማራ ። እነዚህ ለሕዝባቸው በቂ ምግብ ማምረት ያልቻሉት ሀገሮችም የግዴታ ቢያንስ ለከተማው ሕዝብ ገበያ ላይ ማቅረብ ስለአለባቸው ምግብ ከውጪ ለማስመጣት ተገደዱ ። ይህም የግዴታ በጥሬ ገንዘብ መከፈል ስለአለበት የበለጠ ጥሬ ገንዘብ እየጠየቀ፣ ምግብንና ሌሎች ሸቀጣሸቀጦችን ከውጪ ባስመጡ ቁጥር፣ ለውጪ የሚያቀርቡት የእርሻ ምርት ዋጋው ታችና ላይ /fluctuate / ስለሚሉ የንግድ ሚዛናቸው ይበልጥ እየተበላሸ መጣ ። ይህ ሁለት ነገሮችን አመጣ ። የመጀመሪያው ለውጪ ገበያ የሚያቀርቡትን ምርት ለማምረትና የእርሻ መስኩን ለማስፋፋት ከውጪ፣ እንደ ትራክተር፣ ማዳበሪያ ...ወዘተ የመሳሰሉትን ባስመጡ ቁጥር ከውጪ ንግዱ የሚያገኙት ገቢ ስለማይበቃቸው የግዴታ በዶላር ውስጥ እንዲገቡ ተገደዱ ። ይህንኑ በዶላር የሚወስዱት / የሚያገኙት / ዕዳም የተወሰኑ ሁኔታዎችን ኒያሟሉ ነው ።በዚያው ለውጪ ገበያ በሚቀርብ የእርሻ መስክ ላይ ማተኮሩ ብቻ ነው፣ምክንያቱም ዕዳና ወለዱ የሚከፈለው በየሀገሩ ገንዘብ ሳይሆን በዶላር ስለሆነ ነው ። ሁለተኛም የንግዱ ሚዛናቸው በተለይም በጠቅላላው የውጪ ክፍያ ሚዛናቸው /Balance of payment / በዚህ የሥራ ክፍል በመበላሸቱ ይህንን ለማስተካከል የዓለም አቀፍ የገንዘብ ፈንዱ /IMF /ባለው " ኃላፊነት " መሠረት ሚዛኑን ለማስተካከል የግዴታ የተወሰኑ ግዴታዎች ማሟላት አለባቸው ። ከውስጥ መንግሥታት፣ ከውጪ የሚያስመጡትን ምግብ የሚደጉሙትን /subsidize / እንዲተውና እንደዚሁ ለውጪ ገበያ በሚቀርቡ ምርቶች ላይ እንዲያተኩሩ መሆን አለባቸው ። ይህ የየሀገሬው ሕዝብ የምግብ ዋጋ እየተወደደበት በሬው ሕዝብ ምግብን ገዝቶ መመገብ ወደማይችልበት ሁኔታ እንዲወድቅ ተደረገ ። በሌላ ወገን ደግሞ መንግሥታት ከውጪ የሚያመጡትን ምግብ ይህም ሆነ ቢደጉሙ፣ ይህ ድጎማ / subsidization / በተጨማሪ ለሌላ የዕድገት መስክ ሊውል የሚችለው የበጀት ክፍል በዚህ በየጊዜው እያደገ በሚሄደው ድጎማ ስለሚነጠቅ ነገሩ የዙሪያ ጥምጥም ሆነ ። ይህ የየመንግሥታቱ በጀት በሁለት እንጻሮች ይበ

ረብር ጀምር :: የመጀመሪያው በየዓመቱ እያደገ ለሚሄደው የውጪ ዕዳ ክፍያ / Debt service / ቢሆን፣ ሌላው ደግሞ መንግሥታቱ ከራሳቸው ማምረት የማይችሉትን ምግብ ከውጪ ስለሚያስመጡና /Import / ይህ በንግድ ላይ ሃጋው በጣም እንዳይገር ዱጎጫ ማድረግ ስለአለባቸው ከእነዚህ ሁለት አቅጣጫዎች ለዕድገት የሚውለው ገቢ ከፍኛ ይበረበራል ::

እንግዲህ ዛሬ ስለ ረሀብ ሲወራ ከዚህ ውስብስብ ሁኔታ ውስጥ ጥቂቱ ነገሩን ነቅሶ ማየት በፍጹም አይቻልም :: እንደዚህ ሆኖ ሁኔታው በመጠኑ ቢሆን ካልታየና ይህንን መፍትሄ ካልተቻለ በቂ መፍትሔ ለመስጠት አይቻልም :: በሌላ በኩል ግን የእንዱን ችግር ምንነት መረዳት ብቻ በራሱ በቂ አይደለም :: ይህ ቢሆንማ ኖሮ የዓለም ሕዝብ መፍትሔ ባገኘ ነበር :: የነገሩን ፍሬ ከመረዳት ላይ ባይሆን የመለወጡ ላይ ነው :: ለምሳሌ በዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍል ውስጥ ብዙ የሦስተኛው ዓለም ሀገሮች ለዓለም ገበያ የሚያቀርቡት ምርት እየረከሰ፣ እንዱ የኢንዱስትሪ ምርት ለመግዛት በፈለጉ ቁጥር ደግሞ ዋጋው እየጨመረ — እንግዲህ ባለው የዘመኑ ቴክኒክ የምርት ማምረቻ ዋጋ /Production cost/ ቀንሶ ሳለ ነው — መሄዱ ሲታወቅና የነገሩ ሚዛናቸው እየተበላሸ ሲሄድ ለምን የየሀገሩ መንግሥታት ከዚህ ሁኔታ ተላቀው ለሀገራቸው ዕድገት የሚሆን እርምጃዎችን አይወስዱም :: ጋይንም ደግሞ ሕዝቦችን ለመግበር የሚያስችሏቸውን የእርሻ ምርት አያበዙም :: አያስፋፉም :: ይህ ፖሊሲስ ይመስላል :: ይህንን ለመረዳት በዓለም አቀፍ ደረጃ የተሳሰረውን ቁሥልጣን በነበለት መረዳት ያስፈልጋል ::

ከዚህ ቀደም ተብሎ እንደተጠቀሰው ከ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ ካፒታሊዝም ዓለም አቀፋዊ መልክ ይዞ እንደመጣና በእሱ አምሳል ሰዎችን ማምረት እንደቻለ ወይንም ደግሞ የእሱን ፍላጎት / Interesst / የሚጠብቁትን ማዘጋጀት እንደቻለ ነው :: ካፒታል ከሀገሩ ገበያ ውጭ የሚያመርታቸውን ምርቶች ለሽያጭ ሲፈልግና ያረጁ የምርት መሣሪያዎችን በሦስተኛው ዓለም ሀገሮች ውስጥ እያቋቋመ በርካሽ የጉልበት ዋጋና የቀረ ሀብት ምርት እንዲመረት ሲያደርግ የሀገሩ ገበያ ስለጠበበው ባይሆን የተሻለ የትርፍ ማትረፊያ ገበያ / market outlets for a better varolization of Capital/ ስለሚፈልግ ነው ::



የካፒታሊስት ስልተ ምርት ወይንም የምርት ክንውን በመጀመሪያ ደረጃ የሰውን ፍላጎት ለማርካት ባይሆን የሚመረተው ሸጦ ዓላማው ትርፍን ለማትረፍ ነው :: ይህንን ለማድረግ ደግሞ የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ንጹሕ የአሠራር እርምጃዎች ማለት፣ የአሠራር ውድድር ብቻ ባይሆን ርዕዮተ ዓለም — የሰውን ጭንቅላት መስለብ፣ ሰዎች ጠልቀው እንዳያስቡና እንዲወራረሩ በማድረግ፣ የሰዎች ግኙኝነት ንጹሕ የገንዘብ ግኙኝነት ብቻ እንዲሆንና ገንዘብ ያለው ሁሉን ሊያደርግ ይችላል የሚለው ፍልስፍና በሰዎች ጭንቅላት ስር እንዲገባ በማድረግ፣ በማስሚዲያና በማስታወቂያ / Advertisment / በመጠቀምና በማደንዘዝ ሰውን ኢሰብአዊ ሲያደርገው ጭምር ነው :: የእነዚህን መሠረት የሆነውን የሀብት ቀያቂ ለመጠበቅ ፖሊሲና አልፎም በኃይል ቀዩና የአድሚኒስትሬሽን እርምጃዎች ሲያደርግ ነው :: ይህንን የአሠራር ፍላጎቱን ለመጠበቅና ትርፍን በከፍተኛ ደረጃ ለማካበት በሚደረገው ውድድር በሀገር ውስጥና ከሀገር ውንበር አልፎም ኢንስቲቲሽኖችን፣ ሰዎችን በእሱ አምሳል ይኮተኩታቸዋል ::ለእሱ የዘበዛ በሚስማማ መሠረት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን፣ የአሠራር ዘዴዎችን በየጊዜው ይፈጥራል :: ለትርፍ ማካበቻ ብቻ ባይሆን ባይገበና ቴክኖሎጂን፣ አዳዲስ የአሠራር ዘዴዎች እንደ አገዛዝ መካኒዝም / Power mechanism / ይጠቀምባቸዋል :: እነዚህን የአሠራር ዘዴዎች ሊያውቁት የሚችሉትና የሚጠቀሙበት በእሱ አምሳል የተፈጠሩትና የሱ አፈቀላጤዎች ብቻ ናቸው ::

ይህ ትርፍን ለማካበትና የአገዛዝ መካኒዝምን ለመጠበቅ በዓለም አቀፍ ደረጃም ትግል ያደርጋል :: በዚህ በሚያደርገው ትግል፣ በየትምህርት ቤቱ በሚሰጠው ትምህርት የሦስተኛው ዓለም ሕዝቦች ለዚህ አገዛዝ መካኒዝም ተቀባይና አገልጋይ ሆነው እንዲሠሩ ትምህርቱ ከርዕዮተዓለም ጋር ተደባልቆ ሲመረመሩ በማይችሉበት መልክ እየተፈተፈተ ይሰጣቸዋል :: በሌላ ወገንም በዚያው በሦስተኛው ዓለም ውስጥ ለካፒታል በሚያመች መንገድ የተገነባው የትምህርት ዓይነት እንደዚሁ ሰዎችን እየፈለፈለ ያወጣል :: ከዚህም በላይ በየሀገሩ ባሉት ኢንስቲቲዩሽን ውስጥ ያሉትን

ሰዎች በጥቅም አያባለጋቸው ተጽዕኖውን ያባዱራል :: በጥቅም መሳሳባቸውን እንዲገነዘቡት ያስተምራቸዋል :: በቢሮክራሲው ውስጥ፣ በዕርዳታ መስክ፣ በፖሊስና በፀጥታ ውስጥ፣ በወታደሩ ውስጥ ሁሉ እየገባ ሰዎችን በማበልጠን የጥቅምና የአገዛዙ ጠበቂ ሆነው ወሳኝ መሣሪያዎችና አሩኞች ይሆናሉ ::በዚህ ዓይነት መልክ የተገነቡት ሰዎች፣ ኢንስቲትዩሽኖች ለዓለም አቀፍ ካፒታሊዝም የበዝበዛ መንገዱ ይጠርጉለታል :: ቦታ እየቀየሩና እያዘጋጁ ይሰጡታል ::ከላይ በተባለው የአሠራር ዘዴ እንዲተበትቡቸውና ሰፊው የየሀገሬው ሕዝብ ደሀና ረሀብተኛ እንዲሆን የዘለዓለም ጥገኛ እንዲሆን ያደርጉታል ::

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት፣ ካፒታል የሶስተኛውን ዓለም ሀገሮች የሚበዘ በዝባቸው መሠረታዊ መንገዶች በሆኑ ይህንን ለመጠቀም በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢንስቲትዩሽኖችና ድርጅቶችን መሰርቶ ነው :: እነዚህም የዓለም ባንክ፣ የዓለም አቀፍ የገንዘብ ፍንድ /IMF /፣ የምግብና የእርሻ ድርጅት /FAO /... ወዘተ ናቸው :: እነዚህ በዓለም አቀፍ ካፒታሊዝም ማለትም በአሜሪካን፣ በእንግሊዝ፣በፈረንሳይና በጀርመን ቁጥጥር ስር የተያዙ ናቸው :: ሌሎች የሶስተኛው ዓለም ሀገሮች የእነዚህ ድርጅቶች አባላት ቢሆኑም በተጨባጭ ቢታይ ምንም ኃይል የሳቸውም :: ከላይ የተጠቀሱት የካፒታሊስት ሀገሮች ድምፅ የበላይነት የበሬን በትና አወያየሩም ለእነሱ እንደሚያመች ሆና ነው :: እነዚህ ድርጅቶች ደግሞ ከተለያዩ ባንኮችና /private Banks / ከኢንዱስትሪዎች ጋር በሽህ ድሮች ተሳስረዋል :: በመሆኑም የእነዚህን ባንኮችና የካፒታሊስት ሀገሮች ጥቅም ለመጠበቅና የሶስተኛው ዓለም ሀገሮች የሚበዘበዙበትን የአሠራር ዘዴ የፕሮጀክት ፕላን /project planing & feasibility studies / በማውጣት በሚገባቸው ሀገሮች በሙሉ በካፒታሊስት ሀገሮች የሚመረቱት ምርቶች አዚያው እንዲረገሩና የሚደጎሙት ፕሮጀክቶች በቀጥታ ከካፒታሊስት ሀገሮች ጋር እንዲያያዙ በማድረግ፤ በተጨማሪም የሶስተኛው ዓለም ሀገሮች ለውጪ ገበያ በሚቀርቡ ነገሮች ላይ እንዲሰለጥኑ በማድረግ ወይንም ደግሞ በባንኩ አማካይነት የተወሰኑ አካባቢዎችና የኀብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ፣ ሌላውን የኀብረተሰብ ክፍል ያደኽዩና የሚያደኽዩ ድርጅት ነው :: የዓለም አየቀፍ የገንዘብ ፍንድ ከዚህ ቀደም በሉ በተጠቀሰው መሠረት መንግሥታት የማይሆን ፖሊሲ እንዲያወጡ በማ



ድረግና ሀብት ከሶስተኛው ዓለም በወለድ አማካይነት በእርሻ ምርቶች ላይ በሚወነው ዝቅተኛ የዓለም ገበያ ዋጋ አማካይነት፣...ወዘተ እንዲተላለፍ በማድረግ ለሰፊው የሶስተኛው ዓለም ኅብረተሰብ ድህነትንና ረሐብን እያቀመሙትና እየተፈወቀበት ነው ::

ይህ ከላይ የተጠቀሰው ነገር ለእነዚህ ሀገሮች ድህነትን በሙሉ ረሐብን ሲያመጣ፣ በተጨማሪም በየሀገሩ በዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴዎች ለአውሮፓ ገበያና ለከተማው በላተኛ ሕዝብ የተስፋፉት እርሻዎች በሰፊው ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ጉዳትን አምጥተዋል :: የእርሻ ማባዎች የሚታረሱት ለአውሮፓ አየርና መሬት ታስበው በተበሩ ትራክተሮች ስለሆነ እነዚህ ለመሬቱ መሸርሸር በሙሉ ለምርት መቀነስ አስተዋጽኦ አድርገዋል :: ይህ አዲስ ቴክኖሎጂ መስፋፋት ደግሞ በዚያው መጠን አረሾ ገበሬዎች ከቦታቸው አየገፋቸው አንደ መሄዱ መጠን የሰዎች በተወሰኑ አካባቢዎች መከማቸትና ያንን አካባቢ አየመሳሰሉ ማረስ ልምድና ግዴታ ሆነ :: ይህም ለምርት መቀነስ በበኩሉ ምክንያት ሆነ :: ከዚህም በላይ በእነዚህ ሀገሮች እንደዚሁ የሰው ኑሮ በቀጥታ ከአንጠት ጋር የተያያዘ እንደመሆኑ መጠን ዛፍን በቆረጡ ቁጥር ደን እየጠፋ፣ ዝናብ እየቀረ፣ አየሩ እየደረቀ፣መሬቱ እየተሸረሸረ፣ ለምሳሌ አፈር በነፋስ እየተወሰደ ለዝናብ አለመምጣት በሙሉ ለድርቅ መሰረን ምክንያት ሆነ :: እነዚህ ሁኔታዎች ተደማምረው ይበልጥ በተፈጥሮ ጥገኛ በሆነው፣ በዝናብ መምጣትና አለመምጣት የሚተማመነው ገበሬ፣ ዝናብ በቀረ ቁጥር ሊያርስ አልቻለም :: ይህ ሁኔታ አየተጠለ ሲሄድ ለድርቅና ለረሐብ መጋለጥ ዐጣው ሆነ ::

## 4.0 የኢትዮጵያ ረሐብ ምክንያት ምንጭ ::

በዙሪያችን በምናወራበት፣ በምንጽፍበት ጊዜ ከጥቂቶች በስተቀር ለኢትዮጵያ ረሐብ ዋናው ምክንያት ፖለቲካና ድርቅ እንደሆነና ድርቁን በሁለተኛ ደረጃ በማስቀመጥ ነው፤ ሌሎቻችን ደግሞ ድርቅ ብቻ ነው ለረሐቡ ዋናው ምክንያት የሚል ነው :: ባለፉት ገጾች ውስጥ ድርቅ ለረሐብ አንድ ምክንያት ሆኖ ሊቀርብ እንደማይችል ተረድተናል:: ድርቅ የዝናብ አለመዘነብ ውጤት እንደመሆኑ መጠን ይህንን ውጤት ሰዎች እንዳንዱ ነገሮች ካሳበሯቸው በስተቀር ለመቋቋም እንደሚችሉ አመልክተናል :: እንግዲህ የኢትዮጵያ ረሐብ ዋናው ምክንያት ፖለቲካ ብቻ ነው በሚለው የምንስማማ ከሆነ የኢትዮጵያ ሁኔታ የራሱ ጠባይ ስላለው በቀኝ አገዛዝ ስር ሲማቀቁ በነበሩት በሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ዓይን ልናየው አንችልም :: ይሁንና ግን በእጅ አዙር ቀኝ አገዛዝ ስር ስትማቀቅ የነበረችና ዛሬም ያለች ሀገር ለመሆኗ ገልጽ ነው :: የዚህም ውጤት ምን እንደነበረና እንደሆነ በተለያዩ ጊዜያት በታጠቁ፣ በትግላችንና በሌሎች የተማሪ ማኅበራት መጽሔቶች በሰፊው ተብራርቷል ::

የኢትዮጵያ ሁኔታ ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ልዩ የሚያደርገው የፊውዳሉ ሥርዐት ለረጅም ጊዜ መቆየቱና ይህም ለሀገሪቱ ዕድገት እንቅፋት ሆኖ እንደነበር ገልጽ ነው :: የፊውዳሉ ስርአት ሲባል ከዚህ ስርዓት ጋር የተያያዙ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ርዕዮተ ዓለማዊ / ሐይማኖት /፣ ባሕላዊ... ወዘተ ማለታችን ነው :: በኢትዮጵያ ውስጥ እንደዚሁ በአጠቃላይ የፊውዳሉ ስርዓት አለ ይባል እንጂ፣ ይህ አጠቃላይ መልኩ ብቻ ነበር :: ይበልጥ ለመረዳት የመሬት ስሪትን በመጠኑም ቢሆን መረዳትና ይህም ምን ያህል በምርትና በምርት ኃይሎች ዕድገት ላይ ያመጣውን አሉታዊ ነጥብ ማየት ያስፈልጋል :: ለዚህም በደቡብና በሰሜን የነበረውን የመሬት ስሪት መመርመር ያስፈልጋል ::

### 4.1 የደቡቡ ሁኔታ በምርት ዕድገት ያለው አሉታዊ ውጤት አጠቃላይ መልኩ

ከምኒልክ ወደ ደቡብ መስፋፋት በፊት የፊውዳሉ ስርአት ይህንን ያህልም



የተስፋፋ ስርዓት አልነበረም :: በ17ኛው ምዕተ ዓመትና በ18ኛው ክፍለ ዘመን በዚሁ አካባቢ በአንዳንዱ ቦታዎች የፊውዳሉ ስርዓት ቀስ በቀስ ስር እየሰደደና ከዚያ በፊት የነበረውን ኢጋሊቴሪያንና የቲሪቡን የምርት ግንኙነት / Tributary mode of Production / እያጠፋውና እየተካው እንደመጣ የታሪክ መጽሐፍት ያረጋግጣሉ :: ከ1860 ዓ.ም ወዲህም በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ ምኒልክ ወደዚያ አካባቢ ሲዘምቱ የምርት ግንኙነቱ በመለወጥ አዲስ ዓይነት የኅብረተሰብ ግንኙነት / Social-relationship / እንዲመሠረት አድርጓል :: በጉልበት ያስለቀቋቸውንና ያለብዙ ትግል ያስገበሯቸው ቦታዎች ለጦር አለቆችና በየቦታው በተመሠረቱት የአስተዳደር ቦታዎች መሬት " ከፋፈለ " እነዚህ የጦር አለቆች እንደየሹመታቸውና እንደየማዕረጋቸው መሬት እየተበረከላቸው ገባሮች እየተሰጧቸው የአገዛዙ መሠረት ሆኑ :: ይህ የመሬት ይዞታ ጉልት በመባል ይታወቃል :: ሌሎች በማዕረጋቸው ዝቅ ያሉትና በወታደርነትና በአስተዳደር ሥራ ውስጥ ለሚያገለግሉት የደመወዝ ጠባይ ያለው የማደሪያ መሬት የሚባል ተሰጣቸው :: በሌላ በኩል የምኒልክን ጦር ከፍተኛ ተቃውሞ ባያሳዩ የነበሩት የሀገሬው ባላባቶች ከቀድሞው ይዞታቸው አንዱ ሶስተኛው ብቻ በይዞታቸው ስር ቀረ :: ይህ ሁኔታ በምኒልክና በእነዚህ ባላባቶች መሀከል መግባባትና እርቅ እንዲፈጠር የተደረገ ፖሊሲ ነበር :: ቤተክርስቲያንም የዚህ ድልድል ተካፋይ ነበረች :: ቤተክርስቲያን በተቆረቆረበት ቦታ ሁሉ የቤተክርስቲያን መሬት እየተባለ ለካህናትና ለዲያቆናት የተደለደለው መሬት ቁጥር ስፍር የለውም ::

ያም ሆነ ይህ የመሬት " አደላደል " የፊውዳሉን ስልተ ምርት በአዲስ ፍርም አስፋፋ :: ከዚህ በፊት ተበጣጥሮ፣ በተለያዩና በትናንሽ የሀገሬው ነገሥታት / Kingdoms / ባላባቶች ይገዙና ይበዘበዙ የነበረው የሀገሬው ገበሬ ወደ ሌላ ግንኙነት ተለወጠ :: አጠቃላይ የሆነ የፊውዳል ስልተ ምርት በደቡብ ሕዝብ ላይ ተጫነ :: ከዚህ በፊትም እስከ ተወሰነ ደረጃ ድረስ " ነጻ " የነበሩ ገበሬዎች ከሰሜን በመጡ ሰዎች ቁጥጥር ስር በመውደቅ የእነሱ አሽከር ሆኑ :: የዚህ አዲስ የባላባትና የጭሰኛነት ግንኙነት አስከፊነቱ ገበሬው መሬቱን እያረሰ ለባላባቱ ምርቱን ብቻ የሚያካፍል አልነበረም :: ከገጠር፣ ባላባቶች እስከ ሚኖሩበት ቦታ ድረስ እንጨት፣ ውሃ እንዲሁም ሌሎች ነገሮችን እየተሸከመ በመው

በዱና ሌሎች አገልጋዮቶች በማበርከት የአቶና አቶና ይበዘበዙ ነበር ። በአ ንጻሩ ግን የባላባቱ ወገን የአስተረረሱን ዘዴ ለማሻሻል፣ ምርት እንዲያድግና የገበሬውን ችግር ለማቃለል የሚወስደው እርምጃ በፍጹም አልነበረም ። በዚያው ባለው ተደስቶ የሚኖር ወገን ነበር ። በዚህም በባላባቱ እጅ ተይዞ ባይታረስ የሚያዩረው መሬትም በዙ ጋሻ ነበር ። ይህ ሁኔታ በፍጹም ምርትን አያባዱግም፣ የመፍጠር ችሎታን አያዳበርም፣ የምርት ኃይሎችን አያስፋፋም ነበር ። የገበሬው ወገንም ከምርቱ በዙ ስለሚወስዱበትና በተለያዩ ዘዴዎች ስለሚበዘበዙ አራሱንና ቤተሰቦቹን እስከ ማረፍት ይደርስ ነበር ። በዚህም አራሱንና ቤተሰቦቹን በሚ ገባ ለመገብ የማይችል እንደመሆኑ መጠን፣ ሌሎች አራሱ የሚያመርታቸውን ነገ ሮች እንደ ሳምባ፣ የእጅ ባትሪ፣ ጨው፣ ክብሪት ፣... ወዘተ የመሳሰሉትን ካብቶቹ ለመግዛት የሚችለው ከሚቀምሰውና ከሚጎርሰው ቀንሶ እንጂ በበቂው እምርቶ ወይንም ከመረተው የበለጠ ደርሶት አልነበረም ። ይህም ሁኔታ የማይቻል ከሆነ አራጣ በመበደር የባሰ መራቆትና መደኽየት ውስጥ ይገባ ነበር ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የኃደተው አብዛኛው የደሐ ገበሬ የምርት መሣሪያዎችን አያሻሽል፣ መሬቱን አያዳብረና አየለዋወጠ ማረስ ቀርቶ አራሱን እንኳ በበቂው መገብ አይ ችልም ነበር ። ከምፈር፣ ቀንበርና በሬ ጋር ለአገሩ መከላከያ ባይኖረው ለብ ርዱና ለውርጭ ተጋልጠ በሌሊት ከቤቱ አየወጣ ኑሮውን ለማሸነፍ የሚጣጣረው ገበሬ ኑሮው እጅግ አሰቃቂ ነበር ።

የደሐ ገበሬ አራሱንና ቤተሰቦቹን አሸንፍ ቢኖር የተለየ የምግብ ልም- ዱና አይደር በማዳበሩ ነበር እንጂ ያመረታቸውን እንደ ስንዴ፣ ጤፍ፣ ገብስ፣ ማሽላ፣ ...ወዘተ የመሳሰሉትንና ሙክትና ቅቤ በመቅለብ አልነበረም ። እንደ ሁለተኛ የምግብ ዓይነት የሚታዩትንና በመሬት ስር የሚበቅሉትን / Under- groundroots / ፣ እንደ ጎደሬ፣ ወጨና፣ የሮ፣... ወዘተ በማፍሬትና በመመገብ ነበር ። እነዚህ የምግብ ዓይነቶች በሬዋላ ወገን የተናቁ የምግብ ዓይነቶች ነበሩ ። የገበሬው ወገን የአራሱን የምግብ ፍላጎት ለማሟላት በእነዚህ ብቻ አይጠቀም ነበር ፡፡ ሥጋ ለመብላት በበዓና በፍየል እንዲሁም በበሬ ሥጋ ፋንታ / ለመግዛት ስለማይችል፣ የሚያረባውን ለባላባቱ ስለሚሰጥ/ ዶሮ፣ ሚዳቋ ጅግራ፣ አሪያ፣... ወዘተ የመሳሰሉትን የዱር አራዊቶች በማደንና በማቀዱ



ነበር የአራሱንና የቤተሰቦቹን የሥጋ መብላት ፍላጎት የሚያሟላው ። ይህ ዓይነቱ የምግብ ሁኔታ በእርግጥ በደሐ ገበሬ ዘንድ ሊኖር የሚችል የምግብ ችግርን መከላከል ችሏል ብንል ስህተት አይሆንም ።

በቤተክርስቲያን እጅ የተያዙትን፣ በሩሬ ጋሻ መሬቶች በነመለከት ደገሞ በዙዎች የሚታረስባቸው አልነበሩም ። በዙዎቹ ቀባውስት፣ እንደኛ በወር ውስጥ እስከ አስራ ዘጠኝ ዱረስ በሚየጠሩ በዓላት የቤተክርስቲያን ተገባሪቻቸውን ለማ ሟላት በምርት ሂደት ውስጥ አይሰተሩም ። ሁለተኛ በእነዚህ በዓል ቀናት በው ስምትና እርባ ቢወጣ፣ ዝክር ቢደገስ፣ ክርስትና ቢነሳና በሌሎች በዓላት በሚ ደረገው የደጀ ሰላም ዱግስ ምገብ የሚኖሩ ተገኛ የነበረተበበ ከፍሎች ነበሩ ። በዙው የደሐ ገበሬ የቤተክርስቲያን ቁይማኖት ተከታይ ባይሆንም፣ እማኝ የሆ ኑ፡ገበሬ የቤተክርስቲያን ክልል ሳንበር የሚሆን ስንዴ፣ ለነፍስ አባት የሚ ሆን በጠታና ወይንም ጠበል ቢረጭ የሚቀርበውና የሚደገሰው መጠነኛ ዱግስ የገበ ሬውን መደበና ላሳውን ደጋ የነበረተበበ ከፍል ቢያራቆት፣ ካህናትን ተገኛ / Parasite / አድርጓቸዋል ። በዚህም ላያርስ፣ ላጣር የሚችለው ወጣት ካየቀን፣ ካህንና ደብተራ በዚህ ልማዱ ተጠምደ መሬቱን ጦም አያባደረ እሱም በከለበት ደረጃ አራሹን ገበሬ ቢያራቆት የሚኖር ነበር ። ይህ ሁኔታ ይበልጥ በበሚን ማህተሙን ረገጠና ተስፋፍቶ ይገኛል ።

ከፒታሊዝም ወደ ኢትዮጵያ ሲገባና በእንዳንዱ አካባቢዎች የገንዘብ ኢኮ ኖሚ ቢስፋፋ መሬት የመሸጥና የመለወጥ ዕድል ያጋጥም ነል ። ከዱሮው አስተዳደር የተሻለ ከጣሊያን ዱል መመታት በኋላ በወረዳ፣ በምክትል ወረዳ፣ በአውራጃዎች ቢኒያም በዙዎቹ በዳኝነት፣ በምክትል ወረዳ ገዥነት፣ በወረዳ ገዥነት፣ በጠበቃነት በሬጋር ጸሐፊነት፣ በተሳሳኪነት፣... ወዘተ ከበሚን በመጠና የቤተክርስቲያን ትም ህርት ዕውቀት ባለቸው ሰዎች ይያዛል ።በዙዎች ደብተራዎች፣ ደያቆኖች ወይንም ያፈ ረሱ ቄሶች ነበሩ ። በእርግጥ በእንዳንዱ ወረዳዎች ቆራጊን የሚችሉ ለፖሊሲ ተበሉ በአነስተኛ ደመወዝ የተቀጠሩ ከሀገሬው የባላባት ወገን የተመረጡ ታዲ በመ ባል የሚታወቁ ሰዎች ነበሩ ። ያም ሆነ ይህ እነዚህ የአስተዳደር ሰዎች የመሬትን የመገዛትና የመሸጥ ዕድል በመጠቀም በአጭር ጊዜ ውስጥ ሀብታም ሲሆኑ በአንጻሩም የሀገሬውን ሕዝብ ሊያራቆቱት ችለዋል ። እንዴት ? በእውነቱ ከሀገሬው ባላባት

በስተቀር የመሬት ባለቤትነትን ያገኙ የሀገሬው ሰዎች ነበሩ ። የገንዘብ ኢኮኖሚ ሲስፋፋ በዙዎች ወደ ቡና ተከላ ይሰማራሉ ። ቡና ካሽ ክሮፕ እንደመሆኑ መጠን ከሌሎች ጋር ሲወዳደር ሥራው አዳካሚ ስላልሆነ ማራኪነቱ ከፍ ያለ ነበር ። ይህንን ሁኔታ የተመለከተው የሀገሬው ሰው ፊት ያርስ የነበረውን የእህል ዓይነት እየተወ ወደ ቡና ተከላ ያደላ ነበር ። ነገር ግን ይህ የገንዘብ ኢኮኖሚ ማደግ ያመጣው ሁኔታ፤ በዚያ ሀገር ሥርዓት የሕዝቡን ደህንነት ለመጠበቅ ባይሆን የአስተዳደሩን ጸጥታ ለመጠበቅ ተብሎ በረቀቀበት ሀገር የባላባት መደብና እነዚህ አዲስ የአስተዳደር ሰዎች በጥንቻቸውና በእሳቸው ሥልጣን በመተማመን እነዚህን አነስተኛ መሬት ያላቸውን በመገፋት ወደ ፍርድ ቤት እንዲመላለሱ ያደርጓቸው ነበር ። ፍርድ ቤት በተመላለሱ ቁጥር ደግሞ ወጪ ቸው እየጨመረ ሄደ ። ለማመልከቻ ፀሐፊ፤ ለተሳሳኪ፤ ለ ዳኛ ፀሐፊ፤ ለዳኛ ፤ ለፋይል መክፈቻ እየተባለ የሚሰጠው ጉቦና የሚከፈለው ገንዘብ በኑሮአቸው ላይ አሉታዊ ውጤትን አስከተለ ። አምርተው የሚሸጡት ቡና ይህን ወጪ ቸውን የሚሸፍንና ቤተሰባቸውን ለማስተዳደር የሚችል ስላልነበር፤ ለዚህና አራሽ ቸው የሚያመርትትን መገብ ለመግዛት የገንዘብ አራጣ ይገቡ ነበር ። ይህ ደግሞ በዓመት ሲከፈል አጥፍ ሆና ስለሚመጣ ዕዳቸውን መክፈል ያልቻሉት እንዳንደቹ መሬታቸውን ለመሸጥ ይገደዱ ነበር ። ወይንም ለሰው ባላባት ጋ ሄደው በመበደር የበለጠ የዕዳ ከምቸት ያርፍባቸዋል ። ይህ ሁኔታ በአንዱ በኩል እነዚህን የመንግሥት ባለሥልጣናት ሲያደልባቸው የሀገሬ ሕዝብ እየደኸየ መጣ ። በእርግጥ ረሐብ የሚባለው ነገር በደሩ አይታወቅ እንጂ በዕብቅ " ረሐብ " የሚታየው ሕዝብ ቁጥር ቀኔት አልነበረም ።

መሬት የመሸጥና የመለወጥ መብቱን ቢይዝ፤ የገንዘብ ኢኮኖሚ በመጠኑም ቢሆን ሲስፋፋ፤ ቀስ በቀስ ቡና በበዛት በሚያቀልባቸው አካባቢዎች የተዘረጋው መንገድ፤ የአንዳንዱ " ዘመናዊ " ከተማዎች መስፋፋት የአረጀውን የፊውዳል ስልተ ምርት ለመታትነውና በምትኩ ካፒታሊዝም ሊያድግ አልቻለም ። ይህ የፊውዳል ስልተምርት ጠንካራ ስለነበረና በገበረተቡ ውስጥ ማሕተሙን የረገጠ ስለነበር ከወዲ ለገቡ " የካፒታሊስቱ ኢኮኖሚ "– የገንዘብ ኢኮኖሚ በገለው ይሸሳል – ቦታውን ሊለቅና እርስ በእርሱ የተያያዘ የካፒታሊስት ስልተ ምርት/ Capitalst mode of production / ሊያድግ አልቻለም ። በገንዘብ መስፋፋትም ቀስ በቀስ የቡ



ና ተከላ ያስፋፋው የባላባት መደብም በየጊዜው ከቡና ሽያጭ የሚያገኘው ገንዘብ ለልጆች፤ ለቀርስ እያለና መሬት በተጨማሪ ከመግዛት፤ ትንሽ ዘመናዊ ለሆነውና በከተማዎች ለሚኖረው ዘመናዊ ቤቶች ከማሠራትና አንዳንዱ ትላልቅ ዕቃዎች ከመደገስ በስተቀር ይህን ያህልም በሀገሪቱ ውስጥ የሚመረቱትን የኢንዱስትሪ ምርቶችን እየገዛ የሚጠቀም መደብ አልነበረም ። በአንዳንዱ አካባቢዎች በትላልቅ የውጪ ሀገር ከበርቴዎችና ከባንዳዎች፤ በመንግሥትና በኢትዮጵያውያን " ከበርቴዎች " በአነ ዓለም ባንክ አበዳሪነትና አማካይነት የተደጎሙት፤ ወይንም በሲዳ /SIDA / አማካይነት የተሠራት የእርሻ ማባያች እንደዚሁ ለካፒታሊዝም ማደግ የረዱ አልነበሩም ። ትናንሽ ገበሬዎችን እረዳለሁ ብሎ በጸር በመስመት፤"የተሻለ ዘር" በማበደር ማዳበሪያ በመስጠት ይተባበራል የተባለው ይህ የዓለም ባንክ፤ ይረዳ የነበረው የመሬት ከበርቴዎችን እንጂ ደሃ ገበሬዎችን አልነበረም ። በሀገሪቱ አይፈቀዱም ። ይልቅ በተያያዘው በዚህ ዘመናዊ እርሻ መስፋፋ የተነሣ ትናንሽ ገበሬዎች፤ ከእነዚህ ቀደቶች በዚህ የዘመናዊ የእርሻ መስክ ላይ በባሪያ ደመወዝ /አነስተኛ ደመወዝ / ሲቀጠሩ፤ አብዛኞቹ ይህንን ዕዳ ያላገኙት ደግሞ ለዘመናት ያደጉበትንና የኖሩበትን መንደርና ማሣ በገዱ እየለቀቁ ወደ ከተማዎች በመሰደድ ኩሊነት ፤ ቤተኛ አገልጋይነት፤ ለአከርነት ፤ አንዳንዶቹ የቤት አሽከር ገረድ በመሆን፤ ሌሎች ይህንን ዕዳ ያላገኙት ደግሞ ማጅሬት መኛ ኪስ አውላቂ ወደ መሆን ተሰማሩ ። ይህ ሁኔታ ሌላ የገበረተብ ክፍልን፤ በኑሮው በጣም ዝቅተኛና ተጎጂ የሚኖርና ደሀን ፈጠረ ። አብዛኛው ማደያ እንኳ አልነበረውም ። በየበረንዳው ውርጭ እየነደፈውና እየተሰቃየ የሚኖር ነበር ። ዛሬም የምናየው ነው ።

በሌላ ወገን ግን እነዚህ በውጪ ሀገር ከበርቴዎች፤ በመንግሥትና በሀገሪቱ የመሬት " ከበርቴዎች " በተደጎሙት እርሻዎች ላይ የሚመረተው ምርት ለውጪ ገበያና ለጥቂት የከተማ ተመጋቢ ሕዝብ ተብሎ ስለነበር የሀገሪቱን ሕዝብ የምግብ ጥያቄ ሊያሟላና ሊመልስ አልቻለም ። ይህም ማለት አብዛኛው በሬ የከተማ ሕዝብና ሌላው በየክፍለሀገሩ የሚኖረው የዚህ ዘመናዊ እርሻ ውጤት ተጠቃሚ አልነበረም ። ከዚህ በላይ ግን፤ ይህ በዘመናዊ እርሻ መደጎምና ለውጪ ገበያ በማቅረብ ሀብት

ማካበት የቻለው የሀገሪቱን ከበርቴ የውጪ ሀገር ዕቃዎችን ከመግዛትና ከመጠቀም / consume / በስተቀር ፕሮዳክቲቭ የሆኑና የሥራ መስክ ሊከፍቱ የሚችሉ ኢንዱስትሪዎች ላይ አትኩሮ ሊያደርግ አልቻለም ። ከውጪ የገባው ውስን የካፒታሊስት ግንኙነት ዓይኑን ሊከፍት አላስቻለውም ። የመደብ ጥቅሙን አውቆና ተረድቶ ታሪካዊ ሚናውን ሊጫወት አልቻለም ። ይልቁንስ ወግ አጥባቂና ባለው ሀብት ተደስቶ የሚኖር መደብ ሆኖ ቀረ ። ይህ ከላይ የተዘረዘረው ሁኔታ በሀብታምና በድሃ መሀከል ያለውን ልዩነት ይበልጥ አሰፋ ። ችግሩ የዙሪያ ጥምጥም ሆነ ። በዚህም ሀገሪቱን በአላት የሰው ጉልበትና የተፈጥሮ ሀብት በመጠቀም ወደፊት የተራመደች ባትሆን እየቀረቀዘች የሄደች ሀገር ሆነች ።

4.2 የሰሜኑ ሁኔታ ።

የሰሜኑ የመሬት ስሪትና በየጊዜው እየተደጋገመ የታየው አስቃቂ ረሐብ ሁኔታውን ከደቡብ ለየት ያደርጉታል ። በሰሜን ክፍላተሀገራት የተለያዩ የመሬት ስሪቶች እንደነበሩ የታወቀ ነው ። በተለያዩ ዘመናት የነገሡት ነገሥታት መሬት ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራቸው ስር የነበረና መሬትን የማከፋፈል መብትና ሥልጣ ማን እንዳላቸው /እንደነበራቸው/ ግልጽ ነው ። በዘመኑ መሬት፣ በሐይማኖት በወታደርነት አገልግሎትና ለንጉስ በቀረቡና ለቤተክህነት በይዞታ ይሰጥ ነበር ። የክርስቲያን ሐይማኖት ባልደረባ ያልነበሩ ከዚህ የመሬት " ዱልዱል " ውስጥ ከቁጥር አይገቡም ነበር ። ይህ እስላሞችን፣ ፈላሻዎችንና ሸክላ ሠሪዎችን እንደሚመለከት ስለኢትዮጵያ ታሪክ በተጻፉት መጽሐፍት ውስጥ ይገኛል ።

ይህ የመሬት ዱልዱል ቢያንስ ሦስት ዓይነት የመሬት " ዱልዱሎችን " ይይዛል ። አንደኛው ርስት በመባል የሚታወቀው ለአረሽ ገበሬዎች በቤተሰብ አማካይነት /family unit / የሚሰጥ ነበር ። ሁለተኛው ጉልት የሚባለው ለንጉሡ ሹማምንት እንደየማዕረጋቸው የሚሰጥ መሬት ነው ። ሰሞን በመባል የሚታወቀውና በቤተክርስቲያን ስር የሚወድቀው የመሬት ይዞታ ነበር ። ከእነዚህ ውስጥ ለየት ያለውና በዚህ ዱልዱል ውስጥ የማይገባው የመንግሥት መሬት በመባል የሚታወቀው ነው ። በዘመኑ ይህ ዓይነት አደላደል ይኑር እንጂ ማንኛውም ዜጋ መሬትን የመሸጥና የመለወጥ መብት አልነበረውም ።



እያንዳንዱን የመሬት ይዞታ ወስደን ብንመለከት የሚከተሉትን ስዕሎች እናገኛለን ። ርስት /Rist / የተባለውና በቤተሰብ አረሽ ገበሬዎች ስር በተያዘው መሬት ላይ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል አርሶ የመጠቀም መብት ነበረው ። ይሁን እንጂ ከታረሰው ውስጥ የተወሰነው ምርት ባካባቢው በሚገኘው የወረዳ ሹም የቀበሌ አስተዳዳሪ አማካይነት ለንጉሡ ይቀርባል ። እንዳንዱም እዚያው ለአስተዳዳሪዎች ይቀራል ። ይህ ብቻ አይደለም ። የዚህ ቤተሰብ አባል የሆኑ ገበሬዎች በንጉሡ መሬት ላይ ወይም በአስተዳዳሪዎች መሬት ላይ እንደየሁኔታውና አስፈላጊነቱ የጉልበት ሥራ ማበርከት ግዴታቸው ነበር ። ለዚህ ለጉልበት ሥራ የሚያገኙት ክፍያ ወይንም ዋጋ አልነበረም ። ከዚህ በተረፈ፣ በተለያዩ ባላባቶች ግጭት በተፈጠረ ቁጥር የአካባቢው አስተዳዳሪዎች ገበሬዎችን ከሥራቸው አስተጓጉለው ለጦርነት የማሠማራት " መብት " ነበራቸው ። በዚህ ሁኔታ፣ በየጊዜው በሚፈጠረው ግጭት የሚያልቀው ሰው፣ የሚቃጠለው መሬት ሀብትና ንብረት ከፍተኛ እንደነበር የታሪክ መጽሐፍት ያስረዳሉ ።

የሰሜኑ ገበሬዎች በገዢዎቻቸውና በአስተዳዳሪዎች የበላይነትና በዘባቺነት ብቻ የተጠቁ አልነበሩም ። የቤተክርስቲያን አባላትና የክርስቲያን ሐይማኖት ተከታዮች በመሆናቸው የሐይማኖት ግዴታቸውን ለማሟላት ግብር ለቤተክርስቲያን መስጠት፣ ድግስ መደገስ፣ ለነፍስ አባት ስጦታዎችን ማቅረብ፣ አዳዲስ ቤተክርስቲያኖች በተመሠረቱ ቁጥር ከሥራቸው እየተጓጉሉ እንጨት ማቅረብና ቤተክርስቲያን መሥራት ግዴታቸው ነበር ። ከዚህም በላይ የሐይማኖት ሕግጋትን በጣም ስለሚያከብሩ በበዓላት ቀናት በፍጹም የግብርና ሥራዎችን አያከናውኑም ። ሴቶቹም በእነዚህ ቀናት ወፍጮ አይፈጩም፣ ሙቀጫ አይወቅጡም፣ ስፌት አይሰፉም፣ አይፈትሉም ። ይህ ሁኔታ በጠቅላላው ተደምሮ ተደማምሮ በሰሜን ገበሬዎች ላይ በየጊዜው ከፍተኛ ድህነትን አስከተለ ። ምርታቸው በየጊዜው ዝቅ እያለ ሄደ ። ሀገሪቱ በነበረችበት የቦስቀ ኢኮኖሚ ሁኔታና እስከ ዛሬ ድረስ እንደሚታየው እነዚህ ገበሬዎች የአስተራረስ ዘዴአቸውን ለማሻሻል የኢኮኖሚ ሁኔታቸውና ባሕላዊ አኗኗራቸው አይፈቅድላቸውም ነበር ። የመሬታቸው መጠን /ቦታ/ ውስን ስለነበር ከዓመት ዓመት እንዲሁ ሆኖ አባዶሮው ለሳ ቦታ በማረስ ዱር ይታረስ የነበረውን እንደገና ፍሬያማ / reproduced /ለማድረግ ወይንም እንዲሆን ችሎታ አልነበራቸውም ። በመሆኑም ያው መሬት ከዓመት ዓመት

ካለማዳበሪያና ሌሎች አፈሩን ሊያለመልሙና የአፈሩን ለምለምነት የሚጠብቁ ነገሮችን እንደ ማዛወርና / rotation / ቴራሲንግ / terrac-ing / ለመጠቀም አይችሉም ነበር ። በሌላ አነጋገር በበሬን ከፍላተ ሀገሬት – ሌላውም ቦታ እንደዚሁ በሰፊም–መሬትን መላልሶ የማረስ / extensive farming / ልምዱ የተስፋፋ ነበር ። ይህ ሁኔታ ከዓመት ዓመት የምርትን ዝቅ ማለት፣ የመሬትን መሸርሸር በሎም የመሬትን ልምላሜ ማጣትና በመጨረሻም በገበሬዎች ላይ ድህነትና ረሐብን አስከተለ ።

ይህ የበሬን ገበሬዎች በአህል መልክ ይገበሩ የነበረው የገበርና የጉልበት ሥራ በኃይለ ሥላሴ ዘመን የቀረና የተከለከለ በሆነም መሠረታዊ ለውጥ ባለመደረጉና ከዚህ በፊት የነበረውን የኅብረተሰብ ግንኙነት / social relationship / ከስር መሠረቱ ስላልነካው የገበሬዎቹ የኑሮ ሁኔታና የምርት መሻሻል / productivity / በፍጹም ከድሮው ሁኔታ አልተለወጠም ። የቤተክርስቲያን ካህናትም በእነዚህ ገበሬዎች ላይ ጥገኛ ስለነበሩና የበዓል ቀናትም ከድሮው ያልተቀነሱ ስለነበሩ ሁኔታው እስከ የካቲት አብዮት ድረስና ዛሬም በሆነ ማሕተሙን እንደረገጠ ይገኛል ።

ስለ ኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ በተለያዩ ጊዜያት የተጻፉት መጻሕፍት ስለእርሻ ምርት አለማደግ ወይንም መቀነስ ገበሬው የምርት መሣሪያዎችን ለማሻሻል ዝግጁ ያለመሆኑን፣ በነፍ መሆኑንና ወግ አጥባቂ መሆኑን ያመለክታሉ ። በእውነቱ ይህ አባባል በጊዜው የነበረውን የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ በፍጹም አያንጸባርቅም ። በአብዛኛዎቹ ገበሬዎች የተያዘው መሬት በአማካይ ሲታይ ከ1.95 ሔክታር አይበልጥም ነበር ። ከዚህ እየተመናመነ ከሚታረስ መሬት የሚገኘው የምርት ውጤት ደግሞ ካለው ዝቅተኛ ቴክኖሎጂ ጋር ተደምሮ ምርትን ሊያባዛ አይችልም ነበር ። በዚህም ከምርቱ ሽያጭ የሚገኘው ገቢ – ገበሬው ምርቱን የሚሸጠው በዙ ስለሚያመርት፣ ወይንም እትርፍ በማምረቱ / Surplus product / ባይሆን – እራሱ የሚያመርታቸውን ነገሮችንለጊዜው ሊጠቀምባቸው / Consumption goods / የሚችላቸውን ነገሮች ለመግዛት እንጂ፣ ተርፎት ተትረፍርፎት አይደለም ። የምርት መሣሪያዎች ቢገዛ ግፋ ቢል በእጅ የተሠራ እንደ ማጭድ ፣ ገጀሬ /የገጠሬ/፣ መቆፈሪያና



ወገል... ወዘተ እንጂ በሬ እንኳ ለመግዛት ችግር ነበረበት ። እንግዲህ ይህ ማለት እንደ ጥሬ ዘር፣ ትራክተር፣ ማዳበሪያ የመሳሰሉት በፍጹም ጥያቄ ውስጥ አይገቡም ማለት ነው ። በሬ ለመግዛት እንዲችል እንኳ፣ በቡና ለቀማ ወራት ወደ ጅማ፣ አጋሮ፣ ሊሙና ሌላ ቡና ወደ ሚመረትባቸው ከፍላተሀገሬት ቦስት ወተ አራት ወተ ኪሎ ሜትሮች የሚጓዘው የጎንደር፣ የጎጃም፣ የትግሬና የወሎ ሕዝብ እራሱ በቂ ምስክር ነው ። ያበበውንም አገሩ ባያደርስ በመጓዝ ላይ እያለ በጊዜ በረሐና በሌላ አካባቢዎች የሚሞተው ስፍር ቁጥር አልነበረ-ውም ። ሁለተኛ የበሬኑ ገበሬ ወግ አጥባቂ ነው ቢባል እንኳ የሐይማኖት ሚናና ይህ በተለያዩ ጊዜያት የነገሡት ነገሥታት ሥርዓቱን ለመጠበቅ እንዲረዳቸው ሕዝቡን ለማሠር እንደቻሉና ራሱን የቻለ ርዕዮተዓለምና ከነበረው ሥርዓተ ማኅበር ጋር በፍጹም ተነጥሎና ተለይቶ ሊታይ አይችልም ። ቦስተኛ የኢትዮጵያ ገበሬ ሰነፍ ነው የሚባለው በእውነቱ ነገሮችን በሚገባ ለማየት አለመቻልና የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ ካለመረዳት የተነሳ ውንጀላ ነው ። የኢትዮጵያ ገበሬ /በመቶካኙው/ ወፍ ሳይጮህ ተነስቶ ካገኘ ቁርስ ቂጣ በበርበሬ በልቶና ውኃ ተጎንጭቶ ቀፈርና የነበሩን ተሸክሞ እንቅፋት ይመታኛል፣ ጋሬጣና እሾክ ይወጋኛል ባይል ከለምንም መከሳከያ መሬቱን እርሶ፣ አገሳብቦ፣ ዘርቶ፣ አርሞ ሲደርስ ከቤተሰቦቹ ጋር ካተቻለ በደቦ ቀኑን ሙሉ ቀጢቶ በሶ አርቆ ጎልጉሎ፣ እህሉ ሲደርስ አጭዶ፣ አድርቆ ከምሮ፣ ወቅቶ የሚያተርፍ ነው ። ይህ ሁሉ የቴክኖሎጂ ሁኔታዎች ባልተሟሉበት፣ መንገዱ ባልተሠራበት፣ ... ወዘተ በውነቱን ለመጠበቅ /reproduce / ጥሬ ምገብ በማይገኝበት ሁኔታ ውስጥ ነው ። ይህ ሁኔታ እሁንም በሆነ አልተሻሻለም ። አልተለወጠም ።

ክስ ሲቀርብ በኢትዮጵያ ገበሬ ባይሆን፣ ስንትና ስንት ወተ ጋሻ መሬት ይዞ ባይጠቀምበት የቀረው ባላባት መደብ ላይ መሆን አለበት ። ይህንን ሁኔታ ለማሻሻል ባለመፈለጉና – ባሕሪዩም ስለማይፈቅድለት – ሕዝባችንን እራቁቱና አደኸየቶ ሊያስቀይ የነበረው አገዛዝ ላይ መቅረብ አለበት ።

ሌሎች የመሬት ስሪቶችን ብንመለከት ጉልትና ስሞንን፣ በእውነቱ የጋሳ ጋሳ ሙሉ በሙሉ በቤተክርስቲያን እጅ የወደቁ፣ ጉልት የተባለው የባላባትን የመሬት ገን

ችነት የፈጠረ ነው ። ለምርት አለማደግም ያለው አሉታዊ ውጤት በባላባቱ መደብ ወግ አጥባቂነትና ከመሬቱ ባገኘው ሀብት ብቻ ተደስቶና ተመክቶ የሚኖር መደብ ብቻ በመሆኑ ነው ። በቤተክርስቲያን እጅ ሥር የነበረው አብዛኛው መሬት የሚታረስ አልነበረም ።

እንግዲህ እነዚህን ሁኔታዎች በምርት ሂደት ላይና በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ያላቸውን አሉታዊ ውጤት በመጠኑም ቢሆን ከተመለከትን በኋላ፣ ሌሎች ለመሬት መሸርሸር፣ለለምለምነቱ መቀነስ ምክንያት የሆነውን ድርቅ ምን ያህል ከፖለቲካ ጋር በቀጥቅ የተሳሰረ ለመሆኑና በኢትዮጵያ ውስጥ የኃይል /Energy / ችግር ለዚህ እንዴት አስተዋጽኦ እንዳበረከተ እንመልከት ።

4.3 <u>የኃይል ችግር / Energy problem / የፖለቲካ ውጤት፣ነው</u> ።

ከሃምሳ ዓመታት በፊት የኢትዮጵያ መሬት ስልሳ በመቶው / 60% / በደን የተሸፈነ እንደነበር የታሪክ ፀሐፊዎች ያረጋግጣሉ ። ከዚያ በፊት የደረሰውን ተደጋጋሚ ረሃብ ለታሪክ ብንተው ይህ የደን ሀብትና የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ፀጋ እንዴት ኢትዮጵያን አሰለቀናለሁ በሉ ወይንም /Modernizer / ተብሉ በሚጠራው የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ሊወደም ቻለ? ምክንያቶቹስ ምንድን ናቸው?

የዘመኑ ባይገነስ፣ ቴክኖሎጂና ልዩ ልዩ የአጠቃቀም ዘዴዎች ባልተስፋፋበትና ባላደገበት ሀገር የሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ፍላጎቱን ለማርካት የግዴታ በቀርቡ በሚያገኛቸው ነገሮች ላይ መመካት አለበት፡፡ እህል ዘርቶ፣ አብቅሎ የግዴታ ይህንን አብስሎ መብላት አለበት ። ካለበለዚያ ለመፍጨው / ለመጋገረው / ያስቸግረዋል ። እራሱን ከብርዱ፣ ከዱር አራዊት ለመከላከል የግዴታ መጠለያ ያስፈልገዋል ። የሰው ብዛት እየጨመረ፣ ቢአንዱ ቦታ መንደርን በየረቀረ ቁጥር እንደ ሕዝቡ ብዛት ፍላጎቱም ይጨምራል ። መንደሮች ይቀረቀሩ፣ ቤቶች በብዛት ይሠራሉ ። እንደዚሁ ይቀጥላል ። እንግዲህ አንዱ ሰው፣ አንዱ ቤተሰብ፣ የአንዱ መንደር ኗሪ ሕዝብ ለመቀቀያ እንጨት ቢያስፈልገው፣ ለመኖሪያ ቤት ቢያስፈልገው፣ ለማረሻ ቀንበርና ሞፈር ቢያሻው ያቺ ተፈጥሮ የለገሰቸውን መጠቀም አለበት ። እሷ እንዳታልቅበት ካሰበ ደግሞ፣ እነዚህን በሌላ የሚተካባቸውን ዘዴዎች መፍጠር አለበት ማለት ነው ። ይህ ሁኔታ



ከሌላ፣ከታሠረ ዘር ዘር የግዴታ ተፈጥሮ ያቀረበውን ፀጋ ብቻ መጠቀም አለበት ። ለዚህም እንዱ ዛፍ ሁለት ዛፎች፣... ወዘተ በተቀረጡ ቁጥርና እነዚህን መልስ ለመተካት ካልቻለ ከዚህ በፊት በደን የተሸፈነው መሬት ከጊዜ ወደ ጊዜ፣ ከወረት ወደ ወረት ከዓመት ወደ ዓመት እየቀነሰና ብሎም እየወደመ ይሄዳል ማለት ነው ። ይህንን ሁኔታ አዙር ባያይ፣ ባያስበ ሁኔታዎች ስላለአስገደዱት እንጂ — በነገሬችን ላይ የሰው አስተሳሰብ ካሉት የማቴሪያል ሁኔታዎች ጋር የተያያዘ ነው። ይህ ማለት ግን የማቴሪያል ሁኔታዎች ባደገበት ሀገር፣ ባይገነስ ቴክኖሎጂ በተስፋፋበት ሀገር የሰው አስተሳሰብ የገበረ ነው ማለት አይደለም ። ነገሮችን መመርመር ይችላል ማለት አይደለም— አቅንና አገሩን ስለ ተበተቡት እንጂ ሌላ ምክንያት ኖርት አይደለም ። በመሆኑም የዛፎች መቀረቅ፣ የደኖች መቀፋት የአካባቢንን ሁኔታ፣ የአየርን ጠባይ እንደሚለውቀ ደገም የታወቀ ነው ።

ባለፈት ገጾች ውስጥ መላልስ ማረስ / Extensiv farming / የተለመደ መሆኑን ማዘዋወር /rotation / አስቸጋሪ መሆኑን አይተናል ። በነዚህ ላይ ተደምሮ የደን መቀፋት ለኢትዮጵያ ድርቅ ብሎም ለረሃቡ መገባት እንደ ምክንያት ሆና ይቀርባል ። ይህ ደግሞ ዘር ዘር ቸናው ምክንያት የፖለቲካ እንደሆነ በኋላ ማየት እንችላለን ። የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሕይወት ከእንጨት ጋር የተያያዘ ለመሆኑ የታወቀ ነው ። 95% የሚሆነው ኃይል /Energy /ከእንጨትና ከእንስሳት በተገኙ ውጤቶች / ኩበት፣ ፋንዲያ፣ በጠቀ / ላይ የሚመካ ነው ። ከዚህ ውስጥ እንጨት ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል ። ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ዕድገቷ፣ ሕዝቧ በማቴሪያል ሁኔታው ወደኋላ የቀረና የደኸየ ስለነበረና ስለሆነ የግዴታ የራሱን ኑሮ ለማቸነፍ ከላይ በተቀመጠው መልክ ዛፍን እየቆረጠ መጠቀም አለበት ። ዛፎች በተቀረጡና ቀስ በቀስ በወደመ ቁጥር የአየሩን አርጥበት የሚጠብቅት፣ መሬቱ በየጊዜው እንዳይሸረሸር የሚረዱት፣ እቀፈው ደገፈው የሚይዙት አይኖሩም ማለት ነው ። ዛፎች በተፈጥሮ ፀጋቸው ኦክሲጅን ይተነፍሳሉ ። ይህም ከሃይድሮጅን ጋር ተቀላቀሉ ከተወሰነ ከነውን / Reaction / በኋላ ወደ ውኃ፣ ዝናብ ይለወጣል ። ዛፎች በተቃራኒው ከእንስሳት ካርቦንዳይኦክሳይዱን / $CO_2$ / ወስደው ለምግብ

መሥሪያቸው ከሌሎች በተፈጥሮ ዛፎች ውስጥ ካሉ /Chlorophyll /ነጥረ ነገሮችና ከፀሐይ ጋር ይጠቀሙበታል ። እንግዲህ የሰው ልጅና የደን መኖር የሚደጋገፉና መጠበቅ ያለባቸው ናቸው ። ይህ ሁኔታ ከሌለ ግን፣ አፈሩ እንዳይሸረሸር፣ ዝናብ እንዲዘንብ ጥላ እንዲኖር፣ ነፋስ እንዲነፍስ የሚያደርጉት ዛፎች ተፈጥሮአዊ ተግባራቸው በመቋረጥ ስለሚነፈግ የመሬት ለምለምነት ይበደላል ። በየጊዜው እልፍ እልፍ ኃይለኛ ዝናብ ሲዘንብ በጎርፍ የመሬቱ ለምለም ክፍል /Top soil / ይታጠባል ። ነፋስም በነፈሰ ቁጥር እንደዚሁ በደን መጥፋት የተጋለጠው በነፋስ አፈሩ እየበነነና እየተጠረገ ይበታተናል ። ይህ ሁኔታ ለረጅም ጊዜ ከቆየና ቶሎ ብሎ አስቸኳይ እርምጃ ካልተወሰደ ዙር ዙር ዝናብ አለመዝነብን፣ ድርቅን ብሎም የተዘራ አለመብቀልን ሲያስከትል ሰዎች የሚበሉት ሲጠፉ፣ በሰውነታቸው ውስጥ የተከማቸው እየተመጠጠ፣ መጨረሻ ላይ ለረሃብና ለሰውነታቸው መመንመንና ብሎም ለሞት ይጋለጣሉ ። ሰዎች ይጠፋሉ ። የረጅም ጊዜ መንደርና ኑሮ ይበታተናል ። ሀገር ምድረ በዳ ትሆናለች ። ይህ እንዱ ምክንያት ሆነ በጠቀሳሰው ከብቶች/ በሬ፣ ላም፣ ፍየል፣ በግ፣ አህያ፣ ፈረስ፣ በቅሎ፣ .../ የሚመገቡት ምግብ በተለየ መልክ ካልተዘጋጀላቸው የግጦሽ ሜዳ ላይ ስለሚውሉና ስለሚግጡ እነሱም በበኩላቸው ለምለም መሬትን ያደርቃሉ ። ወደ 70 ሚሊዮን የሚጠጉ ከብቶች ባሉባት ሀገር ሁኔታው የበለጠ አሳሳቢ ለመሆኑ ግልጽ ነው ። ይህ ጉዳይ ግን እንዴት ከፖለቲካ ጋር ሊያያዝ ቻለ ወይንም ይችላል?

እንዱ መደብ ሥልጣን ላይ ተቀምጦ እራሱን የሚያደልብ፣ ጭቆረሊ የሚረገጥ፣ ለሀገሩ ዕድገትና በልጽገና ማሰብ የማይችል ከሆነ የሚያመጣው ውጤት ጥፋት፣ ድህነትና ረሀብን ነው ። እንዱ ኃላፊነት የሚሰማው መንግሥት ከሆነ ደግሞ/ በእርግጥ ከመደቦች በላይ መንግሥት የለም /ለሕዝቡ ፣ መንገዱ፣ ትምህርት ቤት ፣ ኃይል ፣ ሌሎች መሥሪያና ማምረቻ ነገሮችን ወዘተ ወዘተ ማቅረብ መቻል አለበት ። ሕዝቡ እንዲሠራ፣እንዲማር ዕቅዶችን ማውጣት ብቻ ሳይሆን በሥራ መተርጎማቸውን በየጊዜው መመርመር አለበት ። በእርግጥ እንደዚህ ዓይነቱን ሁኔታ ማንኛውም መንግሥት አያደርገም ። የታሪክን ኃላፊነት የተቀበለ፣ የሰው ልጅ ታሪክ ምን እንደሆነ የተረዳ፣ የፖለቲካ ባሕል ያለው፣ የተፈጥሮ ፀጋ ምን እንደሆነና ይህንን ተንከባክቦ መያዝ እንዳለበት የተረዳ መንግሥትና አገዛዝ መሆን አለበት ። ካለበለዚያ ከሕዝቦች በሚዘረፈው ሀብት የታወረ ከሆነ፣ እራሱን ከማንኛውም ሰውና ፍጡር በላይ አድርጎ የሚቆጥር ከሆነ የታሪክ ተልዕኮውን የማያውቅ ኃላ ቀር መንግሥትና አገዛዝ ነው ።



የመወርወሩና የመደምሰሱ ጉዳይ ታሪካዊ ግዴታ ይሆናል ማለት ነው ።

ያ የኃይለሥላሴ መንግሥት ያደረገው ይህንን ከፍተኛ ወንጀል ነው ። መብራት ቢገባ ለተወሰኑ ከተሞች፣ መንገዱ በሥራ ለተወሰኑ አካባቢዎችና የእርሻ መስኮች፣ ትምህርት ቤትና ሆስፒታል በሥራ ለተወሰኑ ከተማዎች፣... ወዘተ በመሆኑ ሀገሪቱን ከፍተኛ ውድቀት ውስጥ ከተታት ። ያ ለማበስል፣ ማታ ለማየት፣ ለመጠለል፣ የግዴታ የሚፈልገው የሰሜን ሕዝብ ዛፍን ብቻ እየቆረጠ መጠቀም አለበት ። ካለበለዚያ ፍርዱ አብስለህ አትብላ፣ መጠለያ አትሥራ ፣ ለእራቲት ለብርዱ ተጋለጥ ማለት ነው ። እንግዲህ መንግሥትና አገዛዝ ይህንን ኃላፊነት ካልተረዳ ዙር ዙር የድርቅና የረሐብ ዋና ተጠያቂ ነው ማለት ነው ።

ይህ ብቻ አይደለም ። የሥራ መስክ መክፈት የማይችል አገዛዝ /Government / ከሆነ ሰዎች እራሳቸውን ለማሸነፍ ሌላ የመኖሪያ ዕድል ከሌላቸው እንጨትን ቆርጠ ፣ አድርቀና ፈልጦ በመሸጥ እንዲኖሩ ይገደዳሉ ።ሌሎችም ከሰል አክስለው እንደዚሁ ገንዘብ ያገኙበታል ።ዛፍ / እንጨት / የኃይል ምንጭና የመጠለያ መሥሪያ ብቻ ሳይሆን የገቢ ምንጭ እንደሆነም መረዳት ያሻል ። ብዙ እናቶቻችን፣ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን በዚህ እንደሚተዳደሩ መረዳት ያስፈልጋል ።እንግዲህ ይህንን የሚያይ መንግሥት፣ ሀገርን አስተዳድራለሁ የሚል፣ እንደዚህ ዓይነቱን ችግር ለመቋቋም፣ በእንጨት ፈንታ ሌላ የኃይል ማመንጫ ዘዴ፣ በእንጨት መሸጥ ፈንታ ሌላ የሥራ መስክ መክፈት አለበት ። በአጭሩ ሕዝብን መንከባከብ ሀገርን መጠበቅ አለበት ማለት ነው ። በእውነቱ ድርቅና ፖለቲካ፣ ረሐብና ፖለቲካ፣ ድህነትና ፖለቲካ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች መሆናቸውን መረዳት ከባዱ አይሆንም ።

### 4.4 የኃይለ ሥላሴ መንግሥት የእርሻ ፖሊሲ በተጨባጭና የቡና ሚና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ።

የአንዱ መንግሥት የኢኮኖሚ ሆነ የእርሻ ፖሊሲ የዚያው ሀገር የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሥርዓትን የሚያንፀባርቅ ሲሆን፣ በአጠቃላይ የሶስተኛው ዓለም ሀገሮች ከሀገራቸው ባሕል፣ ከሕዝባቸው አኗኗር፣ ከሕዝባቸው ፍላጎትና ዕድገት ጋር የሚሄድና የሚያያዝ ፖሊሲ አላቸው ብሎ አፍን ሞልቶ መናገር በፍጹም ያዳግታል ። በዚህም ወገን ኢትዮጵያችን ፍጹም የተለየች አይደለችም ። በዓለም አቀፍ ካፒታሊ

ዝም መሠረት የተቀነባበረው " የዕድገት " ፖሊሲ /The so called Develoment policy/ ከ1950 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ መመሪያ ነበር ::በዚህ ክፍል ውስጥ የኃይለ ሥላሴ መንግሥት የሀገሪቱ ዕድገት ዋና መሠረት በሆነው እርሻ ላይ ያደረገውን አትኩሮት፣ የተከተለውን ፖሊሲ እንዲሁም የውጭ ሀገር በእዚህ እርሻ ላይ የነበረውን ተፅዕኖ እንመለከት ::

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዋናው መሠረት እርሻ ነው :: ሀገሪቱ ከምታመርታቸው ምርቶች /GDP / 50 % የሚይዘው የእርሻ ውጤት ነው :: 80 –90% የሚሆነው ሕዝብ የሚኖረው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከእርሻ ጋር ከተያያዙ ተግባሮች ጋር ነው :: እርሻ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እምብርት እንደመሆኑ መጠን ሀገሪቱ ወደ ውጭ ከምትልከው 90 % ቱን የሚይዘው የእርሻ ውጤትና ከዚህ ጋር የተያያዙ ውጤቶች ናቸው :: ከዚህ ውስጥ 60% የሚሆነው ቡና ነው :: እርሻ የሀብት መመኪያ አንቀሳቃሽ በሆነበት ሀገር ውስጥ እስከ 1967 ዓ.ም ለ.ለ.ለ ባሉት ጊዜያት ውስጥ የኃይለ ሥላሴ መንግሥት በየዓመቱ ከሚያወጣው በጀት ውስጥ ከ2 –4 % ብቻ ለእርሻ ልማት ይመደብ ነበር :: የበጀቱ አማዛኙ ጉን የሚሄደው ለመከላከያ፣ ለፀጥታና ለሀገር አስተዳደር ክፍል ነበር :: በመጀመሪያዎቹ አንደኛና ሦስተኛ የአምስት ዓመት ፕላኖች አትኩሮት የተሰጠው ለእርሻ ምርት ባይሆን ለኢንዱስትሪ እንደነበር በየጊዜው የወጡት ዕቅዶች ያመለክታሉ :: ይሁን እንጂ፣ በአውሮፓ አቆጣጠር [illegible] ዓ.ም መጨረሻ ላይ የእርሻ መስክ " አትኩሮት እንዲደረግበት " በታሰበው መሠረት ከሀገሪቱ ጠቅላላ በጀት ውስጥ ወደ 13% በኋላ ደግሞ ወደ 16% ያድጋል ::በሶስተኛው ዓመት የአምስት ዓመት ፕላን በጀቱ ከዚህ ከፍ ያለ በሆነ 22% – ከዚህ ውስጥ 13% የሚሆነው ከውጪ የተገኘ ዕርዳታ ነበር :: በዚህም መሠረት የውጪ ተፅዕኖ በመንግሥት የእርሻ ፖሊሲ ላይ እየጨመረ እንደ ሄደ ልንገነዘብ እንችላለን :: ሆኖም ግን ለእርሻ የተሰጠው አትኩሮት ከፍ ያለ በሆነም በሀገሪቱ የእርሻና የምግብ ዕድገት ላይና በጠቅላላው ኢኮኖሚ ላይ ያመጣው ለውጥ እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም :: የሀገሪቱ ኢኮኖሚ፣ በተለይም የእርሻው መስክ የቆረቆዘ እንደ ነበር ይታወቃል ::

ለእርሻው መስክ " አትኩሮት " ሲሰጥና የውጪ ተፅዕኖ እያደገ ሲመጣ ትላልቅ የእርሻ መስኮች መስፋፋት ይጀምራሉ :: ከ1958/59 እስከ 1969/70 ዓ.ም



ባሉት ጊዜያት ውስጥ በዘመናዊ ዘዴ የሚታረሱ ማሳዎች ቁጥራቸው ከ32 ወደ 2626 ከፍ ይላል :: በዚያው መጠን የሚታረሰውም መሬት ስፋት ከ6244 ሄክታር ወደ 481659 ሄክታር ያድጋል :: የዘመናዊ እርሻ መስፋፋት የኃይለ ሥላሴ መንግሥት በሰጠው አትኩሮት መሠረትና በወሰዳቸው አመቺ ፖሊሲዎች እንደነበር ግልጽ ነው :: ይሁን እንጂ ይህ የዘመናዊ እርሻ መስፋፋት ሀገሪቱ ከዚህ ቀደም ከነበረት አነስተኛ ቴክኖሎጂ ጋር ሲወዳደር በጣም ዘመናዊ ስለነበርና በጥቂት ሠራተኞች የሚንቀሳቀስ /Capital intensive / ስለነበር ብዙ ድሃ ገበሬዎችን ከቦታቸው አፈናቀለ፣ በጣም ጥቂቶች ደግሞ እዚያው በጣም በአነስተኛ ደመወዝ ሲቀጠሩ፣ ሌሎች ደግሞ ወደ ከተሞች በመፈለስ የሥራ አጡን ሰፈር እንዲያጥለቀልቁትና በባሰ ድህነት ውስጥ እንዲኖሩ ተገደዱ :: ለምሳሌ ይህ ዘመናዊ እርሻ በተስፋፋባቸው አካባቢዎች በወላይታ አካባቢ ከ500 እስከ 550 የሚሆኑ የገበሬ ቤተሰቦች ሲነቀሉ፣ በጭላሎ አካባቢ፣ ይህ የእርሻ መስክ በተስፋፋ በመጀመሪያዎቹ ሰባት አመታት ውስጥ ከ2000 በላይ አራሽ ገበሬ ቤተሰቦች እንዲፈናቀሉ ተደርገዋል :: ለውጪ ገበያ ተብለው የእርሻ ምርት በተስፋፋባቸው ቦታዎች ደግሞ የመፈናቀሉ ቁጥር ከፍተኛ ነበር :: የዘመናዊ እርሻን መስፋፋት ያፋ የሀገሪቱ "ከበርቴዎች" እነዚህ እርሻዎች በተስፋፉበት አካባቢ እየመጡ ከድሃ ገበሬዎች ከፍተኛ ቀረጥ በመጠየቅ ወይንም በመንግሥት አማካይነትና በዓለም ባንክ ድጋፍ ባገኙት የገንዘብና ሌሎች ዕርዳታዎች የእርሻን መስክ በማስፋፋት ለችግሩ ምክንያት ይሆናሉ :: ይህ በእንደዚህ እንዳለ አነስተኛ ገበሬዎችን ለመርዳት በሚል በ1971 ዓ.ም ኢፒድ/ EPID / የተባለው የዘር፣ የቴክኒክ [illegible]፣... ወዘተ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤት ይቋቋማል :: ሆኖም ግን ባለው ቢሮክራሲያዊ አሠራርና የመሬት ስሪት ምክንያት አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች እስከ አንድ ሄክታር መሬት ድረስ ኢፒድ ከመደበው ጠቅላላ ዕርዳታ /Inputs / ውስጥ 1.2% ብቻ እስከ 1975 ዓ.ም ይደርሳቸዋል :: የችግሩ አለመፈታት በዚህ ይገለጻል :: ግን ደግሞ ይህንን የዘመናዊ የእርሻ መስፋፋትና ከ80 % በላይ የሚሆነውን በሬው አራሽ ገበሬ የሚተዳደርበትን ከእጅ ወደ አፍ የሆነ የእርሻ መስክ / subsistence Sector / አትኩሮት አለመስጠት በእርግጥ የሀገሪቱ ዋና የፖለቲካና የኢኮኖሚ ተፅዕኖ ነጸብራቅ በሆነም፣ ከቲዎሪ አንጻር መመልከትና

የውጪ ተጽዕኖና ጫና እንዲሁም ርዕዮተዓለም ምን ያህል በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በአጠቃላይና፣ በተለይም በአርሻ ላይ እንደነበራቸው መረዳት ያሻል ።

ካፒታሊዝም ዓለም አቀፋዊ መልክ ሲይዝና እየሰፋና እያደገ ሲመጣ የበስተኛውን ዓለም ሀገሮች ይበልጥ በቀጥተኛ ስር ለማዋል ለአርሱ በሚስማማ መልክ ኢኮኖሚ ቲዎሪዎችንም እንዲፈጠሩና እንዲስፋፉ ቀደም ብሎ ተገልጿል ። ይህ "የዕድገት ቲዎሪ" / Development theory / በመባል የሚታወቀው ከየሀገሩ ባሕል፣ ታሪክ፣ የሀብት ሁኔታና ክፍፍል አንጻር፣ እንዲሁም የኢኮኖሚ ተጨ የተነደፈ ባይሆን፣ ለዚህ ተብለው በሰለጠኑ " ኤክስፐርቶች " ርዕዮተዓለማዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጽዕኖን ለማስፋፋት ተብሎ የተቋቋመ ኢንስቲቱት ነው ። በአጠቃላይ በዚህ ቲዎሪ መሠረት፣ እነዚህ ወደ ኋላ የቀሩ የበስተኛው ዓለም ሀገሮች አሁን የካፒታሊስት ሀገሮች የደረሱበት ደረጃ ሊደርሱ የሚችሉት፣ በእነሱ ዕርዳታ አማካይነት በየሀገሩ አንዱ አካባቢ ላይ ዘመናዊ እርሻዎች፣ ወይንም ኢንዱስትሪዎች ከተቋቋሙና የእርሻ ምርቱ ወደ ውጪ ከአተኮረ /Export orentied / ይህ ዘመናዊ የእርሻ መስክ እያደገና እየተስፋፋ ሲሄድ ቀስ በቀስ ወደ ኋላ የቀሩ የኢኮኖሚ ሴክተሮች ወይንም አካባቢዎች በዚህ በዘመናዊ መስክ እየጎተተ እነሱም ያድጋሉ፣ ይስፋፋሉ ። ዘመናዊ ይሆናሉ የሚል ነው ።

እንግዲህ በኢትዮጵያም የደረሰውና የተደረገው ከዚህ የተለየ አይደለም ። ውጤቱ ግን ይህ ቲዎሪ እንደሚለው ባይሆን አሉታዊ የሆነና በሀገሪቱ ውስጥ ያልተስተካከለ ዕድገት እንዲኖር መንገድ የጠረገ፣ ከላይ እንደተመለከተው በዙ ዱን ገበሬዎች ከመሬታቸው እየተፈናቀሉ የባሰ ድኅነት ውስጥ እንዲገቡ የተደረገበት፣ ሀገሪቱ በውጪ ገበያ በጥቂት የእርሻ ምርቶች ላይ ብቻ እንድታተኩር የተገደደችበት፣ እርስ በእርሱ የተያያዘ ኢኮኖሚ እንዳትገነባ የታገደችበት፣ ዓለም አቀፍ ካፒታሊዝም የሥራ ክፍፍል ውስጥ ይበልጥ የተገፈተረችበትና ጥገኛ እየሆነች የመጣችበት ነው ። በተጨማሪም የሀገሪቱ ሕዝብ የምግብ ፍላጎት እንዳይሟላ የተደረገበት፣ሰፊው ሕዝብ ካለው የኢኮኖሚ ሥርዓት ጋር ተደምሮ ለረሐብ፣ ለድኅነት የተጋለጠበት የኢኮኖሚና የእርሻ ፖሊሲ ነው ። የዚህ ውጤት በሀገሪቱ ውስጥ ቅራኔዎች እያደጉ እንዲመጡ አደረገ ። ለየካቲቱ አብዮት መፈንዳትና ለኃይለ ሥላሴ መባረር አስተዋጽኦ አበረከተ ።



## 4.5 <u>የቡና ሚና በኢትዮጵያ</u>

ስለኢኮኖሚ ፖሊሲና ስለእርሻ ፖሊሲ እንዲሁም የውጪ ሀገሮችንና የኢኮኖሚ ፖሊሲ በሀገራችን ላይ ያለውን ተጽዕኖ ካነሳን ዘንድ፣ ኢትዮጵያ ወደ ውጪ ከምትልከው 60% ን የሚይዘው ቡና ስለሆነ የቡናን ታሪካዊ አመጣጥና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ያለውን ትርጉም ማየትና መመርመር ያስፈልጋል ። የቡና የኋላ ኋላ በሀገራችን መስፋፋትና ለውጪ ገበያ ከሚቀርበው አብዛኛውን መያዝ ቀደም ብለን ከተቸነው የዕድገት ቲዎሪ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ይህንን እንደገና በሌላ የአቀራረብ መልክ መመልከቱ የዚህን "ቲዎሪ " ምንነትና ተጽዕኖ መረዳት ያስችለናል ።በዚህ ቲዎሪ አንዱ ክፍል መሠረት፣ እያንዳንዱ ሀገር ባለው ሀብት ላይ፣ የሰው ጉልበት፣ክህሎት፣ የሰው ጉልበት በመጠቀም፣ " ካፒታል " ከሆነ ካፒታል በመጠቀም ቢሰለጥንና በዓለም የንግድ ልውውጥ ውስጥ ቢካፈል ይህ የሥራ ክፍፍልና የንግድ ልውውጥ በየሀገሮች ዕድገትን ብሎም ለሕዝባቸው ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን ያመጣል ይላል ። ይህ ቲዎሪ ኢኮኖሚያዊ መዛባት በሌለበት፣ ሀገሮች በእኩል ደረጃ በሚቀርቡበት ሊሠራ ይችላል ።ግን አሁን ባለው የዓለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊ መዛባት፣ካፒታል የበስተኛውን ዓለም ሀገሮች በተለያዩ መስኮች በተበተበበት ዘመን እንደምናየው ለሕዝቦች ዕድገትን ባይሆን ጉዳትና ድኅነትን የሚያመጣ ነው ። እንግዲህ ቲዎሪው በሥራ ላይ ይውል ዘንድ ጣዒታ እኩልነት / equal partnership / እንዲሰፍን ያስፈልጋል ። ይህ ቲዎሪ የሚነሳው ከይሆናል እንጂ ተጨባጭ ሁኔታዎችን በማጤንና ሌሎች የፖለቲካ ሁኔታዎችን በመገምገም አይደለም ። የየሀገሩ ኢኮኖሚና ኃይሎችና መዋቅር የእነዚህ ዳይናሚክነት ባይሆን ለአንዱ ሀገር ዕድገትን የሚያመጣው፣ የዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍልና በዚህ መስክ ውስጥ መግባት ብቻ ነው ። ከዚህ በተረፈ የተለያዩ ሀገሮች ለምሳሌ ያህል አምስት ወይንም ከዚያ በላይ አንዱን ዓይነት ምርት የሚያቀርቡና በእነርሱ መሀከል ውድድር እንዳለ ይህ ቲዎሪ አያጤንም ። አሁን ባለው መዛባት አንዱ በአንዱ የካፒታሊስት ሀገር ማትኮሩ እንደሚሆንና መስመሩን የቀየረ ሁሉ ተጽዕኖ የሚደርስበት መሆኑን፣ ይህ ቲዎሪ እንዲሁ ተስፋፍቶ እነዚህን "ኢለመንቶች" / Constraints / በቲዎሪ ውስጥ አላገባም ። እንግዲህ በአጠቃላይ በበስተኛው ዓለም የሚካሄደውን ፖሊሲ ስንመለከትና ከዚህ ቀደም ብሎ በ4.4 ውስጥ በተነሳውና በተቸነው ቲዎሪና በዚህም ላይ በመመስረት ውጤቱ ምን እንደሆነ አመልክተናል ። አሁን ደግሞ ቡና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን ሚና ከኢኮኖሚክስ አንጻር / Economstic Approach / ለማሳየት እንሞክራለን ።

ስለኢትዮጵያ ታሪክ የጻፉ አንዳንድ የውጪ ሀገር ሰዎች ቡና በኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የበቀለና ይህም ወፍ ዘራሽ በሆነ መልክ የተስፋፋ መሆኑን ይናገራሉ :: ይሁን እንጂ የቡና ተክልና ጥቅም የታወቀው በ19ነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ እንደሆነ ይታወቃል :: እስከዚህኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ግን የቡናን ተክል መስፋፋትና መጠጥ " የእስላሞች መጠጥ" ነው በሚል ቤተክርስቲያን ተቃውሞዋን ታሰማ እንደነበር ግልጽ ነው :: ነገር ግን ይህ አስተያየት በዘመኑ በነበረው አገዛዝ ተቀባይነት ባለማግኘቱና የቡና ተክልም ጥቅም በመታወቁ እንዲስፋፋ ይደረጋል ::

የዛሬይቱ ኢትዮጵያ በአንድ አገዛዝ ስር ስትወድቅ የዚህ አማካይ መንግሥትም አስተያየትና አመለካከት ይለወጣል :: በጊዜው የተመሠረተውና ቀስ በቀስ እያደገ የመጣው የገዥ መደብ በአውሮፓ ካፒታሊስቶች አማካይነት ወደ ሀገራችን በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ይማረካል :: የአውሮፓ ካፒታሊስቶች ደግሞ ዕቃ ብቻ በሀገራችን ገበያ ላይ አምጥቶ መሸጥ በቂ አለመሆኑን ሲረዱ ከፍተኛ ትርፍ ወደሚያካብቱበት በአንዳንድ መስኮች ላይ እንደ ሀዲድ መዘርጋት በመሳሰሉት ተግባሮች ላይ በመሠማራት ሀገሪቱን ይበልጥ የሚበዘብዙበትን መንገድ ያዘጋጃሉ :: መንገዶችና ሀዲዶች የቡና ምርት ተመርቶ ወደ ወደቦች በቀላሉ ሊተላለፍ ወደሚችልበት አካባቢ ይዘረጋሉ ::እስከዚህ ጊዜ ድረስ ወይንም ቡና ለውጪ ገበያ የሚቀርብ ሆኖ የመጀመሪያውን ቦታ እስኪይዝ ድረስ የዝሆን ጥርስ ዋናው ኢትዮጵያ ለውጭ ገበያ የምታቀርበው ምርት እንደነበር ይታወቃል :: የቡና ጥቅም እየጎላ ሲሄድና ብዙ ዝሆኖች እየተገደሉ ሲያልቁ፣ የዝሆን ጥርስ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ትርጉሙን እየቀነሰ ይመጣል :: የቡና ምርት ለዓለም ገበያ መቅረብ በኢጣሊያንና በኢትዮጵያ ጦርነት ወቅት / ከ1935 እስከ 1941 እንደ እ.አ / ለጊዜው ቢገታም ከጦርነቱ በኃላ የኢትዮጵያ የውጪ ገበያ በዚህ ላይ እንዲያተኩር የአውሮፓ ካፒታሊስቶች ሀገራችንን ማስገደድ / በኃይል ባይሆን /ችለዋል :: ከጣሊያን ወረራ በኃላ እስከ ዛሬ ድረስ የቡና ተክል እየተስፋፋ የመጣና ከሌሎች ለዓለም ገበያ ሊቀርቡ በሚችሉ ምርቶች የተተካ ወይንም ሚናው የቀነሰ አይደለም :: ዛሬ ቡና 80.000 ሺህ ሄክታር በሆነ መሬት ላይ ተስፋፍቶ ይገኛል :: ሀገሪቱ ውስጥ ከሚመረቱት ምርቶች / GDP / 8 % የሚሆነውን የሚይዘው ቡና ነው :: እስከዚህ ድረስ ታሪካዊ አመጣጡ ::



የአንድ ምርት ጥቅም ይልቁንስ ሊታወቅ የሚችለውና ኢኮኖሚያዊ ትርጉም የሚኖረው የውጪ ና መገበያያ ብቻ ባይሆን ይህ ሰብል ወይንም የኢኮኖሚ ዘርፍ ከሌሎች አንድ ሀገር ከምታመርታቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች፣ ለምሳሌ ከኢንዱስትሪ ከእርሻ መስኮች ጋር፣ ከአገልግሎት ጋር ግኙነት ሲኖረውና ለዚያ ሀገር ገበያ ማደግ፣ መስፋፋት በሙሉ ለጠቅላላው ኢኮኖሚ መዳበር አስተዋጽኦ ሲያደርግ ብቻ ነው :: በዚህም መሠረት ቡና ከሌሎች መስኮች ጋር ያለውን ግንኙነት መመርመር መመልከት ያስፈልጋል ::

የቡና ምርት መስፋፋት ና ለውጪ ገበያ ከሚቀርበው ውስጥ 60% ቢይዝ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መስፋፋትና ማደግ ያለው ትርጉም በጣም ዝቅተኛ ነው ማለት ይቻላል :: ከላይ እንደተጠቀሰው አንድ የኢኮኖሚ ዘርፍ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር መያያዝ እንዳለበት ነው :: በዚህም አንጻር ቡና ከሌሎች ኢንዱስትሪ መስኮች ጋር በጥብቅ የተያያዘና የንግድ ልውውጥ የሚደረግበት ዘርፍ አይደለም :: ቡና በሀገራችን ውስጥ መጀመሪያ ጊዜ ወፍ ዘራሽ ተክል እንደ መሆኑ መጠን ምንም እንኳ የጋሳ ጋሳ ቢስፋፋም ቀሉ፣ ሀገሪቱ ውስጥ ካሉት ለቡና ተክላ፣ ምንጣሬ፣ መኮትኮቻ፣ ለቀማ... ወዘተ የሚያስፈልጉት መሣሪያዎች ወይንም ይህንን ከሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች ጋር የተያያዙና እነዚህ ለዚህ ተግባር ተብለው በቡና ተከላ በየጊዜው የሚገዙ አይደሉም :: ይልቁንስ የቡና ተክላ በቀላል ፣ በእጅ በተሠሩ፣ ለምሳሌ በገጀሬ፣ በመቆፈሪያ ... ወዘተ ሊተከልና ሊዳበር የሚችል ነው :: ይህም ማለት የቡና ተክላ በዘመናዊ ና በትላልቅ መሣሪያዎች ሊስፋፋ የሚችል ባይሆን፣ የሚያስፈልጉት ቀላል መሣሪያዎችና እነዚህን መሣሪያዎች ደግሞ ሰው ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ሊጠቀምባቸው የሚችልባቸው ናቸው :: በእነዚህ መሀከል በቡናና በሌሎች ኢንዱስትሪዎች መሀከል ሊኖር የሚገባው የንግድ ልውውጥ፣ ለምሳሌ በየጊዜው የምርት መሣሪያዎችን መግዛት፣ እነዚህ የምርት መሣሪያዎች ደግሞ እያደገ በሚሄደው ጥያቄ / Demands / መሠረት የሚመረቱ ከሆነ፣ ይህ ዘርፍ ምርቱን ለማሳደግ በበዛት ሠራተኞችን ይቀጥራል ማለት ነው :: ኢንዱስትሪውን ያሻሽላል :: የምርት መሣሪያውንም የተሻለ እያደረገ ለጠያቂው ያቀርባል ማለት ነው :: በዚህ መሠረት የንግድ ልውውጡ ሲዳበር በሌላ የኢኮኖሚ ዘርፍ ላይ አዎንታዊ / posetive effect / ይኖረዋል :: ቡና ግን በዚህ የተካነ አይደለም ::

ከዚህ በላይ ደግሞ፣ ቡና ተለቅሞ ፣ ደርቆ፣ ተፈልፍሎ እዚያው ሀገሪቱ ውስጥ እየተፈጨና እየታሸገ ለሀገሪቱ ገበያ የሚቀርብ አይደለም ። በዚህም ረገድ ለሀገሪቱ ገበያ መስፋፋትና ማደግ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ አልቦ ነው ማለት ይቻላል ። ቡና ተለቅሞ ሀገሪቱ ውስጥ ቢደርቅ፣ ቢፈለፈልና ቢቆሸር በኢንዱስትሪ ውስጥ አይፈጭም ። 95 % የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቡናን የሚወቅጠው በቀላል ከእንጨት በተሠራ ሙቀጫና ዘነዘና ነው ። እነዚህ ደግሞ በቀላል የእጅ ሥራዎች ስለሚሠሩና እንደዚሁ ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ ስለሆነ ለሀገሪቱ ገበያ መስፋፋት እስከዚህ ድረስ ትርጉም የላቸውም ። ለምሳሌ ቡና ሀገሪቱ ውስጥ ቢፈጭ፣ የሚፈጨው ኢንዱስትሪ የግዴታ ሠራተኞች ይቀጥራል ። እነዚህ ሠራተኞች ገቢ ሲያገኙ የመግዛት ኃይል አገኙ ማለት ነው ። እንደዚሁ ኢንዱስትሪው እራሱ ቡናውን የሚጠቀልልባቸውን ወረቀቶች ወይንም ካርቶኖች እራሱ ስለማያመርት ሌሎች ይህንን ከሚሠሩ እየገዛ፣በሁለቱ መሀከል የንግድ ልውውጥ ቢደረግ ሁለቱም የኢንዱስትሪ ዘርፎች ያድጋሉ ። ያበባሉ፤ በሎም ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ መዳበርና መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ማለት ነው ።

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የቡና ተክልና መስፋፋት፣ የሚለቀምበት ጊዜ፣ ደርቆ በሚፈለፈልበትና ቀሽሽው የሚጣራበት ወቅት፣ ከዚያም ከአንዱ ቦታ ወደ አንዱ ቦታ ትራንስፖርት የሚደረግበት ወቅት አንዱ የተወሰነ ጊዜ / seasonal / በመሆኑ በዚህ ወቅት ተቀጥረው ለሚሠሩ ይህንን ያህልም የገቢ ምንጭ አያስገኝም ። በቡና ለቀማ ሰዓት ተቀጥረው ገንዘብ አገኝተው ወደ እየአካባቢያቸው ሄደው እንደገና ኑሮአቸውን ለመቀጠል የሚፈልጉት በቀን የሚያገኙት ገቢ ከአንዱ ገፋ ቢል ሁለት የኢትዮጵያ ብር ብቻ በመሆኑ፣ በገበያ ላይ የሚቀርቡትን የኢንዱስትሪ ምርቶች ገዝተው ለመጠቀም / consume / የሚችሉ አይደሉም ። በዚህም፣ እነሱ በሚያገኙት ገቢ በጣም ለኑሮአቸው ከሚያስፈልጋቸው ነገሮች ፣ ለምሳሌ ለቂጣ የሚሆን የበቆሎ ዱቄት፣ አንዳንዱ ጊዜ ደግሞ ሌሎች ጥራጥሬዎችን ከመግዛት በስተቀር ሌሎች ነገሮችን ለመግዛት አይችሉም ። ቡና ተክሉንም የወሰዱን እንደሆነ፣ አብዛኛው ባላባት ስለሆነና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ገዝቶ የሚጠቀም ስላልሆነ፣ — መሬት ይገዛል፣ ቡና ይተክላል፣ ዱግስ ይደገባል — ገቢው ከፍ ያለ ቢሆንም ለሀገሪቱ ገበያ መዳበር



ያለው አስተዋጽኦ በጣም ዝቅተኛ ነው ። እንግዲህ የቡና ሚና በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ትርጉም በጣም ዝቅተኛ ነው ።

ወደ ውጪ የሚላከውን ደግሞ እንመልከት ። ኢትዮጵያ ለዓለም ገበያ የምታቀርበው የቡና መጠን በዓመት ከ70.000 እስከ 80.000 ቶን ብቻ ነው ። እንደሌሎች የእርሻ ምርቶች የቡና ዋጋ በዓለም ገበያ በየጊዜው ዝቅና ከፍ ስለሚል ከዚያ የሚገኘው ገቢ አስተማማኝ አይደለም ። ይህም ሆኖ፣ የሚገኘው ገቢ በኃይለ ሥላሴ ጊዜ ለቅንጦት ዕቃዎች ማስመጪያ የሚውል፣ ዛሬ ደግሞ ለመሣሪያ ዕዳ መክፈያና እንደዚሁ ለቅንጦት ዕቃዎች የሚውል እንጂ ለሀገሪቱ ዕድገት ለሚውሉ የምርት መሣሪያዎች መግዣና የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ የሚውል አይደለም ። የቡና ሚና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ትርጉም እስከዚህም አለመሆኑ " እየታወቀ " የዘረው አገዛዝ የቡና ተከላ እንዲስፋፋ እያደረገ ነው ። ለዚህም ከዓለም ባንክ ብድር 31 ሚሊዮን ዶላር አገኝቷል ። ይህ ሁኔታ ሀገሪቱን የባሰ የውጪ ካፒታል ጥገኛ የሚያደርጋትና ለውጪ ከበርቴዎች የምትከፍለው ዕዳ እየጨመረና እያደገ ሲሄድ፣ ሀገሪቱ የግዴታ ለውጪ ገበያ በሚቀርቡ የእርሻ ምርቶች /Cash Crops / ላይ " ጠንካራ ገንዘብ " ለማግኘት በሚል የበለጠ መሰማራት አለባት ። ነገሩ የዙሪያ ጥምጥም ይሆናል ማለት ነው ። እንግዲህ እስከዚህ ድረስ ነው የቡና ትርጉም በኢትዮጵያ ።

ይህንን ስናቀርብ ግን ሀገሪቱ በፍጹም በቡና ተክል ላይ አትሰማራ ለማለት አይደለም ። ወይንም ደግሞ ሕዝቡ የለመደውን የአኗኗር ዘዴ ቶሎ ይተው ለማለት አይደለም ። — ለምሳሌ ቡና ቤት ቆልቶ እራስ ወቅቶ መጠጣት — ይልቁንስ ይህ የቀረበው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የቡናን ትርጉም በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ እንዲረዳውና ሀቀኛና ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ሲመጣ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማዳበር ከውጪ ካፒታል ቀስ በቀስ መላቀቅ እንዳለበት ለማመልከት ሲሆን፣ ይህንን ካላደረገ ወይንም በአንዱ ሰብል ላይ ብቻ ካተኮረ በምንም ዓይነት ጠንካራ ኢኮኖሚ አስገኝቶ የሕዝቡን ኑሮ ለማሻሻል አይችልም ። አሁን ግን መቶ በመቶ መናገር የሚቻለው ደርግ ይህንን ማድረግ አይችልም ። መደቡ ፣ ጠባዩ ፣ ፖለቲካው እንዲሁም ነፃት ኅሊናው አይፈቅዱለትም ።

## 5.0 በአብዮቱ ጊዜና ወዲህ

ባለፉት ገጾች ውስጥ የኃይለ ሥላሴ አገዛዝ፣ ሥርዐቱና ከዚህ የፈለቀው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዕድገት ወደ ኋላ መቅረት፣ ለድኅነት በሙሉ ለረሀቡ ዋና ምክንያትና ተጠያቂ እንደሆነ አመልክተናል ። ፖለቲካ ወባኝ እንደመሆኑ መጠን ሀገሪቱ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ የተያያዘችበት የኢኮኖሚ ሥርዐትና ከዚህ የፈለቀው ፖለቲካ ምን ያህል በኃይለ ሥላሴ አስተባባሪነት አድኃሪ ኃይሎች ተሳስረው ይህ ከውጪ ሀገር ከሚያገኙ ፖሊሲና ድጋፍ ጋር ተዳምሮ ሀገራችንን ወደ ጥፋት፣ ወደ ባሰ ድኅነት ለማምራት እንዳበቃት ተመልክተናል ።

በዚህ ቸኛዋ አጭር ክፍል ውስጥ ደግሞ የዛሬው አገዛዝና መንግሥት መቅቀር ለምን ለዛሬው ረሀብ፣ ለዛሬው በሰውና ከብት ዕልቂት ለሀገራችን ጥፋት ዋና ተጠያቂ ለመሆን እንደሚችል እናመለክታለን ። ይህንን ከማድረጋችን በፊት ግን እስቲ ደርግ ሥልጣን ለመጨበጥ ሲያቆበቁብና ከጨበጠ ብኋላ በወቅቱ ይጠቀምባቸው የነበረውን ዘዴዎች እንመልከት ።

ደርግ ሥልጣን ሊይዝ ውር ውር ሲልና በእርግጥም በዚያን ጊዜ "የተወሰነ" የሀገር ፍቅር ስሜት ቢኖርም፤ የኃይለሥላሴ መንግሥት የፈጸመው በደል በአንዱ በኩል የኃይለ ሥላሴ ወሾች በብር ባሕን ላይ ሥጋ እየቆረበሳቸው ሲመገቡ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የወሎ ሕዝብ በረሀብ አለንጋ እየተገረፈ ሥጋው አልቆ፣ አጥንቱ ወጥቶ መሄዱ ሲያቅተውና፣ ሌላው ደግሞ በሞት ሲረገፍ ለሕዝቡ አያሳየ፣ ረሀብን የሚወጋ ኃይል መስሎ ከተፍ አለ ። በተጨማሪ የኃይለሥላሴን ሹማምንት የሚያደርጉትን አጥተው በነበራቸው ሥልጣንና ከሕዝብ በዘረፉት ሀብት እየተመኩ እራሳቸውን ልዩ ፍጡር አድርገው / The arrogance of power / እነርሱ ሲንደላቀቁ፣ ሕዝቡ በረሀብ ሲገረፍ ሲያልቅ ነው ። ይህንን ሁሉ በደል በዐይኑ ያየው የከተማው ሕዝብ በስሜትና በጸጸት እየተገፋ በኃይለ ሥላሴ አገዛዝ ላይ ያለውን ጥላቻ በገልጸ አሳየ ። ያ የማይወድቅ የማይነኩታኮት አገዛዝ ከፍጡሮች በላይ አድርጎ እራሱን ይቆጥር የነበረው በአጭር ጊዜያት ውስጥ ተፈረካከሰ ። ሕዝቡ ወደ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ ገባ፤ ወደ በልጽግናና ወደ ነጻነት የሚያመሩት መንገዶች ተከፈቱለት ።



ከኃይለሥላሴ ሥልጣን መባረር፣ ከጥቂት ገበሬአበሮች መሬቱን ከጨማሪ፣ የኢትዮጵያ ተማሪዎች፣ ሀገር ወዳዶችና ዲሞክራቶች የነበረው የረጅም ጊዜ ትግል "መሬት ለአራሹ" በየካቲት ወር 1975 ዓ.ም ሲታወጅ፣ በተለይም የኢትዮጵያ ገበሬ ከኢኮኖሚ አንጻር ብቻ ባይሆን ከማኅበራዊና ሳይኮሎጂካል ጎኑ ጋር ተደምሮ ትልቅ ድል እንደተቀዳጀ ገልጾ ነው ። በአራሹ ላይ የበለጠ እምነት አሳደረ ። የዚያን ጊዜ በእርግጥም ሰው መሆኑና ሌሎች ይበዘብዙት፣ ያስቃዩትና ፍዳውን ያሳዩት የነበሩት መተረማመስ፣ መፈረካከስና መበታተን እንደሚችሉና ያ ፍዳ ያየበት ዘመን ከጨባጭ / reality / በኅኑም፣ ተፈጥሮአዊ እንዳልሆነች መረዳት ቻለ ። እነኚህ የኃይለሥላሴ ከዙፋን መውረድ መሬት ለአራሹ መታወጅ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ያመጡት አዎንታዊ ውጤት በኢኮኖሚ-ለጊዜውም ቢሆን - መልካቸው ብቻ ባይሆን በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ ግንኙነት በኅሊናዊ አስተሳሰብ፣ በርዕዮተዓለማዊ ጎኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የሚይዙ ናቸው ። ነገር ግን ይህ ሁሉ ሆኖ ለሀገሪቱ ዕድገት ኃላፊነት ዋናው ምክንያት የኃይለሥላሴ አገዛዝና የእሱ መሠረት የነበረው የመሬት ይዞታ ተናግተውና ተሽረው ሀገራችን እንዴት ከዚያ በኋላ ተደጋጋሚ ረሀብ ሊደርስባት ቻለ? ሕዝቡ እንዴት ዛሬ ወደባሰ ድኅነት ውስጥ ሊወድቅ ቻለ? እስቲ የነዚህን ምክንያቶችና የዛሬውን አገዛዝ ፖሊሲ እንመልከት ።

### 5.1 የመሬት ለአራሹ መታወጅ

ማኅበራችን፣ ሌሎች ድርጅቶችና በጊዜው ለደረሰው ረሀብ ተቆርቋሪ የነበሩ፣ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ኋላቀርነት የነበረውን የመሬት ስሪት ተጠያቂ አድርገው የተመለከቱት ገለሰብ ጋዜጠኞችና ፀሐፊዎች የመሬት ለአራሹ መታወጅ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ፣ በሕዝቡ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ከፍተኛ መሻሻልን እንደሚያስከትል ጽፈዋል ። ስምምነትም ነበር ። ዛሬም ቢሆን ማኅበራችን የዚህን የመሬት ለአራሹን መታወጅና ታሪካዊነት ለሀገሪቱም ዕድገት በር የከፈተና ወደፊትም የሱ በትክክል ሥራ ላይ መዋል ብቻ ሀገሪቱን እንደሚያራምዳት ይገነዘባል ። ሆኖም ግን ተስፋ የተጣለበት አዋጅ ከአስር ዓመታት - ይህ ጽሑፍ ሲጻፍ ልክ አስር ዓመት ሆነው — በኋላ ለምን ረሀብና ድኅነት የገብረተሰብአችን መለያ ሆኑ? ለምን ኢኮኖሚያዊ መሻሻል አልመጣም?..

የመሬት አዋጅ ከታወጀ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ይህንን በሥራ ላይ ለማዋል ፣ ሕዝቡን ለማስተማር ብዙ ተማሪዎችና አስተማሪዎች እንደተሰማሩ ገልጸ ነው ። እነዚህ

ተማሪዎችና አስተማሪዎች ካሰበዙ መሰናዶ፣ ሬሳቸውን ለመጠበቅ የሚያስችላቸው አስፈላጊ አርምጃዎች ባይወሰዱና ዝግጅት ባይደረግ በገጠር ተሰማርተው ሕይወ ታቸውን አየሰው ያደረጉት አስተዋጽኦ በጣም ከፍተኛ ነው ። በአጭር ጊዜያት ውስጥ ሕዝቡን በማስተማር ገበሬውን በማኅበር በማደራጀት የተደረገው ሥራ በታ ሪክ ውስጥ ተመዝግቦ ለዘለዓለም የሚኖር ነው ። የመሬት አዋጁ ከታወጀ በኋላ ገበሬው መሬት የራሱ መሆኑን ሲረዳና ሲደሰት የበለጠ ማረስ — ከዚያ በፊት ይሰራው ነበር ለማለት አይደለም — ፍላጎቱ እየጨመረ እንደመጣና በ1975/76 ዓ.ም ውስጥ የእርሻ ምርት ከዚያ በፊት ከነበረው ዝቅተኛ ሁኔታ ጋር ሲወዳደር አንዳደገ የውጪ ሀገር ጸሐፊዎችና የዓለም ባንክ ያምናሉ ። በዚያን ጊዜ፣ አንዳ ንዶች የእርሻ ምርት በየዓመቱ ከ5–10 ያድግ ነበር ይላሉ ። ሌሎች ደግሞ ከ10 እስከ 20 አንዳደገ ያመለክታሉ ።

> The radical nature of changes in the agricaltural sector initiated by the PMAC spurred predictions of dire for food production in Ethiopia. Nevertheless, the 1975 harvest turned out to be well above average.... Food production in 1975/76 surpassed the previous years level by between 10 and 20% ... and there are indications that the production of cereals and some other agricultral goods either remained constant or increased from 1976-1977.
>
> ( P. Kohen; Ethiopia: Famine, food production, and changes in the legel order, in African studies Review.( East Lansing), xx. 1. 1979, p.51-71. Coted in the Journal of Modern African Studies. 1980)

ይህ የእርሻ ምርት ማደግ ለጊዜውም ቢሆን በዚያው መልክ ሊቀጥል አልቻለም ። በዚያን ጊዜ ምርት ቢያድግ ከመሬት አዋጁ መታወጅና በጊዜ ከነበረው የተወሰነ ነጻ ነት አንጻር የሚታይ እንጂ የገበሬው የአስተራረስ ዘዴ ተሻሽሎ፣ የተሻሉ የምርት መሣ



ሪያዎች ተዘጋጅተውለትና ተርበውለት አልነበረም ። በእርግጥ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይህንን ሁኔታ መለወጥና ማሻሻል ይቸገራል ። ይሁን እንጂ ዓመታት እያለፉ ሲሄዱ ደግሞ፣ እርሻ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አምርት እንደመሆኑ መጠን ለሠራ የሚችሉና በሥራ ላይ መዋል ያለባቸው የምርት ሁኔታ የሚያሻሽሉና ዕድገትን የሚጠምሩ ሁኔታዎች በፍ ጥም አልተፈጠሩም ። ይህን ስንል ምን ማለታችን ነው? በእርግጥ ሀገሪቱ ባለቸበት የኢኮኖሚ ሁኔታ ከውጪ ትራክተር፣ ማዳበሪያ፣ የእረም ማጥፊያ... ወዘተ የመሳሰሉትን አስመጥታ ለገበሬው ልታድል አትችልም ። እንዲያውም ከእውነተኛ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ዕድገት አንጻር፣ ከሀገሪቱ የአር ጠባይና የመሬት ሁኔታ አንጻር ከሕዝቡ ባህላዊ አኗኗር አንጻር ይህ ዕድገትንባይሆን ወደ ሌላ ችግርና ጥገኝነት ውስጥ የሚከት ይሆ ናል ። ሀገራችን ትራክተር ባስመጣች ቁጥር፣ ለዚህ ሥራ ሰዎችን ማሰልጠን ያስፈልጋ ታል፣ ትራክተሩ ሲበላሽ መጠገን ያስፈልጋል፣ ለመጠገኛ ቡሎኖች ያስፈልጋሉ ። ትራክተሩ በሀገራችን ውስጥ የማይመረት በመሆኑ የግዴታ ትራክተሩ ከመጡበት ሀገር በየጊዜው የመጠገኛ መለዋወጫዎች ማስመጣት አለብን ። በዚህም ለዕድገት የሚረዳንን ገንዘብ በተ ወሰነ ነገር ላይ ብቻ አዋልነው ማለት ነው ። ይህ የመለዋወጫ ዕቃ ከውጪ ታዝ እስኪ መጣ ድረስ ብዙ ጊዜ ይፈጃል ። ከዚህ ሁሉ ገን፣ ያ ብዙ የሰው ጉልበት በተከማቸበት ሀገር በዚህ የዘመናዊ ማረሻ /capital intensive / አማካይነት በሥራ ላይ እንዳይሠማራ ሊያገደው ይችላል ። የእኛንም ቀስ በቀስ የመፍጠርና በአረሳችን ዕውቀትና ችሎታ የመተማመንን ሁኔታና ለሀገራችን የሚስማማ የተመና ምርት እንዳናመርት ያግደ ናል ።

እንግዲህ ትራክተር ሰፋፊና ከዚህ በፊት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በነበሩት እርሻዎች ላይ መሰማራት ቢያስፈልግ፣ ከ80–90% ለሆነው አራሽ ገበሬ ሊቀርብ የሚ ችለው የምርት መሣሪያ በሀገሪቱ ውስጥ መመረት ያለበትና ቀላል የሆነ ማንኛውም ገበሬ ሊጠቀምበት የሚችልና ዕድገቱን ጠብቆ መጓዝ መሆን አለበት ። ይህ ምን ማለት ነው? ይህንን ቴክኒካል ጎኑን ብቻ መመልከት በቂ አይደለም ። ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ጎኑንም አንዱ ላይ አጣምሮ መመልከት ያሻል ። በሀገሪቱ ውስጥ የአካሬና የደጋ ፋብሪካ አለ ። በዚህ ፋብሪካ ውስጥም ሆነ በእጅ ጥበብ ሠሪዎች ወገልም ሆነ ሌሎች የምርት መሣሪያዎች ይሠራሉ ። በተጨማሪም ቀላል የብረታ ብረት ፋብሪካዎች አሉ ። እንደሚታወቀው 90%

የሚሆነው የኢትዮጵያ ገበሬ መሬትን ለማረስ የሚጠቀመው በአንድ ማረሻ / አንድ መውጊያ ያለውን/ ወይንም ወገል ነው ። አንድ ትንሽ ማሳ ለማረስና ለማገላበጥ በዚያው ማሳ ላይ ከጫፍ እስከ ጫፍ ብዙ ጊዜ መመላለስ አለበት ። ብዙ ጉልበትን፣ ብዙ ሰዓትን ይፈጅበታል ማለት ነው ። ስለዚህም በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ምን ማድረግ አለበት ? እርሻ የሀገሪቱ የደም ስር በሆነበት፣ ተደጋጋሚ ረሐብ የኅብረተሰብአችን መለያ በሆነበት ሀገር፣ ከሁሉም በፊት የምግብ ጥያቄ መፈታት ባለበት ሀገር፣ የግድ እነዚህን የእርሻ ምርት መሣሪያዎች ማሻሻል፣ እነዚህን ለማሻሻል የዕድገትን ዕቅድ በአማዘኝ ጉኑ ወደዚህ እንዲያተኩር ያስፈልጋል ማለት ነው ።ብአ ንድ ወገልና ማረሻ ፋንታ፣ በአንድ ጊዜ ተጣምረው ሊያርሱ የሚችሉ፣ ሁለት፣ሶስት.. ወዘተ መውጊያ / መቆፈሪያ / ያላቸው ማረሻዎችን ማስናዓት ያስፈልጋል ። ስለዚህም የአካፋና የዶማ ፋብሪካዎች፣ የእጅ ጥበብ ሠራተኞች፣ የብረታብረት ፋብሪካ ለዚህ ተገባር እንዲሠማሩ፣ የሠለጠኑ ሰዎችም በዚህ ላይ ጥናት እንዲያደርጉ አስፈላጊውን ዝግጅትና እርዳታ ማድረግ ያስፈልጋል ።

ይህ የላይኛው፣ የመጀመሪያውና በጣም አስፈላጊው ተገባር ሲሆን፣ ዝናብ በማ ይዘንብባቸው አካባቢዎች ወይንም በእርሻ ጊዜ በሚቀርባቸው አካባቢዎች ደግሞ ቀላል መስኖዎችን፣ ጉድጓዶችን እየቆፈሩ ገበሬው እንዲጠቀምባቸው ማድረግ ያስፈልጋል ።እን ደዚህ ዓይነቱን ዕቅድ በሁለት ዘዴዎች ማውጣት ይቻላል ። ይህ ከላይ የተጠቀሰው የቀስ በቀስና የረጅም ጊዜ ፕላን ሕዝቡን ቀስ በቀስ እራሱን እንዲችል የሚያደርጉት ሲሆኑም፣ ይህን ሥራ ላይ አያዋሉ ለአጭር ጊዜ የሚሆን ዕቅድ ማውጣት ያሻል ። በረ ሐብ አለንጋ ለረጅም ጊዜ ሲገረፍ የከረመውን፣ ጉልበቱ የደከመውን አስፈላጊውን የቴ ክኒካል ዝግጅት ቢደረግለት ቶሎ በሥራ ላይ ሊሠማራ ይችላል ማለት አይደለም ። የደከመ ጉኑ እንዲያገግም፣ እንደገና ጉልበት እንዲያበጅ የሚያስችሉት ሁኔታዎች መፈጠር አለባ ቸው ።ስለዚህም ከዚህ በፊት በመንግሥትና በግለሰብ እጅ የተያዙትና በኃላ የተወረሱት ለምግብ የሚሆኑ የእርሻ ውጤቶች እንዲመረትባቸው አስፈላጊውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል ።ይህንን ማድረግ፣ በአንድ በኩል የእርሻን ምርት ሲጨምር፣ በሌላ በኩል ሕዝቡን እየመገቡና የሀገሪቱን የምግብ ችግር እየፈታ የተራበውን ሕዝብ ከረሐቡ ተላቀና ጤናማ ሆና ለሥራ እንዲዘጋጅ ያደርጉታል ። የመጀመሪያውን የረጅም ጊዜ ደግሞ ያኔውኑ መውሰድ ያለበትን ዕቅድ የተመለከትን እንደሆነ፣ በእርሻና በኢንዱስትሪ



መስክ በሚፈጠረው የንግድ ልውውጥ የኢኮኖሚ መስኮች መተሳሰር /linkage effect/ ይፈጥራል ። በዚህም ሀገሪቱ ለኢኮኖሚ ዕድገቷ ብሎም ለሕዝቧ ኑሮ መሻሻል የሚ ሆኑትን መሠረቶች ጣለች ማለት ነው ። በማኅበራዊ ጉኑ፣ ይህ የሀገሪቱን ሀብት መጠቀም የተዛባ የኅብረተሰብ ክፍል እንዳይፈጠር ይረዳል ። በሌላ አነጋገር ትራ ክተር በመጣ ትራክተሩን የሚያንቀሳቅስ፣ የሚጠግን ... ወዘተ የሰለጠኑ ሰዎች የግድ ያስፈልጋል ። ይህ ደግሞ በቂ ንቃተ ኅሊና በሌለበት አካባቢ " በሰለጠ ኑና ባልሰለጠኑ " ሰዎች መሀከል ልዩነት ብሎም አለመግባባት እንዲፈጠር ያደርጋል ። እንገዚህ በአንድ ሀገር ውስጥ የመሬት ለአራሹ ቢታወጅ ወይንም ሪፎርም ቢደረግ የግ ዴታ የምርት መሣሪያዎች መሻሻልና ተዘጋጅተው መቅረብ ቢያስፈልጉ፣ የሕዝቡን የመፍጠር ችሎታ ለማዳበር፣ የተደበቀውና የታፈነው የሥራ ዘዴ ወደ ውጪ ወጥቶ ሕዝቡ የራሱን ችግር በእራሱ እንዲፈታ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ዲሞክራሲያዊ ነፃነቶች ያስፈልጉታል ።ካለ በለዚያ ግን " ሥጋ ሰጥቶ ቢላያ ነሱ " ነው የሚሆነው ነገሩ ።

የደርግ መንግሥት ግን ይህንን እርምጃ በፍጹም አልወሰደም ። ሊወስደም አይች ልም ።የመሬትን አዋጅ ቢያውጅ ይህንን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችሉትን ዲሞክራሲያዊ ነፃነቶችና ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች ሊያሟላ የቻለና የነቃ " የገዥ መደብ " ሊሆን አልቻለም ። መደባዊ ባሕሪውና አመጣጡ አልፈቀደለትም ። እንዲያውም ሁኔታዎችን የሚያ ባሱና አድቬንቸሪስት ፕሮግራሞችን ማውጣትና በትናንሽ ጊዜያዊ ድሎች መርካት ጀመረ ።

እረ ለመሆኑ መደባዊ ባሕሪው አልፈቀደለትም ሲባል ምን ማለት ነው ? የደርግን ታሪካዊ አረማመድ ስንመለከት ከአፈጣጠሩ ጀምሮ በሚከተላቸው ፖሊሲዎችና ፖለቲካዎች የግራና የቀኝ የሚወላገድ ነበር ። ኅብረተሰብአችንም ውስጥ የነበሩት መደባዊ ኅብረተ ሰብአዊ ኀይሎች እየተንጸባረቁበት አንድ ጊዜ ወደ አንዱ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደ ሌላው ሲያደላ የመጣ መደብ ነው ። የሀገሪቱ ፖለቲካ ኃላፊነት፣ የዲሞክራሲያዊ ባሕል ያለ መኖር ደግሞ የዚህን መደብ ውስንነትና ታሪካዊ ተገባርንና ታሪካዊ ኃላፊነትን ወሰደ ቀርቶ ባለ መገንድ ያወጣቸውን አዋጆች በሥራ ላይ ሊያውል አላስቻሉትም ። በሌላ አነጋ ገር የንዑስ ከበርቴው መደብ አንድ አካል ሲሆንም ቶሎ ቶሎ " ዕድገትንና ልማን " ሲሻም በኅብረተሰብአችን ውስጥ ካሉት ሌሎች የንዑስ ከበርቴ መደቦችና ክፍሎች፣ ማለትም

የረጅም ጊዜ የፖለቲካ ትግልና ልምድ እንዲሁም ዲሞክራሲያዊና ፖለቲካዊ ባሕል ያላቸው፣ በተጨማሪም ታሪካዊ ኃላፊነትን ለመቀበል ከሚሹት ጋር ሲተያይ የሌሉት መደቦችን መደራጀትና ከእሱ ጋር መፎካከራቸውን ይፈራል ። ደርግ ይህንን የፍርሃት ልምድ ያዳበረው ጊዜያት ሲሄዱ፣ ሕዝቡ ሲደራጅና ሲነቃ መደቦችና ድርጅቶች ከተበታተኑበት ሲተባበሩና ከኢኮኖሚ ጥቅም አልፈው በፖለቲካም መስክ ወደ መገናኘት ሲያመሩ፣ እንደ መደብ ተደራጅተው ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ሲታገሉና ሲመለከት ነው ። እነሱን ሲፈሩና እንደ መደብ ተደራጅተውና ለጥቅማቸው እንዲታገሉ ቢያገኛቸውና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ቢነፍግ፣ እሱ ራሱ ደግሞ እንደ ገዥ መደብ /State Class / ተደራጅቶ፣ በተባበረ መልኩ / coherent form / የራሱን ታሪካዊ ኃላፊነት ተገንዝቦና ተረድቶ የዕድገት አራማጅ የሆነ የገዥ መደብ ሊሆን አልቻለም ። በመሆኑም፣ መደቦች ተደራጅተው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅማቸውን እንዳያስከብሩና የመደብ ትግል እንዳይፋፋም በማድረጉ — የመደብ ትግል መፋፋም የዕድገት ሞተርና አንቀሳቃሽ ኃይል ነው — የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እንዲዳከም፣ ወዛደሩና ገበሬው የሥራ ፍላጎታቸው እንዳይዳበር በተጨባጭ አፍና ይዟቸዋል ። ይህም ሁኔታ በመደቦች የሥራ ፈጠራና ፍላጎት፣ በምርት መሣሪያዎች መዳበር ላይ ብሎም በኢኮኖሚው ዕድገት ላይና በምርት ማደግ ላይ አሉታዊ ውጤት እንዲኖረው አድርጓል ። ዛሬም የምናየው ይህንን ነው ። ይህ የደርግ ሌሎች መደቦች እንዳይደራጁ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅማቸውን እንዳያስጠብቁ፣ ወደፊት እንዳይራመዱ ማድረጉ በተለይም በገበሬው ላይ ያደረገው ዘመቻ፣ ገበሬው እንዳያብብና ምርቱን እንዳያሳድግ የፈጠረው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅፋቶች በቂ ማስረጃዎች ናቸው ። ገበሬውን " ካፒታሊስት ሊሆን ነው " የገጠሩን ካፒታሊዝም በእንጭጩ መቅጨት ያስፈልጋል እያለ ዘመቻ ያካሄድ የነበረው በተጨባጭ የዚህን መደብ መደራጀትና መፎካከር ፈርቶ ነው ።

## 5.2 ለምን የመንግሥት መዋቅሩ ለምርት አለማደግ፣ ለረሀቡ ተጠያቂ ይሆናል ?

ይህንን ሁኔታ ከደርግ አንፃር ብቻ ባይሆን—ከገዥው መደብና— ከአገዛዙ ብቻ ባይሆን፣ ከመንግሥቱ ይዘት /state form / ጋር በጥብቅ አያይዞ መመልከት ያስፈልጋል ። ለምን ሁለቱ በአንድነት ለምርት አለማደግ፣ ለምርት ኃይሎች አለመዳበር፣ ታፍነው በእዚያው እንዲቀሩ በማድረግ ተጠያቂ እንደሆኑና ፖለቲካዊና ባሕላዊ አወቃቀራቸው እንደማይፈቅዱላቸው መረዳት ተገቢ ነው ።ካለበለዚያ ግን ደርግ ቢወድቅና ሌላ ኃይል እንበል ዲሞክራቲክ ኃይል ቢመጣና ያረጀውን መንግሥት መዋቅር ተጠቅሞ ሀገሪቱን



እስተዳድራለሁ ቢል፣ ይህ ኃይል ዕድገትን ፈላጊ ቢሆንም እንኳ በፍጹም በዚህ የፊውዳል ቡርዧዊ መኪና ተጠቅሞ እርስ በእርሱ የተሳሰረ ኢኮኖሚና ሀገሪቱን የሚያበዱን፣ የምርት ኃይሎችን ዕድገት የሚያዳብር ሁኔታ ይፈጥራል ማለት ዘበት ነው ። ለምን ?

የዛሬው አገዛዝ የሚጠቀምበት መንግሥት መዋቅር በፊውዳሉ አገዛዝ የተዋቀረና ከካፒታሊዝም ወደ ሀገሪቱን መግባት፣ ለካፒታል በሚያመች መንገድ በርዕዮተዓለም፣በፖለቲካ፣ በባሕል፣ በኢኮኖሚ የእሱን ጥቅምና የፊውዳሉን አገዛዝ ለመጠበቅ በሚያመች መንገድ የተሠራ ነው ። ይህም ማለት በዚያው ውስጥ የሚሠሩት ሰዎች — መንግሥት ማለት ሰው የለሽ ነገር አይደለም ። ሰዎች ነው የሚያንቀሳቅሱት — በተለይም የላይኛውን የቢሮክራሲያዊና የቴክኖክራት መደብና ክፍል በጥቅም ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር የተሳሰሩ ስለነበሩና ባላቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ርዕዮተዓለም ሁኔታ / status / ተደስተውና በዚያ ቢቻ ተወስነው የሚኖሩ ስለነበሩና ስለሆኑ በፍጹም እንደ አንድ መደብ ተዘጋጅተው፣ አስበውበት የራሳቸውን ጥቅም በማስጠበቅና ሌሎችን የኅብረተሰብ ክፍሎች ከኋላ አስተሳስረው ለማስነሳት የሚችሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች አልነበሩም ። አይደሉምም ። ከዚህ በላይ ደግሞ፣ የተማሩበት፣ የተሠሩበት ትምህርት ከዚያ የተሻለን ነጻነት፣ ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን ለማስከበር እንዲታገሉ አድርጎ ስለአሳደጋቸው፣ በአስተሳሰባቸው ፈሪሳዊ ' .፣ በአሠራራቸው ንዑስ ቴክኒካል ነገርችን፣ ግን ደግሞ ለችግር መፍትሔ የማይበጁን፣ — ግማሽ ሰው ግማሽ አንበሳ እንደሚሉት ነው — ለመሥራት የተዘጋጁ ነበሩ ። በተጨማሪም በአዛዥ በታዛዥ በበላው በምታው ዘዴ የታነፀ ስለነበር — በተለይ ይህ የሚሊተሪና የፖሊስ ቢሮክራሲውን መዋቅር ይመለከታል — የኅብረተሰቡን ዕድገት አፍነው፣ የመፍጠር ችሎታውን አስረውበት ነበር ።

ከአብዮቱ ፍንዳታ ወዲህ በዚህ መንግሥት መዋቅር የተደበኑ " ለውጦች " /modifications / የመደብ መንሸራሸር ቢካሄድም በይዘት ያለው መንግሥት መዋቅር ክፉኛ የፊውዳሉ ባሕል ያረፈበትና አሁንም ቢሆን በዚያው የአሠራር ዘዴ የሚመራ ነው ። ማለትም በሀገሪቱ ውስጥ የተደረገው ለውጥ በተለይም የመሬት ለአራሹ በዚህ መንግሥት መዋቅር አዲስና ከነጻነት ጋር የተያያዙ የአሠራር ዘዴዎችን እንዲያዳብር አላደረጉትም ። በእርግጥ ይህ ከአጠቃላይ የፖለቲካ ነጻነት መስፈን ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ነው ። አዲሱ መጪ ቢሮክራትን የተመለከትን እንደሆነ አሁን ባለው ስታተስ

ተደስቶና ጠገበ የሚኖር በመሆኑ ፣ እንደአርገው ቡርዢሬት ለተሻለ ሁኔታ ለመታገል የተዘጋጀ አይደለም ። በመሆኑም በኅብረተሰቡ ውስጥ ሊኖር የሚችለን ነጻነት፣ የሌሎች መደቦችን መጓበር ማለትም በሬውን የነውስ ከበርቴ ፣ የገበሬውን — ገበሬው የነውስ ከበርቴው እንዲ አካል ነው — የወዛአደሩን መደብ ማደግና መጓበር እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማገኘትን ይቃናቃናል ። ሁለቱ የሚለያዩት ነገ፣ አርገው ቡርዢሬት የምዕራብ ኢምፔሪያሊስቶችን በተለይም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን ናፋቂ በመሆን፣ አዲሱ መጤ ቡርዢሬት ደግሞ የሶሺየት ኢምፔሪያሊዝም አገልጋይ በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው ። ለምርት አለማደግ፣ ለምርት ኃይሎች አለመጓበር የሚያደርጉት ኪባቢል ኋላቀርነታቸው ሌላ፣ የአሠራር ዘዴያቸውና ስታይላቸው የሠለጠነበት ዘዴ፣ አሻጥር በመሥራት ሥራዎችን ለማስተጓጎልና ለማስተናት፣ በያችን በማልፋት/ ደሐውን የኅብረተሰብ ክፍል/ የሚከበት ቢሆን፣ ከዚህ ወኪና ጋር የተያያዙና በየቦታው የተቀመጡ የምርትና የፖለቲካ ካድሬዎች ደግሞ በገበሬውና በወዛአደሩ ላይ የበላይነት በማበየት ምርቱን እንዳያበዱን፣ የምርት መሣሪያዎችን እንዳያሻሽሉ አፍነው ይዘውታል ።

ከዚህ በተጨማሪ ይህ መንግሥተ መንግር በሀገሪቱ ውስጥ የሚመረተውን ትርፍ ሥራ/ surplus Labour / አብዛኛውን በመውሰድና በመምጠጥ /absorve / እንዲሁም በማባከን፣ ለአዳዲስ የምርት መሣሪያዎች እንዳይውሉ በማድረግና ያሉት ኢንዱስትሪዎች እንዳይስፋፉና እንዳያድጉ በመገታት የሚያደርገው አሉታዊ ውጤት ከፍተኛ ነው ። ይህ ደግሞ የገዥ መደብና መንግሥተ መንግሬ በአንድ ሀገር ውስጥ የሚመረተውን ምርትና የሥራ ክንውን በሚመወስኑበት የምርት ግኑኝነትና መንግሥተ መንግሬ በጥብቅ በተያያዙበት ሀገር ውስጥ፣ የገዥው መደብና መንግሥተ መንግሬ እንደ ዕድገት አራማጅና አዋርጋጅ በመሆን ከፍተኛ አወንታዊና አሉታዊ ሚና ይጫወታሉ ማለት ነው ። ከምርት ክንውን ውስጥ የሚገኘው የትርፍ ሥራ ለምርት ኃይሎች ዕድገት ሬሽናል በሆነ መንገድ እንዲውል ከተደረገና በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ያለው ግኑኝነት የተስተካከለ፣ የነገዱ ሰውውጥ እንዲካሄድ ከታቀደና የሚመረተው የመጠረሻ ምርት ደግሞ በአብዛኛው የኅብረተሰብ በጥቅም ላይ /consume / የሚውል ከሆነ፣ ውጤቱ ጤናማና አዎንታዊ ይሆናል ማለት ነው ። በተቃራኒው ገን ይህ የትርፍ ሥራ ለምርት ኃይሎች ዕድገት ባይሆን የመንግሥተ መንግሬን / State machinery / ለማጠናከሪያ፣ ለገዥው መደብ ማዱ



ለቢያ፣ ለጠርነት ማካሄጃ እንዲውል ከተደረገ፣ ለሌሎች የሀገሪቱን ዕድገት ከማይረዱ እንደ ሕንጻ መሥራት፣ ትላልቅ ገበዛዎች ማዘጋጃና በሌሎች ሌሎች ነገሮች ላይ የሚባከን ከሆነ ሀብት የተከማቸ / Capital accumulation /፣ የምርት ኃይሎች ሊያድጉ የሚችሉበት ሁኔታ አይኖርም ማለት ነው ። በሌላ አነጋገር በአንድ ሀገር ውስጥ የሚሠራው ትርፍ ሥራ / surplus Labour / የዚህ በዕቀዱ መጓልና አለመጓል፣ መባከንና ለፕሮዳክቲቭ ኢንቬስትሜንት መዋል ለአንዱ ሀገር ኢኮኖሚ ማደግና አለማደግ ወሳኝ ነው ማለት ነው ። በአርገጥ ይህ ከመደብ ትግል ተነጥሎ መታየት የለበትም ። የትርፍ ሥራ በቻ ባይሆን የዚህ የትርፍ ሥራ አካል የሆነውና መንግሥት በቀረጥ መልክ የሚወስደው የተለያየ ገቢ እንደዚሁ መሰኪ ባለው መንገድ ለኢኮኖሚው ዕድገት በሚውል ነገር ላይ መሠማራት አለበት ።

እንገዲህ የዘረው የገዥው መደብና መንግሥተ መንግሬ በአንዱ በኩል የመደብ ትግሉ እንዳይፋፋም አፍነው ይዘውታል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከሕዝቡ አየመጠጡ የሚወስዱትን ሀብት ለሕዝብ በሚጠቅም መልክ ለማዋል የማይችሉ በቻ ባይሆኑ በሚከተሉት ፖሊሲና ፖለቲካ፣ ዱንነትንና ረሐብን እያስፋፋና እያባደጉ /reproducing on a higer scale / የመጡና የሚሄዱ ናቸው ። ረሀቡንም ከአጭር ጊዜም ሆነ ከረጅም ጊዜ አንጻር ለመፍታት አይችሉም ። የኢትዮጵያ ረሀብ ጋብ እያለና እንደገና እየተመለሰ የኅብረተሰባችን ተደጋጋሚ ክሬዝ በመሆን በኅብረተሰባችን ውስጥ ማንተመን ለረጅም ጊዜ እንደረገጠና ለማኞችና ቀገኞች እንደሆን እንቀያለን ማለት ነው ።

5.2.1 <u>የደርግ የእርሻ ፖሊሲ ከ1975ዓ.ም ጀምሮ</u>

ደርግ ሥልጣን ሲያዝ ጠቢሁና ከመሬት አዋጅ ወዲህ የሀገሪቱን የእርሻ ምርት የሚያሳድግ፣ የምርት መሣሪያዎችን የሚያሻሽል፣ በምርት መሣሪያ ኢንዱስትሪና / ባሉት የቀላል መሣሪያ ኢንዱስትሪ/ በእርሻ መስክ ሊኖር የሚችለን ግኑኝነት የሚፈጥር ፖሊሲ አውጥቶአል ማለት አይቻልም ። ከመሬቱ አዋጅ ወዲህ የገበሬው የሥራ ፍላጎት በጠምርና ገበሬው በየአካባቢው በማኅበር እንዲደራጅ የሚያደርግ ሕግ ቢጋጠም፣ የእርሻን መስክ የሚያስፋፋ የተለያየ የእርሻ ምርት እንዲመረት የሚያደርገና የሕዝቡን ፍላጎት ሊያሟላ የሚችል ፖሊሲ እስከ 1979 ዓ.ም ድረስ ተጠናቅሮ የወጣ አልነበረም ። ይካሄዱ የነበሩት እርምጃዎች በሙሉ በስሜትና በኀብታዊነት እንጂ እንደ ፖሊሲ ሆነው በአጭር ጊዜና

በረጅም ጊዜ ዕቅድ መሠረት ያለባቸው ነገሮች እየተባለ የወጣ ፖሊሲ የለም ። ረሐብ በደረሰበት አካባቢና በዙ ሕዝብ ባለቀበት በወሎና በትግሬ ክፍለሀገራት እንኳ የችግሩ ጥልቀት ታውቆ ለዚያ የሚሆንና ረሐቡን በከፊልእንኳ ለመግታት የተወሰደ ልዩ እርምጃ የለም ። የመሬት አዋጁ በመታወጁ ብቻ ችግሩ የሚቃለል መስሎት ትኩረት መስጠት የሚገባው ተግባር አልተተለመም ። በፍጹም አልተከናወነም ። የዚያ አካባቢ ሕዝብ እንደገና ዛሬ ለረሐብ እንዲጋለጥ ሆነ ።

የሁን እንጂ፣ በ1979 ዓ.ም በተዘጋጀው " የብሔራዊ አብዮታዊ የዕድገት ዘመቻና የማዕከላዊ ፕላን የሱፐርቪዥን ካውንስል " አማካይነት የዕድገት ዘመቻ ታውጇል ። ይህ ዘመቻ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዘመቻ ቢሆንም የሀገሪቱን የእርሻ ሀብት እንደ መሠረታዊ ነገርና የበፊነቱን የምግብ እጥረትና ረሃብ ለመቋቋም ልዩ አትኩሮ እንደሰጠ ያመለክታል ። በዚህም ዘመቻ መሠረት፣

"... it aims at utilizing the development of agricultural sector as the foundation of the overall economic and social development." ( Quarterly Bulletin New series. Vol.5.No.1 March 1979 issued by Economic Research& Plannig Division National Bank of Ethiopia.)

በዚህ ዘመቻ መሠረት መሟላት አለባቸው ከሚላቸው አምስት አንገብጋቢ ጉዳዮች ውስጥ የምግብን ዕጥረት መቋቋም የመጀመሪያው በማድረግ እንደዚህ ይላል፣

1. " elimination of current food shortage to feed the growing poupulation." ከመጋቢቱ ቡሊተን የተወሰደ ።

የምግብ እጥረትን ለመወጣትና ብሎም የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ ይህ የወጣው ዘመቻ በመንግሥት እርሻ፣ በግልና በኅብረት እርሻ መስኮች ላይ አስፈላጊው የቴክኒክ፣ የሰው ኃይልና የገንዘብ ርዳታ እንደሚደረግ በዚህ የዘመቻ ዕቅድ ውስጥ ያስታውቃል ። በዚሁ መሠረት፣ ከዚህ በፊት ለምርት መቀነስና አለማደግ የመሰሉትን ችግሮች አውስቶ፣ የሚታረሱት ማሳዎች መጠን /ስፋት/ በመንግሥትም ሆነ በግልና በኅብረት ይዞታ ያሉት መስፋፋት እንዳለባቸው የምርትም ቢሆን ከለፋት ዓመታት የበለጠ ማደግ እንዳለበት ያበሰራል ። በተጨማሪም በዚህ የመጀመሪያ ዘመቻ የመንግሥትን፣ የግልንና የኅብረት እርሻን



ለማስፋፋትና ምርትን ለማሳደግ ከተመደበው ጠቅላላ ባጀት ውስጥ / 192.797.200 የኢትዮጵያ ብር / 2% ለሚሆነው የመንግሥት እርሻ 178.220.200 የኢትዮጵያ ብር ሲመደብ፤ 98% ለሚሆነው የግል እርሻ፣ 9.511.500 የኢትዮጵያ ብር ብቻ ይመደባል ። / ከብሔራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻ የመጀመሪያ ዓመት ዕቅድ 71/72 ከገጽ 47 የተወሰደ/

የመንግሥት እርሻ ደግሞ ከሚመረተው የእርሻ ምርት 8.8 ብቻ ሲይዝ የግልና የኅብረት እርሻ 89% እና 1.2% እንደ ቅደም ተከተላቸው /respectively / የሀገሪቱን ጠቅላላ የእርሻ ምርት ውጤት የሚሰጡ ናቸው ። በዚህ ዕቅድ መሠረት ጠቅላላው የእህል ምርት፣ ከመንግሥት እርሻ በ1978/79 ዓ.ም ከታረሰው 72.689 ሄክታር መሬት መጠኑ በ1979/80 ወደ 155.280 ሄክታር እንዲያድግ ሲታቀድ፣ የምርቱ መጠን ከ1.63 ሚሊዮን ኩንታል ወደ 3.27 ሚሊዮን ኩንታል ታቅዶ ነበር ። ከግልና ከኅብረት እርሻ ደግሞ በ1978/79 ከሚታረሰው 5.5 ሚሊዮን ሄክታር መሬት መጠኑ ባይጨምርም፣ የምርቱ ውጤት ከ1978/79 ጋር ሲወዳደር ከ46.8 ሚሊዮን ኩንታል፣ በ1979/80 ወደ 53.3 ሚሊዮን ኩንታል እንዲያድግ ታቅዶ ነበር ። / Quarterly Bulletin. Vol. 5 No. 1 መጋቢት 1979ዓ.ም ገጽ 4 ተመልከት/

ነገር ግን በዙ ተስፋ የተደረገበትና ብዙ ባጀትና ከፍተኛ የሰለጠነ የሰው ኃይል የተመደበበት የመንግሥት እርሻ በሄክታር መሬት 25 ኩንታል እህል ማምረት ሲገባው፣ የአብዛኛው የዚህ መስክ ውጤት በሄክታር በአማካይ ከ14 ኩንታል እንዳልበለጠ መንግሥቱ ማመን ተገዷል ። / የኢሠፓአኮን 2ኛ ጉባዔ ሰነዶችና ውሳኔዎች ታኅሣሥ 1975 ዓ.ም ከገጽ 42 - 50 ያለውን ተመልከት ።/

በሌላ በኩል ገበሬውን በዝቅተኛው ፕሮግራም ሁለት አማካይነት /Minimum package Programme II/ ጥሩ ዘር፣ ማዳበሪያና ሌሎች የብድርና የቴክኒክ እርዳታዎችን ለመስጠት መክሬ የተደረገ ቢሆንም ከቀድሞው የMPPI የተለየ መልክ ቢኖረውም፣ በአንድ በኩል ገበሬዎች በጥርጣሬ የደርግን እርምጃ ስለሚመለከቱት፣በሌላ በኩል ደግሞ ዕርዳታው በተስተካከለና በተቀላጠፈ መልክ ስላልተካሄደ የተጠበቀውን ውጤት ሊያመጣ አልቻለም ። እንዲያውም ዱሮ በየክፍለሀገሩ የነበረውን ልዩነት የሚያስፋፋ ሆናል ። ለምሳሌ ሲዳሞና ኢሊባቦርን ስንወስድ ከ1975 ዓ.ም በፊትና ወዲህ ባሉት ጊዜያት

ውስጥ ስለመንግሥት እርሻ ፖሊሲ የባጀት አመዳደብ ባጠኑት ውስጥ ከዚህ የሚ ከተለውን ያስፍራሉ ::

" While post 1975 programme have made attempts to reach the rural poor, it has not been posible to avoid entirely the regional inequalities created by past development programms. In areas affected by pre- 1975 rural development projects, more farmers have been reached than in areas with no pre- 1975 programms, a situation which has exacerbated disparities in regional development."
( Agricultural Development in Ethipia: Goverment budgeting and Development Assistance in the pre. and post - 1975 periods. in: the Journal of Develo-ment Studies 1980. pp. 175 )

ይህም የሚያሳየው ረሀቡ በተደጋጋሚ በሚደርስበትና ድርቅ በሚያጠቃበት አካባቢ ሁኔታው በጣም አሳሳቢ የሆነውን ያህል ደርግ አትኩሮ ያልሰጠው መሆኑን ነው :: በተጨማሪም ምርትን ለማሳደግ ጥረት ቢደረግ ትናንሽ መሰናዶችን በመሥራት፣ የውኃ ጉድጓዶች በመቆፈርና ለበሬው አረሽ ገበሬ ሕዝብ በተለይም ለሰሜኑ ክፍል የሚደርስበትን ዘዴ በመፍጠር የተደረገ ጥረት አልነበረም :: በሀገሪቱ ውስጥ በጠቀላላው 55.000 ሄክታር መሬት ብቻ በመስኖ ይታረሳል :: ይህ ከኃይለሥላሴ ጊዜ ከነበረው በምንም አልጨመረም :: ይህ ደግሞ አብዛኛው በደቡብና ለውጪ ገበያ በሚቀርቡ ሰብሎችና ለሀገሪቱ ፋብሪካ እንደ ጥሬ ሀብት / raw materials / ሊያገለግሉ በሚችሉ ሰብሎች ላይ ብቻ ያተኮረ ሲሆን፣ የሰሜኑ ሁኔታ ምንም አልተነካም ማለት ነው ::

የደርግ ፖሊሲ ከዚህም ቢታይ ከዚህ በፊት በኃይለሥላሴ ጊዜ ይካሄድ ከነበረው የእርሻ ፖሊሲ በአጠቃላይ መልኩ አብዛም የሚለይ አይደለም :: ይህንንም በመንግሥት እርሻ ላይና ድር " በአደጉት የእርሻ መስክ አካባቢዎች " ላይ ከፍተኛ አትኩሮ በመስጠትና የሰሜኑን ሁኔታ " በመዘንጋት " የሚከበት ነው ::ይህንን ስንል ግን የደቡብ ገበሬ አስፈላጊው እርዳታ እየተደረገለት ነው ማለታችን ባይሆን፣ የደርግ ፖሊሲ እሁንም ያልተስተካከለ ዕድገት ማራመዱን ለማመልከት ነው :: በአጠቃላይ መልኩ የኃይለሥላሴው ጊዜ ይመስሳል ስንል፣ በሲዳ /Sida / አማካይነት በADU /፣ በዓለም



ባንክ አማካይነት' :/ WADU / . . የሚካሄደው የእርሻ ፖሊሲና እርምጃ የተወሰነ ርዕዮተዓለምን የሚያንፀባርቅና የተስተካከለ ዕድገትን የሚያመጣ፣ ብዙ ገንዘብና የቴክኒክ ዕርዳታ የፈሰሰበት፣ የዚሁ ፖሊሲ ዓዝት በመጀመሪያ አንዱ አካባቢን ማሰልጠን / modernize / ማድረግ ከዚያ በኋላ ሌሎች ኋላ ቀር ሴክተሮች እየተጎተቱ የኅኔታ ወደ ዘመናዊ ይገባሉ የሚለውን ፍልስፍና የተከተሉ በመሆናቸው ብዙ ገንዘብ፣ የቴክኒክ ዕርዳታ / Extension Service / በአንዱ አካባቢ ብቻ የፈሰሰበት ነበር ::የዚህም ውጤት የሀገሪቱን የምግብ ፍላጎት ለመሸፈን ያልቻለ ብቻ ባይሆን ብዙ ደጋ ገበሬዎችን ያፈናቀለና የባሰ ድኅነት ውስጥ የከተታቸው ለመሆኑ ተመልክተናል :: የደርግም ፖሊሲ ብዙኃኑን ገበሬ ለማዳረስ፣ በተለይም በረሀብ የተጎዳውን አካባቢ " ልዩ ዕቅዱ " በማውጣትና የሀገሪቱን ሀብት በመጠቀም ችግሩን ለመወጣት የተወሰደ እርምጃ አይደለም :: አልነበረምም :: የመንግሥትን እርሻ ለማስፋፋት የተወሰደውን እርምጃ ስንመለከት ብዙ ሀብትና የሰለጠነ ሰው የፈሰሰበትና የሚፈስበት የእርሻ መስክ ነው :: ይህንን ሁኔታ አስታኮ / ILO / የኢትዮጵያን አህጉሮችና በተለይም የእርሻውን ፖሊሲ አጥንቶ ካቀረበው ሪፖርት ውስጥ : John M. Cohen የሚከተለውን ትችት ያቀርባል ::

" It finds (the ILO ) the present goverment emphasis on centralized plannig and highly mechanized state farming to be mis directed. From the ILO team perrpective, the Smallholder sector must be the basis for Etiopian economic development. The report quietly warns that it is unrealistic to count on Western or Eastern foreign aid. Instead, it advocates self reliance and emphasis on small holder productivity and suggests that the goverment aid the peasantry by promoting Community Cooperation in weeding and the construction of terraces and irrigation systems, if not producers cooperatives."
( John M. Cohen: Foreign Involvment in Land Tenure . Reform: The case of Ethiopia. In: International Dimensions of Land Reform 1984 pp 198)

ከዚህ ጋር አያይዞ የደርግ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በአጠቃላይና በተለይ የእርሻው ፖሊሲ የሚመካው በውጪ ዕርዳታና በውጪ ምክር እንጂ ሀገሪቱ ውስጥ ባሉት የተማሩ ሰዎችና በሰፊው ሕዝብ ባለመሆኑ የፖሊሲው ውጤት ካለው የአሠራር ጉድለትና ከሀረገዥ ከሬሲነት ጋር ተደምሮ ውጤት ሊያመጣለት አልቻለም ። የውጪ ሀገር ጣልቃ ገብነት፣ ከምሥራቆች ሌላ የምዕራቦች ጣልቃ ገብነትና በተዘዋዋሪና በቀጥታ ምክር ሰጭነት እያደገ የመጣ መሆኑን የሚያመለክቱ ብዙ ፍንጮች አሉ ። ለምሳሌ በኃይለሥላሴ ጊዜ በውጪ ሀገር ድርጅቶችና መንግሥታት አማካይነት ለእርሻ ማስፋፊያ ይደረግ የነበረው ዕርዳታ በደርግ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ ። ይህንን በቁጥር ስንመለከተው የሚከተለውን እናገኛለን፡፡ ከ1973/74 ዓ.ም ለእርሻ ከተመደበው የካፒታል በጀት ውስጥ 50.2% የሚይዘው ከውጪ የተገኘው ዕርዳታ ሲሆን፣ በ1975/76 ወደ 57% አድጓል ። በሙሉ ገንዘብ ሲተመን /in absolut terms / በ1973/74 19.8 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር የነበረው፣ በ1975/76 ወደ 71.2 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ከፍ ብሎአል ። በመቶ ሲተመን 262% ከፍ ብሏል ማለት ነው ።

> " Agricultural development had increased its dependence on foreign assistance since with total aid and the share of aid within he capital expenditure budget had risen." ( Selshi Sisaye & Eileen Stommes. in: the journal of Development Studies. 1980. pp.170 )

እዚህ ላይ "እርዳታው" በመጨመሩ ባይሆን፣ ይህ እርዳታ እያደገ በሄደ ቁጥር የውጪ ኃይሎች በቀጥታ በኢኮኖሚ ፖሊሲና በተለይም በእርሻው ፖሊሲ ላይ ተጽዕኖአቸው እያደገ ለእነሱ በሚስማማ መንገድ እንዲቀየስ፤ በመጀመሪያ ደረጃ ሕዝቡን ለመመገብና ተስ በተስ እርስ በእርሱ የተያያዘ የውስጥ ገበያ / conereant Economy / እንዲያደግ ባይሆን ወደ ውጪ ያተኮረና ከእነሱ ኢኮኖሚ ጋር የተያያዘ ጥገኛ የሆነና የተዘበራረቀ ኢኮኖሚ እንዲያድግ የሚያደርግ በመሆኑ ነው ። ከሀገሪቱ አየር ጠባይ ጋር የሚስማማ፣ የሕዝቡን የሥራ ፍላጎት የሚያዳብርና ጠቃሚውን ባሕሉን የሚያሳድግ ባይሆን፣ ጥብቅ በሆነ የዋጋ ጥቅም ስሌትና "ጥናት" / feasibility study & cost- Benefit- Analysisfrom the logic of capital) የሚከተል የእርሻ ፖሊሲ ሲሆን፤በዚህ ፍልስፍና መሠረት ሊገዛና ይህንን የእርሻ ውጤት ሊጠቀም የሚችለው ገንዘብ ያለው ብቻ እንጂ



/The ability to pay philosophy/ ሰፊው ሕዝብ ገዝቶ የሚጠቀምበት፣ የተመጣጠነ ዕድገትና በመጀመሪያ ደረጃ ደግሞ የሰው ልጅ ምግብና ሌሎች ዘቀተኛ የሆኑ ነገሮች ያስፈልጉታል ከሚለው ፍልስፍና የሚነደፍና የተነደፈ አይደለም ። እንደዚህ ዓይነቱ ዕርዳታ ከዚህ ቀደም እንዳየነው የተመጣጠነ ዕድገት ባይሆን ውንነትን /marginalization of the society & underemployment /፣ የተመሰነውን የኅብረተሰብ ክፍል ብቻ የሚጠቅም ይሆናል ። ይህ ማለት ግን በፍጹም "ዕርዳታ" አያስፈልገም ማለት አይደለም ። በእርግጥ ዕርዳታ የሚባለው ዕውነተኛ ጽንሰ ሐሳብ ካለ ለማለት የሚፈልገው "የዕርዳታው" ተገቢ ወደ መሆኑ ማምራት. በተጨባጭ የሕዝባችን ነጻ የፈጠራ ሥራ መቃወምና እራሱን በራሱ ለመቻል የሚደረገውን ትግል የሚቃወም በመሆኑ ነው ። በእርግጥ፣ ለነደ ደርግ ያለ አድጋሪ አገዛዝ ይህንን መርሆ በፍጹም ሊከተል እንደማይችል ደግሞ ገልጽ ነው ።

በአጠቃላይ የደርግን የእርሻ ፖሊሲ ስንመለከተው፣ በይዘት የሰፊውን ሕዝብ የምግብ ፍላጎት የማያሟላ፣ የሥራ ፍላጎትን የማያዳብር፣ ድህነትንና ረሐብን የማያጠፋ ሲሆን፣ ይህም በተጨባጭ ሲታይ የዓለም አቀፍ ካፒታሊዝም ከቀነባበረው ፖሊሲ በፍጹም የማይለይና የደርግ መንግሥትም በዚህ ውስጥ የሚያገኘ ገሬ የገባው ፍጡር ነው ።

### 5.2.2 የኅብረት እርሻና በገበሬው ላይ የሚደረገው ተጽዕኖ

ማኅበራችን ይህንን ካለጊዜው የታወጀውንና በፈቃደኝነት ባይሆን በኃይልና በጉልበት የተደነገገውን የኅብረት እርሻ ፖሊሲ መቃወም ይቃወቃል ። በመሠረቱ የኅብረት እርሻ አስፈላጊ ሲሆንም፣ በመጀመሪያ ደረጃ ብዙ ብዙ የማስተማር ሥራዎች መሠራት እንዳለባቸው ዴሞክራሲያዊ ነጻነቶችና የገበሬው እምነት መኖር እንደሚያስፈልጉ ተገልጿል፣ በጊዜው ተተችቶበታል ። ይህ ጉንጋኔ ከንጣ በኃላ የታየው ውጤት እቀጋቢ ብቻ ባይሆን በብዙ አካባቢዎች ተቃውሞን እንዳስከተለና በሥራም ቦታ የዝምታ ተቃውሞን /passive resistance / እንዳመጣ ነው ። ይህንን በመቃወም ብዙ ገበሬዎች የእርሻ ቦታቸውን ጥለው ወደ ነጻ አውጪ ድርጅቶቻቸው ተቀላቅለዋል ። በዚህ የኅብረት እርሻ ውስጥ፣ በገበሬ ማኅበራት ከተመዘገቡት 5.326 ሚሊዮን ቤተሰቦች ውስጥ፣ 79.385 ቤተሰቦች ብቻ በአሁኑ ጊዜ በኅብረት እርሻ ተደራጅተዋል ።

ይህ ሁኔታ በምርት አሰጣጥ ላይ ያስከተለው አሉታዊ ውጤት በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። የገበሬው መደብ በነጻ እንዲያድግ፣ የሥራ ፍላጎት እንዳይጨም[illegible]

ባለቤት ሆና መንግሥት የጋ ባይደነገገበት አየሸጠ የምርት መሣሪያዎችን አየገዛና ሌሎች ቀን ተቀን የሚጠቀሙባቸውን ቁሳቁሶች አየገዛ የአስተራረስ ዘዴውን አንዳያሻሽልና ምርቱን ከፍ አንዲያደርግና ኑሮውን አንዲያሻሽል ደርግ አገደታል ::ካፒታሊዝምን በአንጭጩ ለመቅጨት የተደረገው ሙከራ ለምርት አለማደግ ብሎም በገበሬው ዘንድ የባበ ድንነትን አስከትሏል ::

ደርግ ዛሬ በዚህ የነበረት አርሻና በጠቅላላው በገበሬው ላይ የሚከተለው ፖሊሲ በገበሬው ላይ ብቻ ሳይሆን በተጠቃሚው ላይም ጉዳትን አያመጣ ነው :: በአንዳንዴ አከባቢዎች ገበሬዎች የገዒታ ምርታቸውን በመንግሥት በተደነገጉት ለአርሻ ነገዴ ኮርፖሬሽኖች በዝቀተኛ ዋጋ መሸጥ አለባቸው :: ወደ ፈለጉበት አከባቢ ሄደው በደህና ዋጋ አንዳይሸጡ ተገደዋል ::በሌላ ወገን ደግሞ አነዚህ በመንግሥት ሥር የተደነገጉት የንግዴ ኮርፖሬሽኖች የምገብ አጥረት ባለበት አካባቢ ከገበሬዎች በዝቀተኛ ዋጋ የገዙትን አህል አስወድደው ሲሸጡ፣ በሌላ በኩል የተሻሉ አካባቢዎች ደግሞ ከገበሬው ጋር በመወዳደር፣ በዝቀተኛ ዋጋ በመሸጥ የገበሬውን የሥራ ፍላጎት ለየቀጩት ነው ::ይህ ብቻ አይደለም :: ዛሬ የኢትዮጵያ ገበሬ በአማካይ አንዴ ሄክታር መሬት ነው ያለው :: ከዚህ በላይ ደግሞ፣ አንዳንዱ ዝቀተኛ ጥቅሞችን ቢያገኝም፣ ለገበሬ ማኅበሩ በዓመት ከመቶ የኢትዮጵያ ብር በላይ ይከፍላል :: ይህ ሁሉ በተጨባጭ የገበሬውን የመግዛት ኃይል ይቀንባል :: በተዘዋዋሪና በቀጥታ የሥራ ፍላጎትን የሚቀንሱበት ዘመቻዎችና ዱንጋጌዎች የገዒታ በምርት ላይ ብሎም በምርት ኃይሎች ዕድገት ላይ አሉታዊ ጉዳት አለው ማለት ነው ::

5.3 ጦርነትና ረሐብ

የደርግ መንግሥት ቢያንስ ካለፉት ስምንት ዓመታት ጀምሮ የማያቋርጥ ጦርነት አያካሄደ ነው :: ይህ ጦርነት በአንዴ አከባቢ ብቻ ተወስኖ የሚካሄድ ባይሆን ከታወቀት የአርትሬና የትግሬ ውስጥ ጦርነቶች ሌላ በኦጋዴን፣በወሎ፣ በቢዓምና በባሌ ውስጥ በጦርነት ዘፍቋል :: ይህ ጦርነት አየገፋ ከመጣ ጀምሮ፣ በተለይም ከ1977 ዓ.ም ወዲህ ያለቀው ወጣት ኃይል፣ የፈሰሰው ሀብት፣ የጠፋውና የተበታተነው መንደር፣ የተበደደው ወጣት፣ ሽማግሌ፣ የወደመው ማሣ ቁጥር አጅግ ከፍ ያለ ነው :: በትግላችን ውስጥ የሞራል ጥያቄ ከፍተኛውን ቦታ የያዘ ቢሆንም፣ በዚህ ጦርነት ያለቀው ወጣት ገበሬና



አቅንና አገሬን ተቆርጦ ዛሬ ከምርት ሂደት ውስጥ እንዲይባ ተፍ የታገደው ገበሬ ቁጥርና እንዲሁም ከጦርነቱ አየሸሸ ወደ ጎረቤት ሀገሮች የሚሰደደው ገበሬ በኢትዮጵያ አርሻ ሕይወት ውስጥ ከፍ ያለ ጉዳት አንዲደርስ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል :: በአርሻ ተሰማርቶ ከነበረው ገበሬ ወደ 300.000 የሚጠጋው ጠንካራ የሰው ኃይል በአሁኑ ጊዜ በጦርነት ውስጥ ተሰማርቶ ይገኛል ::

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአርሻ አንደሚመካ የታወቀ ነው :: 90% የሚሆነው ሕዝብ ከአርሻ ጋር በተያያዙ ነገሮች ኑሮውን አንደሚያስተዳድር ግልጽ ነው :: በአንደዚህ ዓይነት ኅብረተሰብ ውስጥ፣ ማለትም ትላልቅ የአርሻ መስኮች ባልተስፋፉበትና ከዘመናዊ የምርት መሣሪያዎች ይልቅ የሰው ጉልበት/ ኃይል ትልቅ ሚና በሚጫወትበት ሀገር ውስጥ፣ የአንዴ ወጣት ገበሬ በተለያዩ ምክንያቶች ከአካባቢውና ከቤተሰቡ መወገዴ ከፍተኛ ጉዳትን ያስከትላል ::በሌላ አነጋገር በኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ውስጥ ወጣት ገበሬዎች ለወላጆቻቸውና ለቤተሰቦቻቸው ከሌሎች ባሕላዊ የአደጋ ዘዴዎችና ፍቅር ሌላ የሚሰጡት አገልግሎት ከፍ ያለ ነው :: በአንዴ ቤተሰብ ውስጥ የሚኖረው ወጣት ገበሬ የአባቱና የእናቱ ምሰሶ፣ ጠባቂና አለኝታ ነው ማለት ነው ::እሱ ከሄደ፣ ከሞተ፣ የቤተሰቦቹ ኑሮ ይዳፈናል :: የአካባቢው ሰዎች ካልረዷቸው በስተቀር ወላጆች፣አዛውንቶችና ባልቴቶች ካለምንም ድጋፍና አለኝታ ይቀራሉ ማለት ነው ::

ይህ የደርግ የማያቋርጥ ጦርነት በአጠቃላይ መልኩ ለምርት መቀነስ ምክንያት ቢሆን፣ በተለየ መልኩ በገጠር ባሉ ዕድሜአቸው ገፋ ባለ አረጋሽ ገበሬዎች ላይ ያደረሰው ጉዳት በቀላሉ የሚታይ አይደለም :: ከዚህ በተረፈ ፣ ካለምንም ታሪካዊ ኃላፊነት በአንዳንዱ ቦታዎች የሚደረጉት አስቃቂ የቦንብ ድብደባዎች በሰው ነብረት ላይ፣ በአርሻ ማሣ ላይ በየጊዜው የሚያስከትሉት ጉዳት ከፍ ያለ ነው :: ተዘርተው የበቀሉ የአርሻ ማሣዎች በቦንብ አየተደበደቡ በመቃጠላቸው ብዙ ሕዝብ ለምግብ የሚቸገረው መና ሆኗል ::አነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ አየተባባሱ እንደሚሄዱ ከአሁኑ መናገር ይቻላል ::

ከዚህ በላይ ግን፣ ይህንን በጦርነት የተሰማራውን ከ300.000 –500.000 የሚጠጋ ሚሊሽያና ወታደር – አምራች ያልሆነውን ኃይል – ለመመገብ የሚወጣው ወጪ ከፍ ያለ ነው :: ወታደሩ ጦርነቱን " በሞራል " እንዲያካሂድ የገዒታ የማያቋርጥ የምገብ

መንሸራሸር ያበረልጋል ። ይህም ማለት በማምረትና በመብቃም /consume / መሀከል የተዛባ ሚዛን አለ ማለት ነው ። አንድ የኅብረተሰብ ክፍል ለአልጫ ነገር ባይሆን በኅብረተሰብ ውስጥ የሚመረተውን የምግብ ሆነ ሌላ ሌላ ነገሮችን በየጊዜው ተጠቃሚ ቢቻ ከሆነ፤ በሌላ አነጋገር በምርት ሂደት ውስጥ ወይም ከዚህ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከተያያዙ ነገሮች ጋር ያልተሳሰረ ከሆነ፣ለኢኮኖሚና ለማኅበራዊ ዕድገት የሚያመጣው ውጤት አሉታዊ እንጂ ጥቅም አይደለም ። ዛሬ የኢትዮጵያ ወታደር ሚሊሽያ ከአምራች ገበሬው ጋር ሲወዳደር በሬስ የሚደርሰው አሀል የአጥፍ አጥፍ ነው ። ይህ ማለት ወታደሩ አይመገብ ማለት ባይሆን፣ በእምከሀተኛ ጦርነትና የሀገሪን ሕዝብ ለሚጨርስ ወታደር — በአርጎቀ ታዘም ቢሆን — የሚጋዘው የእርሻም ሆነ የኢንዱስትሪ ውጤት ከፍተኛ ነው ።

የደርግ አገዛዝ ሥልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ ለዚህ ጦርነት የሚያወጣው ወጪ /በጀት / በየዓመቱ ከፍ እያለ እንደመጣ በውጪ ሀገር የሚታተሙ ስታትስቲኮችና የሀገሩ ስታትስቲኮች ያመለክታሉ ። ሌሎች እንዳንዱ የውጪ ሀገር ስታትስቲኮች የአሁኑ አገዛዝ ለዓመት ከሚመደበው ጠቅላላ በጀት ውስጥ / current & capital expenditure / ውስጥ 45% ለጦርነት እንደሚመደብ ያረጋግጣሉ ። ለማንኛውም በሀገሪቱ ውስጥ ከሚታተሙትና በውጪ ከተወሰዱት ስታትስቲኮችና መጽሔቶች ተመርኩዘ ይህን ወጪ በነመለከት ዕድገቱ ከፍ እያለ መሄዱን እንመለከታለን ። ይህንንም በየዓመቱ ከሚወጣው ጠቅላላ በጀት /current & capital expenditure / ውስጥ ከ1974 /75 ጀምሮ ለጦር መሣሪያና ለሠራታ እንዲሁም ለእርሻ የወጣውንና የሚወጣውን ዓመታዊ በጀት አያወዳደርን እንመልከት ።

በሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር /ለመከላከያና ለሠራታ/

| 1974 /75 × | 75 /76 × | 76 /77 × | 77 /78 × | 78 /79 ×× | 79 /80 ×× | 80 /81 ×× | 1981 /82 ×× | 82 /83 ×× |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 330.5 | 465.7 | 534.7 | 537.8 | 817.9 | 882.2 | 875.9 | 906.6 | 965.9 |



በሚሊዮን የኢት. ብር /ለእርሻና ለበረራ/

| 1974 /75 × | 75 /76 × | 76 /77 × | 77 /78 × | 78 /79 ×× | 79 /80 ×× | 80 /81 ×× | 1981 /82 ×× | 82 /83 ×× |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 65.5 | 72.8 | 110.5 | 140.1 | 280.5 | 262.5 | 277.5 | 339.9 | 350.1 |

ደርግ የሚያካሂደው ጦርነት ከየዓመቱ በጀት ላይ የተመለከተውን ያህል ለጠቅላላው የመጨቀኛ መሣሪያው፣ ለመጨፍጨፊያው ይህን ያህል ገንዘብ ያወጣል ። ከዚህ ቀደም እንደተመለከትነው በአንድ ሀገር ውስጥ የሚመረተው ትርፍ ሥራ/ surplus labour / በሕዝቡ ላይ እየጫነ የሚወስደው የተለያዩ ቀረጥ ፕሮፓጋንዳ በሆኑ ነገሮች ላይና ሌሎች የሕዝቡን የኑሮ ሁኔታ በሚያሻሽሉ ነገሮች ላይ ካልተሠማራና ካልተሠረበተ፣ እንዲሁ የሚባክንና በመነግሥቱ የሚቀጥ ከሆነ አንድ ሀገር ልታድግ አትችልም ። አትበለጸግም ። በምትኩ ገን ድንነት፣ ጥገኝነት የኅብረተሰቡ የቀን ተቀን ኑሮ ይሆናል ። በሌላ ወገን የደርግ መንግሥት ለምሥራቅ አውሮፓ፣ በተለይም ክቡሶቪየት ኅብረት በሚያደርገው የመሣሪያ ግዢ የካፒታል ክምችት እየፈጠረላት ነው ። እንዴት? የሶቪየት ኅብረት የጦር መሣሪያ ኢንዱስትሪ በየጊዜው እንዲንቀሳቀስና እንዲያመርት የገበያ ለምርቱ ገበያ በየቦታው ማግኘት አለበት ። ይህ የጦር መሣሪያ ገበያ ደግሞ ባያገኝ የሚኖረው በየቦታው ጦርነት ሲካሄድና ሰው ካለቀ፣ በተለይም ተሸናፊ በሚደናርበት ቦታና ጦርነት ለረጅም ጊዜ የሚካሄድ ከሆነ ታነኮች፣ አውሮፕላኖች በየጊዜው ቢሞቱ ይህን ለመተካት በሚደረገው ጥያቄ / demand / በምርትና በገበያ መሀከል ያለው ግኙነት ባይቋረጥ ይቀጥላል ። የሙቱትና የተበላሹት አውሮፕላኖች ደግሞ መጠገን ስላለባቸው ያሽ የምታዘው

---

× የተገኘው Area handbook Series, Ethiopia a country study 1982 pp.307 by Harold D. Nelson & Ircing Kaplan

×× የተገኘው Economic Development of Ethiopia( wirtschaftliche Entwicklung Athiopien. May 1983

ሀገር መገጣጠሚያውን አረቧ መሠረት ካልቻለች የግዴታ መሣሪያውን ከምታዝበት ሀገር ማስመጣት አለባት :: የመሣሪያ ኢንዱስትሪ ደግሞ እራሱን የቻለ / industrial complex / ስለሆነና የተያያዘው ወይም የሚያያዘው ከብረታብረትና ከሌሎች ለመጨረሻ የመሣሪያው ምርት/endproducts / የሚያገለግሉ ፋብሪካዎች ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ዝር ዝር በእንደዚህ ዓይነት ጦርነትና የመሣሪያ ገበያ የምትጠቀመው ሀገር መሣሪያውን የምታመርተው ናት :: የደርግ መንግሥት ከስምንት ዓመታት ጀምሮ በዚህ ዓይነት ለሶቭየት ኅብረት ይህንን የአንድ ክፍል ሀብት ክምችት የሚፈጥርላት :: በዚህ ጦርነት ውስጥ ኢትዮጵያ የምትገኘው በዚህ ላይ በተጠቀሰው አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን፣ ይህ በየጊዜው እያደገ የሚሄደውን የጦር ዕቃ ለመክፈል ጥሬ ገንዘብ ስለሚያስፈልጋት፣ ይህንን ለማድረግ ደግሞ የግዴታ ለውጪ ገበያ በሚቀርቡ የእርሻ ምርቶች ላይ አትኩሮ ማድረግ አለባት :: ዕዳው ከፍ እያለ ሲሄድ፣ ለዚህ እርሻ መስፋፋት የሚወጣው ወጪ ማለት የሰለጠነ ሰው፣ ቴክኖሎጂ፣ከዚህ ጋር የተያያዙ እንደ ትራንስፖርትና ሌሎች አገልግሎቶች ላይ የሚደረገው ወጪ ከፍ እያለ ይሄዳል :: ይህንንም ለማስፋፋት ከምዕራብ ዕዳ /ብድር/ ስለምትወስድ፣ እንደዚሁ ዕዳውን ለመክፈል የግዴታ በዚያው ላይ ትቀጥላለች ካለበለዚያ ጥሬ ያለው ምርት በዓለም ገበያ ላይ ካላቀረበች፣ — እነዚህ ሌሎች ችግሮችን / constraints / ትቱን ማለት ነው :: — ከሌሎች ተመሳሳይ ምርት ከሚያቀርቡ ሀገሮች ጋር ልትወዳደር አትችልም :: ይህም ማለት የግዴታ ሌሎች ለሕዝቡ በሚቀርቡና በሚያስፈልጉ የምግብ ዓይነቶች ላይ አትኩሮ አታደርግም :: የዚህም ምርት ከሕዝቡ ፍላጎት ጋር ስለማይሄድ፣ የምግብን ፍላጎት ለማሟላት ቢያንስ የከተማውን ሕዝብ እንዲለመገብ ምግብ ከውጪ ማስመጣት ይኖርባታል :: ከዚህም በላይ፣ ይች ሀገር ኢኮኖሚዋ /flxible / ስላልሆነ፣ ዘናብ ሲቀር፣ ድርቅ ሲመጣ በቀላሉ ለረሐብ ትጋለጣለች :: ለዚህ ደግሞ እጅዋን ወደ ውጪ እንድትዘረጋ ትገደዳለች :: ከሌላ የችግርና የድኅነት ዙሪያ ጥምጥም ውስጥ በመግባት በችግር ውስጥ ለረጅም ጊዜ ትኖራለች :: የዚህ ዙሪያ ጥምጥም ውጤት እንደኛው ክፍል ዛሬ የምናየው ነው ::

5.4 <u>የደርግ የሠፈራ ፕሮግራምና የሚያመጣው ውጤት</u>

የደርግ መንግሥት አሁን ሥራዬ ብሎ የያዘው ሰዎችን ከሰሜን ወደ ደቡብ በግዴታ እየወሰደ ማስፈር ነው :: አንዳንዶቻችን ከቀላል የሞራል ጥያቄዎች ተነስተን፣ ታዲያ ምን ያድርግ ? ያለው አማራጭ ይህ ብቻ ነው ከሚለው መደምደሚያ ላይ እንደርስ ይሆናል ::



የደረስነው አሁን :: ይህ ጉዳይ እንደዚሁ በቀላሉ መታየት የለበትም :: ነገሮችን ትንሽ ጠለቅ ብሎ መመልከት ያስፈልጋል ::

ከዚህ ቀደም ብለን እንዳነሳነው ደርግ በሥልጣን ላይ ሊወጣ ከቻለባቸው ምክንያቶች አንደኛው — የታሪክ አጋጣሚ ቢሆንም — ረሐቡ ነው :: የኃይለሥላሴን መንግሥት እየከሰሰና እየወነጀለ ነበር :: ሆኖም ግን በዚያን ጊዜ በቀረበው ጥናት መሠረትና ከዚያም በኋላ እንደታየው፣ ረሐቡ በተለይም የዚያ አካባቢ " ልዩ መለያ" የሆነውን ያህልና ተደጋጋሚ እንደመሆኑ መጠን፣ የደርግ መንግሥት ለዚያ አካባቢ የሚሆን ልዩ ፕሮግራምና መፍትሔ ሊሆን የሚችል የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅድ አውጥቷል ወይ ? አላወጣም :: ይህ ብቻ አይደለም :: በውጪ ሀገር ኢኮኖሚስቶች አማካይነት በ1977 እና 1980 ዓ.ም በዚያ አካባቢና እንዲሁም በሌሎች አካባቢዎች አስከፊ ረሐብ እንደሚመጣ ተጠንቶ ቀርቦለት እርምጃ ለመውሰድ ብቁነትን አስመስክሯል ወይ ? አላስመሰከረም :: ከዚህ ሌላ እቡ አረቡ ለአንድ የእንግሊዝ ኢኮኖሚስት/professor K. Griffen / ስለ ረሐቡ ጥናት እንዲያካሂዱ በሰጠው ኃላፊነት በመስከረም ወር መጀመሪያ 198[illegible] ዓ.ም የረሀቡን ጥልቀት አሳይቶ ከአቦቀ ጀምር የምግብ እጥረት እንዳለና ምግብ 0.8 እየቀነሰ መምጣቱን አመልክቷል :: ከዚህ ላይ ብቻ የበጋየው አባባል /ጥናት/ረሐቡን ያመጣው ወይንም የረሐቡ ምክንያት አርቆ ነው የሚለውን ያመለክታል :: ተንከልም አለበት :: ይሁን እንጂ፣ ይህ ጥናት በቀረበ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ በሚያሳዝን ሁኔታ 200 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በማውጣት ለተመሠረተው ፓርቲ ፍሬያ ሲጠል፣ ውስኪና ሻምፓኝ መታጠቢያ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ርሮዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ በረሐብ አለንጋ እየተገረፈ ነበር ::ነውም :: ይህ ሁኔታ ምን ያህል በሥልጣን መቆለገን፣ ለሀገር፣ ለሕዝብ አለማሰብን፣ እረመኔነትን የሚያሳይ መሆኑን መረዳት ይገባናል :: እንዲያው የጥቅምና የሥልጣን ጉዳይ ነው በሚለው ብቻ ማለፍ አይቻልም :: ሞራል፣ ሥነ ምግባር፣ ኅምክረኢ ባሕል የጎደለው መሆኑንም አጥብቆ መገንዘብ ያሻል ::

ደርግ ሥልጣን ላይ ከወጣ ወዲህ ለነዚ ድርቅ ድርቅ የመታቸው ቦታዎች ብቻ ሳይሆኑ በዚያው አካባቢና ለምለም የነበሩ ቦታዎች እርዛሮፆች ወደ ምድረበዳነት እየተለወጡ ነው :: የአፈሩ መሸርሸርና በነፋስ መጠረግ የዚያ አካባቢ ዕጣ ሆናል :: እንግዲህ ይህ ዓይነት አገዛዝ፣ አገር ስትጠፋና ስትወድም፣ ወደ ምድረበዳነት ስትለወጥ ዝም ብሎ የሚመለከትና ታሪካዊ ኃላፊነት ባለመስማት ሁኔታውን ጦርነት በማካሄድ የሚያባብስ ከሆነና ከዚያ በኋላ " እርምጃዎችን ለመውሰድ " ደፍ ደፍ ቢል የይስሙላና

የይዞታን እንጂ ለመፍትሔ አይደለም ። በሌላ በኩል ግን ይህ የበፊራ ዘመቻ ከፖለቲካው ባሻገር በአካባቢ ላይ የሚያመጣው ጉዳት ከፍተኛና በዚያውም ለራሱ ለድርቅ ምክንያት ሊሆን የሚችል ነው ። የሚሰፍሩት ሰዎች በሄዱበት አካባቢ፣ የገ ዱታ ቤት ሰርተው መኖር አለባቸው ። ለኃይል / Energy / እንጨትን መጠ ቀም አለባቸው ። በአንድ ቦታ በእርግጥ በተያየ አካባቢ ቢሆኑም ስለሚሰፍሩ የኃይ ልና የመጠለያ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ቢሉ -ማሟላትም አለባቸው - ተፈጥሮ በለገሳ ቻው ላይ ብቻ ይመካሉ ። ዛፎችን ይቆርጣሉ ። ይህ እየቀጠለ ሲሄድ የበረሃ ሁኔታ ወደ ደቡብም ይስፋፋል ። ኢትዮጵያ ወደ ምድረበዳነት ስትለወጥ የቀረት የዛፍና የጫካ መጠን 3-4% ብቻ ነው ። ይህም እንደተገመተው እስከ 20 ዓመት ድረስ ብቻ የሚቆይ ነው ። አሁን ደርግ በሚያደርገው የማስፈር ዘመቻ ዕድሜው ይቀንሳል ማለት ነው ። ከዚህ በተረፈ የሰዎች የአስተፈረር ዘዴ ካልተለወጠና በተወሰነ ቦታ ብቻ እንዲከማቹ ከሆኑ የገዱታ ዘር ዘር ለመሬቱ መሸርሸር፣ ለምለምነት መጥፋት የሚያመ ጣው ጉዳት ከፍ ያለ ይሆናል::

በአኛ ግምት ግን፣ አሁንም በዚያ በሰሜን ረሀብ ከፍኛ በደረሰበት አካባቢ ተበበጣጥረው ያሉትን ሰዎች በመንደር፣በመንደር እያደራጁ ሕዝቡ አራሱ የራሱን ችግር እንዲፈታ፣ ጉድጓዶችንና ቀላልና ተራ መስኖዎችን እያዘጋጁ እንዲጠቀም አስፈላጊውን ዕርዳታ መስጠት ነው ። የመሬትን ለምለምነት ለመጠበቅ፣ በአንድ በኩል ኦርጋኒ ማዳበሪያ / እንደ አበት ፣ ፋንዲያ ፣ በጠጥና ሌሎችን / የመሳሰሉትን አደገኛ ባከ ቴሪያዎቻቸውን እያጠፋና እያጋጡ ለመሬት ማዳበሪያነት መጠቀም ። ኃይል / Energy / ከእነዚህ ኦርጋኒክ ነገሮች ለማግኘት ይቻላል ። በአሁኑ ጊዜ በአንዳንድ አካባቢዎች ስለሚሠራበት ይህ ሊስፋፋ የሚችልበትን ዘዴ በማጥናት ቶሎ በሰፊው ሥራ ላይ ማዋል ። ለዚህ፣ በዚህ ልምድ ካላቸው ሀገሮች ጋር ሃሳብ እንዲያካፍሉ መጋበዝ ። እንደሚታወቀው ከሆነ ይህንን በቀላል ቴኪኒክና ዕውቀት መሥራት ይቻላል ።ሀገራችን ባለችበት ሁኔታ የኤሌክትሪክን ማመንጫ በየቦታው መትከል አትችልም ። የኬሚካል ማዳበሪያ ኢንዱስትሪም ልታቋቁም አትችልም ።በሌላ በኩል፣ የመሬትን ለምለምነት ለመጠበቅ፣ የተጠና የዛፍ ተከላ ማካሄድ ያስፈልጋል ። በዚህ የሰለጠኑ ሰዎች በተለያዩ ሀገሮች የቀሰሙትን ልምድ / ኢትዮጵያውያንን ማለት ነው / በኢትዮጵያ ሁኔታና አየር ጋር የሚስማሙ የዛፍ ዓይነ ቶች በሰፊው የሚተከሉበትን ዘዴ በሰፊው እንዲያጠኑና በዚህ ተግባር ላይ እንዲሠማሩ ማድረግ ።



ይሄ ከዚህ በላይ የበፈረውን፣ በእርግጥ የደርግ አገዛዝና መንግሥት መዋቅር ይሠራ ሄል ማለት አይደለም ። አንድ ሰው አንዱን ነገር ሲቃወም ለምን እንደተቃወመና ከዚህ የተሻለ መፍትሔ ማሳየት አለበት ። ካለበለዚያ ነገሩ ዝም ብሎ ተቃውሞ ብቻ ይሆናል ። በሌላ ወገን፣ ይህ ሃሳብና ፍላጎት ለደርግ ጉትቀ ሊኖር ይችላል ። ይህ አይከፋም ። ነገር ግን ከላይ የተመለከተው መፍትሔ ደጋግመን ሌላ ቦታዎች ለማሳየት እንደሞከርነው፣ ከፖለቲካ ነጻነት፣ ከዲሞክራሲያዊ ባሕል፣ ታሪካዊ ኃላፊነትን ከመቀ በልና ይህንን ከመገንዘብ ጋር፣ ከሥነ ምግባር / Ethics / ጋር የተያያዘ በመ ሆኑ ደርግና ገበሬአበሮቹ የፈለጉትን ያህል ቢፍጨረጨሩም ለገበሬ ተበርአችን ከሪዝ፣ ለረጠቡ መፍትሔ ሊሰጡ አይችሉም ።

## 6.0 መደምደሚያ ።

በዚህ አጭር ጽሑፍ ውስጥ እንዳመለከትነው በባህል አካባቢ በሚገኙ ሀገሮችና በኢትዮጵያ ለደረሰው ረሐብ ምክንያት ድርቅና የሕዝብ ብዛት ሳይሆን እነዚህ ሀገሮች በአጠቃላይና ኢትዮጵያ በተለይ ያሉበት የኢኮኖሚ ሥርዓትና ከዚህ የሚፈልቀው ፖሊሲ ሲሆን፣ እንደ የሀገሩ በዓለም አቀፍ ካፒታሊዝም የሥራ ክፍፍል ውስጥ መግባት ከፍተኛነት፣ / the degree of integration in the internatinal capitalst economy/ የዓለም አቀፍ ካፒታሊዝም እንዴት አድርጎ ለረሀብ እንዲጋለጡ እንደገፋቸው፣ ዋንኛው እንዳደረጋቸው ነው ። የኢትዮጵያ ሁኔታ ለየት ያለ ቢሆንም፣ ዛሬ በሶስተኛው ዓለም በአጠቃላይ፣ እንዲሁም በባሕል አገሮችና በኢትዮጵያ የደረሰውን ድንገት ረሃብ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከበፊቱና በብዙ በለቶች ከተያያዘው የአገዛዝ መከከም ጋር ለይቶና ነጥሎ ማየት ትልቅ ስህተት ነው ። የዚህች ጽሑፍ ዓላማ ይህንን ጠቅላላ መልኩን ለማሳየት የታቀደ ባይሆንም፣ ይህም ገና ብዙ ጥናትና ሥራ ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ፣ በአጭሩም ቢሆን እንዴት ረሀብና ፖለቲካ፣ ድንገትና ፖለቲካ፣ እነዚህ ደግሞ በብዙ ሰንሰለቶች ከኢምፔሪያሊዝም ጋር እንደ ተጋባበሱ ለማመልከት ተሞክሯል ። ይህ ሰንሰለት ሲበጠስና ከውስጥ ደግሞ እውነተኛ ለውጥ ሲደረግ እነዚህ ጠባዮች ከገቡበት ፍጻ ተላቀቁ ማለት ነው ።

የኢትዮጵያን ሁኔታ ለየት የሚያደርገው፣ በዓለም አቀፍ የሥራ ክፍፍል ውስጥ ይህንን ያህልም ጠቀሰለ እስመገባቷ ነው ። ነገር ግን የርዕዮተ ዓለሙ፣ የትምህርቱ፣ የባሕሉና በፖለቲካ መዋቅሩ ላይ ያለው ተጽዕኖ የሚናቅ አይደለም ። ያለው ሳይኮሎጂካል ተጽዕኖ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። የአሜሪካና የሌሎች የምዕራብ ካፒታሊስቶች ኢትዮጵያ ውስጥ በኢኮኖሚም ሆነ በሚሊቴሪ ደረጃ ተጽዕኖአቸው ስለቀነሰ በጠቅላላው ትርጉማቸው ጠፍቷል ማለት ስህተት ነው ። በአሠራር ደረጃ/Beurocratizati techocrtization, tylcrization) እነዚህ ሁሉ የሠፈሩና የሚሠራባቸው፣ ለምርት ኃይሎች እንቅፋት የሆኑ ናቸው ። የመደብ ትግልም የሚካሄድባቸው የአሠራር ስልቶች ናቸው ።

በሌላ ወገን ግን፣ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በየቦታው ደጋግመን ለማሳየት እንደሞከርነው በሀገሪቱን እሁንም ቢሆን፣ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ፣ የምርት ኃይሎችን እንዳያድጉ



አፍና የያዙቸው፣ የፖለቲካ መዋቅር፣ / on the political plane / የተፈታ ባለመሆኑ ነው ። በሌላ አነጋገር ፣ ምንም እንኳ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ቢኖርምና ያንን የመሰለ አምጭ " መሬት ለአራሹ " ቢታወጅም፣ ከፖለቲካ ነጻነት ጋር ባለመያያዙ፣ በአንድ የተወሰነ ወቅት ተፈፅሞ የነበረው የመደብ ትግል " በመጓሌ ኮ "፣ መደቦች፣ የኅብረተሰብ ክፍሎች እንደ መደብ ተደራጅተው ለጥቅማቸው እንዳይታገሉ በድርጎና በመንግሥት መዋቅሩ በመታገዳቸው የምርት ኃይሎች ከማደግ ታፈኑ ። የሰዎች የነጻ ፈጠራ አንደገና ታሠረ ። ይህ እንደኛው መልኩ ሲሆን፣ የፖለቲካ ነጻነት ጥያቄ ጉዳይ ባለመፈታቱና ከዚህ ጋር ተያይዞ የነፃ በሌሬ "እንደ ገዢ" መደብ ያለ / State class / ባለመፈጠሩ፣ ቢሮክራት ግን ሥልጣኑን የመሰደው ደርግ ይህንን ሚና አየተጫወተ የምርት ኃይሎች ከተተበተበት ሰንሰለት / ርዕዮተ ዓለማዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባሕላዊ ... ወዘተ / እንዲላቀቁና የመደብ ትግሉ እየተፋፋመ፣ የምርት ኃይሎች አያደጉ፣ ምርት ከፍ አያለ የኅብረተሰቦችን የምግብ ቢሰም የኢኮኖሚ ችግር እንዲፈታ ሊያደርግ አልቻለም ። በመሆኑም ይህ ነፃት ኅሊና በመጉደሉ በተለይም ሀገሪቱ ውስጥ ያሉትን ቀላል የሆኑ የምርት ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች በአዲስ መልክ አዘጋጅቶ / restructure /፣ የበጋን ሁኔታ ልዩ አትኩሮ ተሰጥቶት ለረሀቡ መፍትሔ የሚሆን እርምጃ ሊወሰድ አልቻለም ። ይህም ማለት ለንደዚህ ዓይነት ኅብረተሰብና የፖለቲካ አወቃቀር፣ በተለይም ለረጅም ጊዜ በሌላ የኃይል / Energy / አጠቃቀም ባይሆን፣ የኅብረተሰቡ የቀን ተቀን ኑሮ ከዚፍ ቀረጣና ይህንን ከመጠቀም ጋር በተያያዘበት በታ፣ የተፈጥሮ ፀጋ በመነፈጉ የተጋለጠው መሬት፣ በዝናብ አለመምጣት ቢሰም ለድርቅ መንገስ ምክንያት ስለሚሆን ረሀብ ዕጣው ይሆናል ማለት ነው ። ይህንን ሁኔታ መለወጥ የሚቻለው ደግሞ የተጓ የአስተራረስ፣ የአመራረት፣ የአስተባበር ለውጦች ሲደረጉ ነው ። ለዚህም ሌላ አብዮት ያስፈልጋል ማለት ነው ።

በጥናቱ ውስጥ ለማሳየት እንደተሞከረው፣ ይህንን በሚገባና ታሪካዊ ኃላፊነት ለመቀበል ያልቻለው ደርግ፣ ከስምንት ዓመት ጀምሮ ሀገሪቱን ጠርነት ውስጥ ዘፍቋታል ። እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ / structurally / ባለተለጋጠው የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ውስጥ የባስ ድንነትን፣ ረሀብን፣ የብዙ ባሕላዊ ጠቃሚ የአኗኗር ዘዴዎች መፈረካከስን፣ ጥገኛነትን የሚያመጣ የዘራፊ ጥምጥም ይሆናል ። ዝር ዝር የፖለቲካ ጥያቄ በኢትዮጵያ ምድር ውስጥ ስላልተፈታ፣ የረሀቡ ምክንያት፣ ዋናው የዘረው አገዛዝ ነው ማለት ነው ። የሶቭየት ኢምፔሪያሊዝም በዚህ ረሀቡን በማምረት፣

በማባባስ ኪተመጽዋችነት በፍጹም ሊያመጣው አይችልም ። ኢትዮጵያችን ለዘለዓለም ጥገኛው እንድትሆን ስለሚፈልጉና እውነተኛ ነጻነት እንድታገኝ ስለማይሹ፣ የመደብ ትግሉ እንዳይፋፋም በማድረግ የጦር መሣሪያ አቀባይነትን ሞኖፖል በመያዝና በዚህ አስታኮ በመበዝበዝ፣ ነዋሪ ውስጥ አየሮፕች እንዲትናር የሚያደርግ ነው ። ይህንን ሞኖፖሉን እስኪያዘ ድረስና፣ የጦር መሣሪያውን በሕዝባችን ላይ እስከ አራገፈ ድረስ፣ ምዕራቦች ገብተው በአንዳንዱ መስክ " እርዳታ " ቢያደርጉም ጥቅም ያገኛል እንጂ አይጎዳም ።

እንደዚህ ደግሞ፣ ለረሐቡ የወጡ ሀገሮች እርዳታ ቢያስፈልገንም፣ ይህ ደግሞ ምንም ዓይነት መፍትሔ እንደማያመጣ መታወቅ አለበት ። ሆኖም ግን መፍትሔ አያመጣም ተብሎ እርዳታ ከመለመን፣ ችግሩን ከማባበቅ፣ ዋናውን ምክንያት ከማመልከት መቆጠብ አያስፈልገንም ። ከዚህ ሁሉ ገን፣ በእርግጥ ለሀገራችን ስሜት ካለን፣ ለሕዝባችን የምናስብ ከሆነ ፣ ሀገራችን ወደ ፊት ስታመራ የሚፀዱትን ከሆነና እንቅፋት የሚሆነን ከሆነ እስቲ በጋራ መታገሉን እናስበበት ። በዚህና በዚያ ተበጣጥሮ መታገል፣ ናፈ ለገው ያህል መጠናከር ይዞር፣ የፈለገውን ያህል ዝግጅት ዱላ ይገኝ፣ ይህ በፍጹም መሠረት ያለው መፍትሔ አይሆንም ። ይልቁንስ የዚያችን ሀገር ችግር ተረድተን፣ የሕዝባችንን ስቃይና መከራ ተገንዝበ፣ ከአልኮኝነት፣ ከገርዝነት ባሻገር ዲሞክራሲያዊና ፖለቲካዊ ባሕልን የፈጠ አያደረጉ ለሕዝባችን ነጻነት መታገል የዜጋው እንገርጋቢ ጥያቄ ነው ። ይህንን ካላደረገን፣ ነፃታችንን አያስተጋገዝ ታሪካዊ ኃላፊነትን ለመቀበል ዝግጁ ካልሆን፣ በበቦ በአስባቡ እርር ለመታገል የሚደረገውን ጥረት የምናስናኪል ከሆነ፣ የእኛ ዲሞክራትነት፣ ነጻነት ፈላጊነት ትልቅ ጥያቄ ውስጥ ይገባል ።



ሰፊ ጥናት ለማድረግ ለሚፈልጉ የሚከተሉትን መጻህፍት፣ መጽሔቶችና ስታትስቲክሶች መጠቀም ይቻላል ።


1. Amin S ; Accumulation on a world scale.New York & London, 1974 .

2. Cohn J ; Foreign Involvment in Land Tenure Reform. The case of Ethiopia . In: International Dimensions of Land Reform. Boulder & London, 1984 .

3. Collins J. & Lappe F: The Myth of Hunger. San Francisco, 1977.

4. George S; How the other Half dies . The Real Reasons for the World Hunger. USA,1977.

5. Harrison P: Hunger & Poverty. " Inside the Third World " London, 1979.

6. Lundström K; North-eastern Ethiopia : Society in Famine.Uppsala, 1976.

7. ME ISONE ; New Ethiopia: Famine Who is to blame? December,19 4.

8. Mesfin W.Mar.; Vulnerability to famine in Rural Ethiopia 1958-77. In: The Proceedings of the Seventh International Conference of Ethiopian Studies. Uppsala,1984.

9. Mooney P: Seeds-Multis & World Hunger. Hamburg 1981.

10.Nelson D; & Kaplan I; Ethiopia a country Study.Washington D.C. 1981.

11.Pankhurst R: Economic History of Ethiopia 18oo-1935 . Addis Ababa 1968.

12.Payer C: The World Bank. New York, 1982

13.Samater M.I; From " Growth" to "Basic Needs". The Evolution Of Develoment Theory . In: Monthly Review.New York, October 1984

14. Shepherd J : The Politics of Starvation. New York, 1975.

15. Tetzlaff R: The World Bank Power Instrument of the USA or Help for the Third World ? Münich-Köln-London, 1983

## ስታትስቲክስና መጽሄቶች

1. Quarterly Bulletin New Series. Vol.5 No.1 March 1979. Issued by: Economic Research & Planing Division National Bank Of Eth.

2. Quarterly Economic Review of Ethiopia. Annual Suppl. 1983.

3. The Journal of Modern African Studies. January 1982.

4. The Journal of Development Studies 1980.

5. Wirtschaftliche Entwicklung Äthiopiens. 1982/83.

6. የብሄራዊ አብዮታዊ የምርት ዘመቻ የመጀመሪያ ዐመት ዕቅድ :: 1971/72 ዓ.ም አንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር፣ አዲስ አበባ 1971.